አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ
BIIROO BARNOOTA BULCHINSA MAGAALAA FINFINNEE
ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION EDUCATION BUREAU

# አማርኛ

## እንደ መጀመሪያ ቋንቋ

## የተማሪ መጽሐፍ

## ፫ኛ ክፍል



፫ኛ ክፍል

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ
BIIROO BARNOOTA BULCHINSA MAGAALAA FINFINNEE
ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION EDUCATION BUREAU


# አማርኛ

## እንደ መጀመሪያ ቋንቋ

## የተማሪ መጽሐፍ

## 5ኛ (፭) ክፍል


**አዘጋጆች**

መላኩ ጌቶ መኮንን

መስፍን ተካ በርሔ

ውበቱ በዛብህ የሱፍ

**ገምጋሚዎችና አርታኢዎች**

መስፍን ደፈረሱ ወ/መድህን

ትንቢት ግርማ ኃይሉ

ፋሲል ብዙነህ በቀለ

**ጥራት ተቆጣጣሪና ገምጋሚ**

ፍሬሕይወት አሰፋ ከበደ

**አስተባባሪ፡-** ጌታቸው ታለማ አጥናፉ

**ምስል እና አቀማመጥ፡-** እንጦጦ ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ(TMS)

© የመጽሐፉ ህጋዊ ቅጂ ባለቤት 2014 ዓ.ም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ነዉ፡፡

# ምስጋና

ይህን የትምህርት መጽሐፍ ከዝግጅት ጀምሮ በከተማችን በሚያስተምሩ መምህራን እንዲዘጋጅ በማድረግ፣ አስፈላጊውን በጀት በማስፈቀድ እንዲሁም በጥብቅ ዲስፕሊን እንዲመራ ላደረጉት ከፍተኛ ሙያዊና አስተዳደራዊ ድጋፍ ላደረጉት ለትምህርት ቢሮ ኃላፊ **አቶ ዘላለም ሙላቱ** ፣
እንዲሁም የዝግጅቱ ስራ ቁልፍ ስራ መሆኑን ተረድተው ትኩረት በመስጠት በሚያጋጥሙ ችግሮች መፍትሄ በመስጠት፣ የአፈጻጸም ሂደቱን በመከታተል፣ በመገምገምሁሌም ከጎናችን ለነበሩ የትምህርት ቢሮ የማኔጅመንት አባላት የስርዓተ ትምህርት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ **አቶ አድማሱ ደቻሳ** ፣ የትምህርት ቴክኖሎጂ ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ **አቶ ዳኛው ገብሩ**፣ የመምህራን ልማት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ **አቶ ሳምሶን መለሰ** ፣ ለትምህርት ቢሮ ኃላፊ አማካሪ **ወ/ሮ አበበች ነጋሽ** ፣ ለትምህርት ቢሮ ጽ/ቤት ኃላፊ **አቶ ሲሳይ እንዳለ** ፣ ለቴክኒክ አማካሪ **አቶ ደስታ መርሻ** ላበረከቱት አስተዋጽኦ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

በመጨረሻም መጽሐፉ ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ የትምህርት ቤት ርዕሰ መምህራን ለአዘጋጅ መምህራን ከዚህ በላይ ስራ የለም በማለት ፍቃድ በመስጠትና የሞራል ድጋፍ ስላደረጋችሁም ምስጋናችን እናቀርባለን፡፡

## ማውጫ


ገጽ

ምዕራፍ አንድ

ጓደኝነት.....................................................1

ምዕራፍ ሁለት

ጽዳትና ንጽህና..............................................14

ምዕራፍ ሶስት

ልማድ.....................................................30

ምዕራፍ አራት

የትራፊክ ደህንነት.........................................43

ምዕራፍ አምስት

አካባቢ ጥበቃ..............................................54

ምዕራፍ ስድስት

ጸረ አደንዛዥ እጾችና ንጥረ ነገሮች.............................70

ምዕራፍ ሰባት

ምግብ.....................................................86

ምዕራፍ ስምንት

በኢትዮጵያ የሚገኙ የዱር እንስሳት............................103

ምዕራፍ ዘጠኝ

ባህላዊ ጨዋታዎች.........................................118

ምዕራፍ አስር

ስነ ቃል...................................................134

ዋቢ መጽሐፍ...........................................................

አባሪዎች.................................................

## መግቢያ

ይህ መጽሐፍ የ5ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋን በአፍ መፍቻነት ለሚማሩ ተማሪዎች በቋንቋው በብቃት ማዳመጥ፣ መናገር፣ማንበብ እና መጻፍ እንዲችሉ በተጨማሪም የቃላት እና የሰዋሰው ዕውቀት እንዲያገኙ ለማድረግ ተሻሽሎ የተዘጋጀው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ሥርዓተ ትምህርት አካል ነው። ከዚህ በተጨማሪም መጽሐፉ ስለነዚህ የክፍል ደረጃዎች ሥርዓተ ትምህርትና ስለሚሰጡ ትምህርቶች ሽፋን መረጃ ይሰጣል። በመሆኑም ተማሪዎችና ወላጆች በትምህርት ቤት የተከናወኑ ተግባራትን ለማስቀጠልና ይበልጥ ለማዳበር በጋራ ለመሥራት ያስችላቸዋል።

## መሰረታዊ መርሆዎች

- ተማሪዎች በማህበረሰብ ሕይወት ውስጥ አስፈላጊ ስለሆኑ የማዳመጥ ይዘቶችና ርዕሰ ጉዳዮችን ይማራሉ።
- ተማሪዎች ስለነዚህ የማዳመጥ ይዘቶችና ርዕሰ ጉዳዮች የተጻፉ ምንባቦችን ካዳመጡ በኋላ በእነሱ ላይ በመመስረት ይናገራሉ።
- በቀጣይም በማሕበረሰቡ ውስጥ አስፈላጊ ስለሆኑ የምንባብ ይዘቶችና ርዕሰ ጉዳዮች ይማራሉ። ስለነዚህ የምንባብ ይዘቶች የተጻፉ ምንባቦችን ካነበቡ በኋላ በእነሱ ላይ በመመስረት ጽሁፍ ይጽፋሉ።
- የቋንቋ፣ ክሂሎች የቃላትና የሰዋሰው ትምህርቶችን በየምዕራፉ በተገለጸው ዓላማ መሰረት ይማራሉ።
- ተማሪዎች በምዕራፎቹ ይዘቶችና በርዕሰጉዳዮች ላይ ተመስርተው የቀረቡ ጽሁፎችን በሚማሩ ቢጤዎቻቸውና በቡድን አብረዋቸው ከሚሰሩ ተማሪዎች ይማራሉ።

## በቤት ውስጥ ከቤተሰብ ጋር መማር

ተማሪዎች በትምህርት ቤት የሚቀስሟቸውና በቤታቸው ከወላጆቻቸው ጋር የሚሠሯቸው በርካታ ትምህርታዊ ተግባራት አሉ፤ ስለዚህ ወላጆች ከእነዚህ በርካታ ተግባራት ቢያንስ የተወሰኑትን ከልጆቻቸው ጋር በጋራ እንዲሠሩ ይጠበቃል።

፩. የየእለቱን ትምህርት ከቴሌቪዥን፣ ከሬዲዮ ወይም ከድረገጽ ስለርዕሰ ጉዳዩ አዳምጡ ወይም ተመልከቱ።

፪. ልጆች የተሰጣቸውን የቤትሥራ ሲሠሩ ወላጆቻቸውን ወይም ሌሎች የቤተሰብ አባላትን በቃለመጠይቅ፣ ንግግርን በመጻፍ ወይም በንግግር ልምምድ ወቅት በመሳተፍ አብሮ መሥራት ተገቢ ነው።

፫. ወላጆች የሳምንቱን ወይም የዕለቱን የምንባብ ይዘቶች ወይም ርዕሰ ጉዳዮች ልጆቻችሁን በመጠየቅ ተረዱ። በትምህርት ቤት ያነበቧቸውን ምንባቦች በጋራ አንብቡ። ይህንንም ልጆች ወይም ወላጆች ለብቻ ወይም በየተራ በማንበብ ሊተገብሩት ይችላሉ።

፬. ልጆቻችሁን የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ስለምንባቡ ተወያዩ።

፭. ስለርዕሰ ጉዳዩ የሚያወሱ ሌሎች ጽሁፎችን ከመጻሕፍት፣ ከጋዜጦች ወይም ከመጽሔቶች ፈልጋችሁ አንብቡ።

፮. በግል ያንብቡ (ልጆች ራሳቸውን ችለው በግላቸው እንዲያነቡ አበረታቱ)፤ ከዚያም ስላነበቡት ጉዳይ ተወያዩ።

፯. ልጆች በክፍል ውስጥ ምን ምን እንደተማሩ ደብተራቸውን በጋራ ተመልከቱ፤ ስለምን እንደተማሩና ምን እንደተሰማቸው የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች በማንሳት ተወያዩ።

፰. የመጻፍ ችሎታቸውን ለማዳበር የተማሯቸውን ዝርዝር ክሂሎች በመረዳት ምን እንደተማሩ ለማወቅ የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች ልጆቹን

ጠይቋቸው:: ለምሳሌ:- የቃላቱ ፊደላት በተገቢ ሁኔታ ተጽፈዋል? በዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉት ሥርዓተነጥቦች (አራት ነጥብ፣ነጠላ ሰረዝ፣ ድርብ ሰረዝና የመሳሰሉት) በተገቢ ቦታቸው ገብተዋል? ወዘተ.

፱. ልጆች አጫጭር ደብዳቤዎችን ለቤተሰብ አባላት ወይም ለጓደኞች እንዲጽፉ፤ በእለቱ ወይም በሳምንቱ ስለተከሰቱ ጉዳዮች ያላቸውን አስተያየት ወዘተ. እንዲጽፉ አበረታቷቸው::

# አማርኛ
## ፭ኛ ክፍል

# ምዕራፍ አንድ
# ጓደኝነት

ከምዕራፉ የሚጠበቅ ውጤት

ይህንን ምዕራፍ ተምራችሁ ከጨረሳችሁ በኋላ፡-

- ስለጓደኝነት ያላችሁን አመለካከት አዳምጣችሁ ታንጸባርቃላችሁ፡፡
- ጽሑፉን አንብባችሁ መልእክቱን ትገልጻላችሁ፡፡
- ከጓደኞቻችሁ ጋር እንዴት ጊዜ እንደምታሳልፉ በቀላል ዓረፍተነገር አንቀጽ ትጽፋላችሁ፡፡
- ምንባቡን መሰረት አድርጋችሁ ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን ትመልሳላችሁ፡፡
- ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች ትሰጣላችሁ፡፡
- የወልና የተጸውዖ ስሞችን ትለያላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ፦ ማዳመጥና መናገር

# የንጉሱ ልጆች



### ቅድመ ማዳመጥ

### ተግባር 1

**የሚከተሉት ቃላት ያላቸውን ፍቺ ለመምህራችሁ በቃል ተናገሩ።**

ሀ. ሰረገላ
ለ.አጀብ
ሐ. እልፍኝ
መ. ፈረስ ጉግስ
ሠ. አደጋ ጣዮች
ረ. ግዳይ

### ተግባር 2

**ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች በቃላችሁ አጭር መልስ ስጡ።**

ሀ. ልጆች መስማት ያለባቸው ምክር የወላጆቻቸውን ነው ወይስ የጓደኞቻቸውን? ለምን?

ለ. ከላይ የቀረበውን ስዕል በመመልከት የምታዳምጡት ምንባብ ስለምን እንደሚያወሳ ገምቱ።

## አዳምጦ መረዳት

### ተግባር 1

**ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ታሪክ መሰረት ትክክል የሆነውን ‹‹እውነት›› ትክክል ያልሆነውን ደግሞ ‹‹ሀሰት›› በማለት በቃል መልሱ፡፡**

ሀ. የምዕራቡ ንጉስ ከህግ ሚስቱ የወለደው አንድ ልጅ ብቻ ነበር፡፡

ለ. የኔ ቢጤዋ ልጅ ከንጉሱ ልጅ በእድሜ የሚበልጥ ነው፡፡

ሐ. የኔ ቢጤዋ ልጇን ለንጉሱ ለመስጠት ፍላጎት አልነበራትም፡፡

መ. ንጉሱ ለኔ ቢጤዋ ልጅ ከወለደው ልጅ እኩል እንክብካቤ ያደርግለት ነበር፡፡

ሠ. ከአንድ ዛፍ ላይ ወጥቶ ምሽቱን ያሳለፈው የንግስቲቱ ልጅ ነበር፡፡

### ተግባር 2

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ታሪክ መሰረት በቃላችሁ መልሱ፡፡**

ሀ. ዛፍ ላይ የወጣው ባለታሪክ ምሽቱን ዛፍ ላይ ወጥቶ ለማሳለፍ የተገደደው ለምንድን ነው?

ለ. ሁለቱ ወንድማማቾች ተቀጣጥረው የተለያዩት ለምንድን ነው?

ሐ. ባለታሪኩ ከገደላቸው እንስሳት እየቆረጠ በኮሮጆ የሚያስገባው ለምንድን ነበር?

መ. የንጉሱ ልጆች ከቤተ-መንግስት ሹልክ ብለው አጃቢ ሳያስከትሉ መሄዳቸው ተገቢ ነው ብላችሁ ታስባላችሁ? ለምን?

ሠ. ካዳመጣችሁት ታሪክ ምን ተማራችሁ?

ረ. ሴትዮዋ ልጇን ለንጉሱ መስጠቷ ተገቢ ነው ትላላችሁ?

ሰ. ባለታሪኩ ቀጥሎ ምን የሚገጥመው ይመስላችኋል?

## ክፍል ሁለት፡- ንባብ

## ጓደኛ መሆን

### ቅድመ ንባብ

#### ተግባር

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃል መልስ ስጡ፡፡**

ሀ. ጓደኝነት ማለት ምን ማለት ነው?

ለ. በሁለት ጓደኞሞች መካከል አለመግባባት ቢፈጠር ምን ማድረግ አለባቸው ብላችሁ ታስባላችሁ?

### የንባብ ሒደት

#### ተግባር

**የሚከተለውን ምንባብ በለሆሳስ (ድምፅ ሳታሰሙ) አንብቡ፡፡**



## ጓደኛ መሆን

ሁለት እጅግ የሚዋደዱ ጓደኛሞች ነበሩ፡፡ የትም ቦታ ሲሄዱ አይለያዩም ነበር፡፡ እንደለመዱት አብረው ወደ አንድ ሀገር በእግራቸው ይጓዙ ነበር፡፡ መንገድ በዝምታ ይረዝማልና እየተጫወቱ ነበር የሚጓዙት፡፡ አንዳንድ ጨዋታ በድካም መንፈስ ከተጫወቱት ለጠብ ይዳርጋል፡፡ ድካም የትዕግስትን አቅም ይፈታተናልና፤ ለዚህ ነው የሀገሬ ሰው ‹‹የድካምና የእረፍት ጨዋታ ለየቅል ነው›› የሚለው፡፡ እነዚህም ጓደኛሞች የእረፍትን ጨዋታ በድካም አምጥተውት ኖሮ አለመግባባት ተፈጠረ፡፡ አንደኛው ታዲያ ብልጭ ሲልበት በቡጢ ግጥም የማድረግ ልምድ ነበረበትና በጓደኛው ላይ ዓለም ያወቀው ቦክሰኛ የሆነው ታይሰን የማይችለውን ቡጢ ሰነዘረበት፡፡ ቡጢውን የቀመሰው ጓደኛውም የፊቱን ደም ጠርጎ እያበጠ የሄደውን ግንባሩን ዳበሰው፡፡ እጅግም አዘነና ጉዞውን አቋርጦ በበረሀው አሸዋ ላይ ተቀመጠ፡፡ አንገቱን ግራና ቀኝ እያወዛወዘ ሀዘኑን ገለጠ፡፡ ንዴቱ በውስጡ እንደሚንተከተክ ሽሮ ቡልቅ ቡልቅ ይልበት ጀመር፡፡ መልሰህ ‹‹በለው! በለው!›› እያለ ስሜቱ አስቸገረው፡፡

ጓደኛሞቹ ምንም ሳያወሩ ቢሄዱ ኖሮ የሚጣሉ ይመስላችኋል?

ከዚህ በኋላ በጓደኛው ላይ ምን የሚያደርግ ይመስላችኋል?

ያን ጊዜ አይኑን አማተረና አንዳች እንጨት ፈልጎ አገኘ፡፡ በአሸዋም ላይ ‹‹ዛሬ እጅግ የምወደው ጓደኛዬ ግንባሬ ላይ በቡጢ መታኝ›› ብሎ ጻፈ፡፡ ቀና ብሎ ሲያይም ጓደኛው ጥሎት በመሄድ ላይ ነበር፡፡ እርሱም ያንን ጽሑፍ በአሸዋው ላይ ትቶት ጓደኛውን ተከትሎት ሄደ፡፡ ብልጭ ብሎበት የተማታው ጓደኛውም እጅግ ተጸጸተ፡፡ በጓደኛው እግር ላይ ወድቆም ይቅርታ ጠየቀ፡፡ የተመታውም ይቅርታውን ተቀብሎ አብሮት ተጓዘ፡፡ የነበረውን ሁሉ ረስተው ደስ የሚል ጨዋታ እየተጫወቱ ተጓዙ፡፡ በመንገዳቸው ላይ አንድ ወንዝ ጋር ደረሱ፡፡ በአሸዋውና በሙቀቱ የተነሳ ተዳክመውና በላብ ተዘፍቀው ስለነበር ልብሶቻቸውን አውልቀው ወደ ወንዙ ገቡ፡፡ ወዲያና ወዲህ እየዋኙ ድካማቸውን በመርሳት ላይ እያሉ ያ በቡጢ የተመታውን ልጅ ወንዙ ነጥቆ ይዞት ሄደ፡፡

ሁኔታውን ያየው ሌላኛው ጓደኛውም ያለ የሌለ ጉልበቱንና ብልሀቱን ተጠቅሞ እየዋኘ ጓደኛውን በወንዝ ከመወሰድ ታደገው፤ በአንድ እጁ እየሳበም ወደዳር አደረሰው፡፡ በወንዝ ከመወሰድ የዳነው፤ ከወንዝ ከወጣ በኋላ አሸዋው ላይ ተቀምጦ በአቅራቢያው ያገኘውን አለት ባልጩት ድንጋይ መቀጥቀጥ ጀመረ፡፡ ለብዙ ሰአታት ከቀጠቀጠ በኋላ በድንጋዩ ላይ ‹‹ዛሬ እጅግ የምወደው ጓደኛዬ ሕይወቴን ከሞት ታደጋት›› ብሎ ጻፈ፡፡

አስቀድሞ የተማታው በኋላም ጓደኛውን ያተረፈው በሆነው ነገር ሁሉ ተገረመ፡፡ ጓደኛውንም እንዲህ ሲል ጠየቀው "ቅድም ግንርባህን በቡጢ ስመታህ፤ <የምወደው ጓደኛዬ ግንባሬን መታኝ> ብለህ በአሸዋ ላይ ጻፍክ፡፡ አሁን ግን በወንዙ ከመወሰድ ሳድንህ <የምወደው ጓደኛዬ ሕይወቴን ከሞት ታደጋት> ብለህ በድንጋይ ላይ ጻፍክ፡፡ የመጀመሪያውን በሚጠፋ አሸዋ ላይ ይህንን ግን በማይጠፋ ድንጋይ ላይ ጻፍከው፡፡ ለምን?" ጓደኛውም መለሰ፡፡ <<ቅድም ጉዳት አደረስክብኝ፤ እኔም አዘንኩብህ፤ ተቀየምኩህም፤ ተሰምቶኛል፤ ተናድጃለሁም፤ ነገር ግን የእኔና የአንተ ባልንጀርነት እንዲቀጥል ከተፈለገ መርሳት

መቻል አለብኝ፤ ስለዚህ በአሸዋ ላይ ጻፍኩት፡፡ አየህ ሰዎች በእኛ ላይ ክፉ ሲያደርሱብን የይቅርታ ነፋስ ጠርጎ ሊወስደው ይችል ዘንድ በአሸዋ ላይ ብንጽፈው መልካም ነው፡፡ በኋላ ሕይወቴን ከሞት ስትታደጋት ግን ዘወትር እንዳስታውሰው ስለምፈልግ በማይጠፋ ድንጋይ ላይ ጻፍኩት፡፡ ሰዎች የሚያደርጉልንን በጎ ነገር ሁሉ ማንም ሊያጠፋው በማይችል ልብ ላይ መጻፍ አለብን፡፡ ጓደኞችንን መውደድ የምንችለው በጎ ነገሮችን አዘውትረን ካስታወስን ብቻ ነው፡፡>> ጓደኛውም አቀፈው፡፡ (ምንጭ፡- ዳንኤል ክብረት፤ 2008፤ የሚከራዩ አማትና ሌሎች፤ ገጽ 9-11)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር 1

**ቀጥሎ በ‹‹ሀ›› ረድፍ በምንባቡ ውስጥ ያሉ በአንቀጾች ቅደም ተከተል የቀረቡ ሲሆን በ‹‹ለ›› ረድፍ ከቀረቡት የየአንቀጾቹ ዋና ዋና ሀሳቦች ጋር በማዛመድ መልሱ፡፡**

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. አንቀጽ አንድ | ሀ. በቡጢ የተመታው ልጅ በአሸዋ ላይ ጻፈ፡፡ |
| 2. አንቀጽ ሁለት | ለ. በጓደኞሞቹ መካከል አለመግባባት ተፈጠረ፡፡ |
| 3. አንቀጽ ሶስት | ሐ. የተማታው ልጅ ተጸጽቶ ይቅርታ ጠየቀ፡፡ |
| 4. አንቀጽ አራት | መ. የትም ቢሄዱ የማይለያዩና የሚዋደዱ ጓደኛሞች ነበሩ፡፡ |

### ተግባር 2

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ሆሄ በመምረጥ መልሱ፡፡**

1. በምንባቡ ሀሳብ መሰረት የትዕግስትን አቅም የሚፈታተነው ምንድን ነው?

ሀ. ይቅር ባይነት ለ. ድካም ሐ. እልኸኛነት መ. ረሀብ

2. በቡጢ የተመታው ልጅ ማዘኑን የገለጸው ምን በማድረግ ነው?

ሀ. አንገቱን በማወዛወዝ ለ. በማልቀስ

ሐ. አሸዋ ላይ በመጻፍ መ. ይቅርታ በመጠየቅ

3. ‹‹ዛሬ እጅግ የምወደው ጓደኛዬ ግንባሬ ላይ በቡጢ መታኝ›› ብሎ የጻፈው ምን ላይ ነው?

ሀ. በድንጋይ ላይ ለ. በአለት ላይ

ሐ. በወረቀት ላይ መ. በአሸዋ ላይ

4. በቡጢ የተማታው ልጅ ጓደኛው እግር ላይ የወደቀው ለምንድን ነው?

ሀ. እየሮጠ ሲሄድ ለ. ጓደኛው በቡጢ ስለመታው

ሐ. ይቅርታ ለመጠየቅ መ. ጓደኛውን ለመጣል

5. ጓደኛሞቹ ልብሳቸውን አውልቀው ወደ ወንዝ የገቡት ለምንድን ነው?

ሀ. ውሃ ለመጠጣት ለ. ስለደከማቸው

ሐ. ዋና ስለሚወዱ መ. ልብሳቸውን ለማጠብ

ተግባር 3

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ በመጻፍ መልሱ፡፡**

ሀ. ‹‹መንገድ በዝምታ ይረዝማል›› የሚለው ዓረፍተነገር የያዘውን ሀሳብ አብራርታችሁ ግለጹ፡፡

ለ. ‹‹የድካምና የእረፍት ጨዋታ ለየቅል ነው››የተባለበት ምክንያት ምንድን ነው?

ሐ. በቡጢ የተመታው ልጅ አለቱን በባልጩት ሲቀጠቅጥ የነበረው ለምንድን ነው?

## ክፍል ሦስት፡- ቃላት

### ተግባር 1

**ቀጥሎ በ‹‹ሀ›› ረድፍ ለቀረቡት ከምንባቡ የወጡ ቃላትና ሐረጋት ተመሳሳይ ፍቺዎቻቸውን በ‹‹ለ›› ረድፍ ከቀረቡት በመምረጥ እያዛመዳችሁ መልስ ስጡ፡፡**

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. ጉልበት | ሀ. ተመለከተ |
| 2. እየተጨዋወቱ | ለ. አቅም |
| 3. አማተረ | ሐ. ጡጫ |
| 4. ብልጭ አለበት | መ. እያወሩ |
| 5. ቡጢ | ሠ. በራበት |
| 6. ባልንጀርነት | ረ. ተናደደ |
| | ሰ. ወዳጅነት |

### ተግባር 2

**ከዚህ በታች በቀረበው አንቀፅ ውስጥ ያሉትን ባዶ ቦታዎች በቅንፍ ውስጥ በቀረቡት ቃላት ተቃራኒ ፍቺያቸው አሟሉ፡፡**

መጥፎ ሰው የጓደኛው________(ወዳጅ) ስለሆነ ሁልጊዜ የሚመኘው በጓደኛው ላይ______________(በጎ) ማድረግን ነው፡፡ ከዚህም በላይ ጓደኛው ሲሳሳት______ ______(ለይቅርታ) ይቸኩላል፡፡ በአጠቃላይ የመጥፎ ሰውና የክፉ ሰው ባህሪ____ ___________(ተመሳሳይ) ነው፡፡

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

### የአንቀጽ ተዋቃሪ አካላት

አንቀጽ ስለአንድ ሀሳብ ብቻ የሚገልጹ ዓረፍተነገሮች ስብስብ ሲሆን ሁለት ተዋቃሪ አካላት አሉት። እነሱም ዋና ዓረፍተነገር እና መዘርዝራዊ ዓረፍተነገር ናቸው።

**ዋና ዓረፍተነገር**፡- በአንቀጹ የሚነሳውን ጉዳይ ጠቅለል አድርጎ የሚያነሳ የአንቀጹ ክፍል ነው። ይህ የአንቀጽ ክፍል በተጨማሪም ኃይለ ቃል ፣ መሪ ዓረፍተነገር ወይም መንደርደሪያ ዓረፍተነገር በመባል ይታወቃል።

**መዘርዝራዊ ዓረፍነገር**፡- በመንደርደሪያ ዓረፍተነገሩ የተገለጸውን ሀሳብ የሚያጠናክሩ ወይም የሚያብራሩ ዓረፍተነገሮች ናቸው።

ዋና ዓረፍተነገርንና መዘርዝራዊ ዓረፍተነገርን ለመለየት የሚከተለውን ምሳሌ ተመልከቱ።

አውቶብሱ መንገዱን እንደያዘ ሦስት ዓይነት ጩኸት ማሰማት ጀመረ። አንደኛው የሞተሩ ጩኸት፣ ሁለተኛው የመኪናው ጥሩምባ (ክላክስ) ጩኸት፣ ሦስተኛው የአውቶብሱ የቴፕ መጫወቻ ጩኸት ነበር። "ድሮ ተሳፋሪዎች ገፋኸኝ፤ ቦታዬን ወሰድክብኝ፤ እግሬን ረገጥከኝ፤ ልጄን ተጫንሻት" እያሉ ያሰሙት የነበረው ጩኸት የአውቶቡሶቹ ውስጣዊ ሁኔታ በመሻሻሉ የቀረ ይመስላል። ስለሆነም በአሁኑ ጉዞዬ ስላልሰማሁት ከቁጥር አላስገባሁትም።

ከላይ በቀረበው አንቀጽ "አውቶብሱ መንገዱን እንደያዘ ሦስት ዓይነት ጩኸት ማሰማት ጀመረ።" የሚለው ዋና ዓረፍተነገር ሲሆን ቀሪዎቹ ደግሞ መዘርዝራዊ ዓረፍተነገሮች ናቸው።

ተግባር 1

**የሚከተለውን አንቀፅ በደብተራችሁ ላይ ከፃፋችሁ በኋላ ከኃይለ ቃሉ ስር በማስመር ለመምህራችሁ አሳዩ።**

ከሰው ልጆች ማኅበራዊ ችግሮች አንዱ ወንጀል ነው። ወንጀል በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ ተቀባይነት የሌለው ተግባር ነው። ወንጀል የሚሰራ ሰው በማኅበረሰብ ላይ ብቻ ሳይሆን በቤተሰቡ ላይም ከፍተኛ ጉዳት ያደርሳል። ወንጀለኛ

የሚያስተዳድራቸውን የቤተሰብ አባላት በሚገባ ሊያኖራቸው አይችልም።

ተግባር 2

**የሚከተለውን የቢጋር ሠንጠረዥ መሰረት በማድረግ ኃይለ ቃልና መዘርዝራዊ ዐረፍተነገሮችን የያዘ አንቀፅ ጽፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡ።**

የሌላዉን ዕቃ ሳያስፈቅዱ አለመንካት + መጥፎ ቃላትን አለመጠቀም + ለሌላዉ ትህትና ማሳየት = ጥሩ ጓደኞች መሆን

## ክፍል አምስት፡- ሰዋስው

**ማስታወሻ**

**የተጸውዖ ስም እና የወል ስም**

የተጸውዖ ስም የሚባለው የአንድ ግለሰብ፣ ቦታ፣ ሀገር፣ ወዘተ. የግል ስያሜ (መጠሪያ) ነው።

ምሳሌ፡- ዳንኤል፣ ሰይድ፣ ትንቢት፣ ማህሌት፣ አንሻ፣ ኢትዮጵያ፣ ጅማ፣ አዲስ አበባ

የወል ስም የሚባለው ደግሞ ተመሳሳይ ግብር ያላቸው ሰዎች ወይም ቡድኖች የጋራ መጠሪያ ነው።

ምሳሌ፡- ሰው፣ በግ፣ ላም፣ ወፍ፣ ተማሪ፣ መምህር፣ ከተማ

ተግባር

**የሚከተለውን ሠንጠረዥ በደብተራችሁ ላይ በማዘጋጀት ቀጥሎ ከ"ሀ" እስከ "ተ" የተዘረዘሩትን ቃላት በትክክለኛው የስም ምድባቸው ላይ የ‹√› ምልክት በማድረግ መልሱ፡፡**

| ተ.ቁ | ቃል | የወል ስም | የተጸውዖ ስም |
|---|---|---|---|
| ሀ | አባይ | | |
| ለ | ወንዝ | | |
| ሐ | ቀበና | | |
| መ | ልጅ | | |
| ሠ | ንጉስ | | |
| ረ | ፈረስ | | |
| ሰ | ወርቅነሽ | | |
| ሸ | አለማየሁ | | |
| ቀ | ነብር | | |
| በ | አፍሪካ | | |
| ተ | ዘበርጋ | | |

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ የተለያዩ የትምህርት ይዘቶችን ተምራችኋል፡፡

ይዘቶቹም ማዳመጥና መናገር፣ ንባብ፣ ቃላት፣ ጽሕፈትና ሰዋስው ናቸው፡፡

- አንቀጽን የሚያዋቅሩት ኃይለ ቃልና መዘርዝራዊ ዓረፍተነገሮች ናቸው፡፡ ኃይለ ቃል የአንቀጹን ዋና ሀሳብ የሚይዝ ዓረፍተነገር ሲሆን መዘርዝራዊ ዓረፍተነገሮች ደግሞ ኃይለ ቃሉን የሚያብራሩት ዓረፍተነገሮች ናቸው፡፡
- ስም በዓረፍተነገር ውስጥ በባለቤትነትና በተሳቢነት የሚያገለግል የቃል ክፍል ሲሆን የወል ስም እና የተጸውኦ ስም በሚባሉ የስም አይነቶች ይመደባል፡፡
- የወል ስም ተመሳሳይ ተፈጥሮ ያላቸው ነገሮች በጋራ የሚጠሩበት ስያሜ ሲሆን የተጸውዖ ስም ደግሞ ለአንድ ግለሰብ ወይም ነገር የሚሰጥ የግል መጠሪያ ነው፡፡

### የክለሳ ጥያቄዎች

**ለሚከተሉት የክለሳ ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡**

1. ጓደኛ መሆን በሚለው ምንባብ ውስጥ በአንደኛው እና በሁለተኛው አንቀጾች ውስጥ የሚገኙትን ኃይለ ቃልና መዘርዝራዊ ዓረፍተነገሮችን አውጥታችሁ አሳዩ፡፡
2. ቀጥሎ የቀረቡትን ስሞች የወል ወይም የተጸውኦ ስም መሆናቸውን ለይታችሁ አመልክቱ፡፡

ሀ. በሬ ለ. ተራራ

ሐ. ማክቤል መ. ወንዝ

# አማርኛ

## ፭ኛ ክፍል

# ምዕራፍ ሁለት
# ጽዳትና ንጽሕና

**ከምዕራፉ የሚጠበቅ ውጤት**

ይህንን ምዕራፍ ተምራችሁ ከጨረሳችሁ በኋላ፡-

- የሚነበብላችሁን አዳምጣችሁ ትመልሳላችሁ።
- ሰዎች ንጽሕናቸውን ለመጠበቅ የሚያከናውኗቸውን ተግባራት ትገልጻላችሁ።
- ለክፍል ደረጃው በሚመጥን መልኩ በትክክል ታነባላችሁ።
- መጣኝ ርዕስ በመምረጥ አጭር አንቀጽ ትጽፋላችሁ።
- በአዳዲስ የይዘት ቃላት ላይ ትወያያላችሁ።
- የድምጾችና የምእላዶችን መዋቅር ትገነዘባላችሁ።

ክፍል አንድ፡- ማዳመጥና መናገር

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥና መናገር

## የአካባቢ ንጽህና

### ቅድመ ማዳመጥ

**ተግባር**

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች የቃል ምላሽ ስጡ፡፡**

ሀ. የአካባቢ ንጽሕና ማለት ምን ማለት ነው?

ለ. አንድ አካባቢ ጽዳቱ የሚጠበቀው በማን ይመስላችኋል? እንዴት?

**ማስታወሻ**

አንድን ምንባብ ስታዳምጡ የሚከተሉትን የማዳመጥ መመሪያዎች ተከትላችሁ ተግብሩ፡፡

- ሙሉ ትኩረታችሁን በምታዳምጡት ነገር ላይ ማድረግ፡፡
- በምታዳምጡት ነገር ላይ ያሉትን ዋና ዋና ሀሳቦች በማስታወሻ መያዝ፡፡
- ዋናውን ሀሳብ ከዝርዝር ሀሳቦች መለየት፡፡
- የሚደመጠውን ነገር አጠቃላይ መልእክት ለመረዳት መሞከር፡፡
- የምንባቡን አቀራረብ የሚያመለክቱ አያያዥ ቃላትን በትኩረት መከታተል፡፡

## የማዳመጥ ሒደት

### ተግባር

ከዚህ ቀጥሎ መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ታሪክ ማስታወሻ በመያዝ በጥሞና አዳምጡ።

## አዳምጦ መረዳት

### ተግባር 1

የሚከተሉት ዓረፍተነገሮች የያዟቸው ሀሳቦች በምንባቡ መሰረት ትክክል ከሆኑ ‹‹እውነት›› ስህተት ከሆኑ ደግሞ ‹‹ሀሰት›› በማለት በቃል መልሱ።

ሀ. የአካባቢ ንጽሕና ተጠብቋል የሚባለው የመኖሪያ ግቢያችን ንጽሕና ብቻ ሲጠበቅ ነው።

ለ. የአካባቢ ንጽህናን መጠበቅ ለጤናማና ደስተኛ ሕይወት በቂ ነው።

ሐ. የሚበሰብሱና የማይበሰብሱ ደረቅ ቆሻሻዎችን ለይቶ ማስቀመጥ ተገቢ ነው።

መ. መርዛማ ጋዞች አካባቢን ይበክላሉ።

ሠ. የቤት ውስጥ ቆሻሻ የማስወገድ ባህልን ማዳበር ከመንግስት የሚጠበቅ ኃላፊነት ነው።

### ተግባር 2


ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች የምንባቡን ሀሳብ መሰረት በማድረግ በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ የደረሳችሁበትን ድምዳሜ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

ሀ. አንድ ሰው የማስቲካ ማሸጊያና የፍራፍሬ ልጣጮችን ሲጥል ብትመለከቱ ምን ታደርጋላችሁ?

ለ. መርዛማ ጋዞች ምን አይነት ጉዳት ሊያመጡ ይችላሉ?

## ክፍል ሁለት፡-ንባብ

### የግል ንጽሕና አጠባበቅ



### ቅድመ ንባብ

**ተግባር**

ሀ. ከምንባቡ ርዕስ በመነሳት ምንባቡ ስለምን እንደሚገልጽ ገምታችሁ ለመምህራችሁ ተናገሩ።

ለ. የግል ንጽሕናችሁን እንዴት እንደምትጠብቁ ለመምህራችሁ ተናገሩ።

### የንባብ ሒደት

**ተግባር**

**ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ ጥንድ ጥንድ በመሆን በትክክል፣ በተገቢው ፍጥነት እና አገላለጽ አንብቡ። አንዳችሁ ስታነቡ ሌላኛችሁ በሚከተለው ሰንጠረዥ ውስጥ ስህተቶችን መዝግቡ።**

| | የመገምገሚያ መስፈርት | በመጀመሪያ ንባብ | በሁለተኛ ንባብ |
|---|---|---|---|
| ሀ | በስህተት የተነበቡ ፊደላት ብዛት | | |
| ለ | ተነጥለው የተነበቡ ቃላት ብዛት | | |
| ሐ | በንባብ ጊዜ የተደገሙ ቃላት ብዛት | | |
| መ | ተገቢው ረፍት ያልተደረገባቸው ስርዓተ ነጥቦች ብዛት | | |
| | ድምር | | |

# የግል ንጽሕና አጠባበቅ

‹‹አባዬ ልሄድ ነው›› አለች ፀሀይ፡፡ ‹‹ወዴት ነው ደብተር ይዘሽ የምትወጪው? አሁን አይደል እንዴ ከትምህርት ቤት የመጣሽው?›› አሏት አባቷ፡፡ ‹‹የሣይንስ መምህራችን ስለግል ንጽሕና አጠባበቅ ሰው ጠይቃችሁ ፅፋችሁ እንድትመጡ ስላሉን ጎረቤት ሄጄ ሰው ልጠይቅ ነው›› ብላ ፀሀይ መለሰች፡፡

አባቷም እየሳቁ፣ ‹‹ስለግል ንጽሕና አጠባበቅ ለመጠየቅ ሩቅ መሄድ የለብሽም፤ እኔው ልነግርሽ እችላለሁ፡፡ ምክንያቱም የግል ንጽሕናን የመጠበቅን ጥቅም አብዛኛው ሰው አውቆት ሁሉም እንደየአቅሙ በየቤቱ እየተገበረው የሚገኝ ጉዳይ ነው፡፡ እንደምታውቂው የኛ ቤተሰብ አባላትም የተቻለንን ያህል የግል ንጽሕናችንን እየጠበቅን እንገኛለን›› አሏት፡፡ ‹‹እሺ በል ንገረኝ ልፃፍ›› አለች ፀሀይ፡፡

‹‹ልጄ እንደምታይኝ ዛሬ ስራ በዝቶብኛል፤ ቁጭ ብዬ ቃል በቃል ላስፅፍሽ አልችልም፡፡ እናትሽ ከመምጣቷ በፊት ለመክሰስ የሚሆን ነገር ማዘጋጀት አለብኝ፡፡ ባይሆን ስራዬን እየሰራሁ ስለግል ንጽህና ዋና ዋና ነገሮችን እንግርሻለሁ፤ አንቺ ማስታወሻ ያዢና በኋላ በደንብ አቀናብረሽ ጻፊው›› አሏት አባቷ፡፡ ፀሀይም፣ ‹‹እሺ አባዬ በል ጀምርልኝ›› አለች፡፡



‹‹እየውልሽ ልጄ የግል ንጽህና በእለት ተዕለት ኑሯችን ልንተገብረው የሚገባ የሕይወታችን ዋነኛ ተግባር ነው፡፡ ምክንያቱም የግል ንጽህና መጠበቅ ከብዙ በሽታዎች ለመከላከልና ጤንነትን ለመጠበቅ ይረዳል፡፡ በይበልጥ ደግሞ እጃችን ከሌላው የአካላችን ክፍል ከበሽታ አምጪ ተህዋስያን ጋር ግንኙነት ስለሚያደርግ የእጃችንን ንጽህና መጠበቅ በእጅጉ አስፈላጊ ነው፡፡ እንደምታይኝ እኔም ምግባችንን ከማዘጋጀቴ በፊት እጄን በውሃና በሳሙና ሙልጭ አድርጌ እየታጠብኩ ነው›› በማለት ነገሯት፡፡

‹‹ቸኮልክብኝ እኮ አባቴ፤ ለምን ቀስ እያልክ አትነግረኝም?›› አለች፡፡

አባቷም ‹‹ልጄ ፀሀይ ልትለማመጂው ከሚገባሽ ነገር አንዱ የማስታወሻ አያያዝን ነው፡፡ ማስታወሻ የሚያዘው ፈጠን ተብሎና በአጭር በአጭሩ ነው፡፡ ቃል በቃል አይፃፍም፤ ገባሽ ልጄ?››

‹‹እሺ አባቴ እንደዚያ ለማድረግ እሞክራለሁ፤ ቢሆንም አንተም አትፍጠንብኝ›› ስትላቸው አባቷም ‹‹እሺ አንቺም ፈጠን ለማለት ሞክሪ፡፡ ቅድም እንዳልኩሽ፣ የእጃችንን ንጽህና የምንጠብቀው በበርካታ ምክንያቶች ነው፡፡ የዘመናችን አስከፊ ወረርሽኝ የሆነው ኮቪድ-19 ቫይረስ በዋነኝነት የሚተላለፈው በንጽሕና ጉድለት ነው፡፡ በመሆኑም እጅ ቆሻሻ ነገር ሲነካ በሽታ ሊያመጡ በሚችሉ ተህዋስያን ይበከላል፡፡ ስለዚህ ከምግብ በፊትና በኋላ እጃችንን ወዲያውኑ መታጠብ ይገባናል፡፡ ሌላው አስፈላጊ የሆነውና ማንኛውም ሰው እንደልማድ አድርጎ ሊይዘው የሚገባ ጉዳይ ደግሞ ከተፀዳዱ በኋላ እጅን መታጠብ ነው፡፡ አንድ ሰው ከተፀዳዳ በኋላ ካልታጠበ የአንጀት ተስቦና የተቅማጥ በሽታ ሊያመጡ የሚችሉ ተህዋስያንን እንዲሁም እንደ አሜባና ወስፋት የመሳሰሉትን ትሎች ወደ ሌላ ሰው ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡›› ‹‹ቆይ አባቴ አሁን ያልከኝን በማስታወሻዬ ላስፍረው›› ብላ ፃፍ ፃፍ ካደረገች በኋላ ‹‹አሁን መቀጠል ትችላለህ›› አለች፡፡

‹‹ሌላው ጉዳይ የፊት ንጽህና ነው፡፡ ፊታችንን ጧት ብቻ ሳይሆን ማታ ማታም መታጠብ ይገባናል፡፡ እንደዚህ ካደረግን የአፍንጫችንና የዓይናችንን ጤንነት ለመጠበቅ እንችላለን፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ዘወትር ማታ ማታ የእግር መታጠብ ልምድ ሊኖረን ይገባል፡፡ ጫማንም በየጊዜው ማጠብ ወይም ማናፈስ ጠቃሚ ነው፡፡ አሁን ያልኩሽን እስክትፅፊ ስራዬን ላቀላጥፍ›› ብለዋት ትኩረታቸውን ወደ

ምግብ ዝግጅታቸው አደረጉ፡፡

‹‹አባቴ ቶሎ ጨርስልኝና ምግቡን እየተጋገዝን እንሰራዋለን፤ በዚያውም ሙያ ታስተምረኛለህ››

‹‹ካልሽ እሺ! ግን ቸኮልክብኝ ምናምን እያልሽ ጊዜዬን እንዳታባክኝብኝ፤ የእናትሽ መምጫዋ እየደረሰ ነው፡፡››

‹‹ቃል ገብቻለሁ፡፡ ስለግል ንጽህና ቀረ የምትለውን ንገረኝ፡፡››

‹‹የግል ንጽህና ሲባል እነዚህ ብቻ አይደሉም፡፡ ፀጉርንና ጥርስንም በንጽህና መጠበቅን ያካትታል፡፡ ፀጉራችንን በየጊዜው መታጠብና ከተቻለ በቀን ሁለት ውይም ሦስት ጊዜ ማበጠር ጠቃሚ ነው፡፡"

‹‹ጥርስ በንጽህና መጠበቅ ካለባቸው የሰውነት ክፍሎቻችን አንዱ ነው፡፡ የጥርስ ንጽህናን ባለመጠበቅ የጥርስና የድድ በሽታዎች በቀላሉ ይመጣሉ፡፡ በተለይ ስኳርነት ወይም ጣፋጭነት ያላቸው ምግቦች በጥርሶች መሃል በመቀመጥ ለበሽታ ተህዋስያን መራቢያ ይሆናሉ፡፡ ይሁንና የጥርስን ንጽህና መጠበቅ አስቸጋሪ ጉዳይ አይደለም፡፡ ሁልጊዜ ምግብ ከበላን በኋላ አፋችንን በውሐ በመጉመጥመጥ አፋችን ውስጥ ተለጥፎ የቀረውን ምግብ ማስወገድ እንችላለን፡፡ በተጨማሪም ጥርሳችንን በመፋቂያ ወይም በብሩሽ በየቀኑ ማጽዳት ያስፈልጋል፡፡ ይህ ድርጊታችን ዘወትር ከሆነ ከማንኛውም ሰው ጋር ስንነጋገር አፋችን መጥፎ ጠረን ስለማይኖረው አናፍርም፤ አንሸማቀቅም፡፡ ይሁን እንጂ እዚህ ላይ ማስተዋል ያለብን ጉዳይ አንድ ሰው በተጠቀመበት መፋቂያ ወይም ብሩሽ መጠቀም እንደሌለብን ነው፡፡

በተጨማሪም ስናፀዳ ጥርሳችንን ብቻ እንጂ ድዳችንን ፈፅሞ በብሩሽ መንካት አይገባንም ገባሽ ልጄ?"

‹‹አዎ አባቴ ገብቶኛል፤ ስለልብስ ግን አልነገርከኝም፡፡››

‹‹ልክ ነሽ ልጄ፤ የአካል ጽዳት ብቻውን ግማሽ ስራ ነው፡፡ ምክንያቱም የግል

ንጽህና የተሟላ የሚሆነው የልብስ ንጽህና አጠባበቅ ሲታከልበት ነው፡፡ ልብስን በንጽህና መያዝ ለጤና እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ የቆሸሸ ልብስ ለተባዮች መራቢያ የተመቸ ነው፡፡ በዚህም ሳቢያ ወረርሽኝ እና የመሳሰሉ ከባድ የጤና ጠንቆች ሊከሰቱ ይችላሉ፡፡ እነዚህ በሽታዎች ተላላፊ ስለሆኑ በአንድ ሰው ብቻ ተወስነው አይቀሩም፡፡ ችግሩ ከግል ደረጃ አልፎ የሕብረተሰብ ጠንቅ ይሆናል፡፡ የቀንም ሆኑ የሌሊት ልብሶችን በየጊዜው በውሃና በሳሙና ማጠብ ያስፈልጋል፡፡ በተለይም ብርድልብስ፣ አንሶላ፣ ፍራሽ የመሳሰሉትን በየጊዜው ፀሐይ ላይ ማስጣት ያስፈልጋል፡፡ ምክንያቱም የፀሐይ ሙቀት ተባዮችንና የበሽታ አምጪ ተህዋስያንን የመግደል አቅም አለው፡፡››

"አመሰግናለሁ አባቴ፤ ባጠቃላይ የሰውነትንና የልብስን ንጽህና መጠበቅ ከልዩ ልዩ በሽታ ለመከላከል ከመርዳቱም በላይ ፍፁም ንቃትንና መዝናናትን በመስጠት አእምሮን እንደሚያድስ ተረድቻለሁ፡፡ በተጨማሪም እያንዳንዱ ሰው የግል ንጽህናውን የመጠበቅና የመቆጣጠር ልምድ ሊኖረው እንደሚገባ ተገንዝቤያለሁ፡፡"

(ደበበ ኃ/ጊዮርጊስ፤ 2002፤ የአማርኛ መርጃ መጽሐፍ፤ ገጽ 38 — 40 ለግል ንፅህና ማስተማሪያነት ተሻሽሎ የተወሰደ)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር 1

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ ሀሳብ መሰረት ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛ መልስ የያዘውን ሆሄ በመምረጥ መልሱ።**

1. በምንባቡ መሰረት ከሌላው የአካላችን ክፍል ይበልጥ ከበሽታ አምጪ ተህዋስያን ጋር ግንኙነት ያለው የትኛው ነው?

   ሀ. እግር ለ. እጅ ሐ. ጸጉር መ. ገላ

2. በምንባቡ ሀሳብ መሰረት የግል ንጽሕና ውስጥ የማይካተተው የትኛው ነው?

   ሀ. ፊትን መታጠብ ለ. ጥርስን መቦረሽ

   ሐ. ጸጉርን መታጠብ መ. አካባቢን ማጽዳት

3. በምንባቡ ሀሳብ መሰረት የጸሐይ ብርሃን ለምን ይጠቅማል?

   ሀ. ሰውነትን ለመገንባት ለ. ለንጽሕና መጠበቂያ

   ሐ. ብርድን ለመከላከል መ. ኃይል ለማግኘት

4. የጸሐይ አባት ‹‹ቁጭ ብዬ ቃል በቃል ላስጽፍሽ አልችልም›› ያሏት ለምንድን ነው?

   ሀ. ስራ ስለበዛባቸው ለ. ፍላጎት ስለሌላቸው

   ሐ. ሀሳብ ስለሌላቸው መ. ቀስ ብለው ማውራት ስለማይወዱ

5. በጥርሶች መሃል በመቀመጥ ለበሽታ ተህዋስያን መራቢያ በመሆን ከፍተኛ ጉዳት የሚያስከትሉት ምግቦች የትኞቹ ናቸው?

   ሀ. ጣፋጭ ምግቦች ለ. ፍራፍሬ

   ሐ. ጥራጥሬ መ. አትክልት

6. አፋችን መጥፎ ጠረን እንዲኖረው የሚያደርገው ምንድን ነው?

   ሀ. ጥርስን መቦረሽ ለ. ምግብ አለመመገብ

   ሐ. ብዙ ውሃ መጠጣት መ. ጥርሳችንን አለማጽዳት

7. የግል ንጽሕና መጠበቅ ምን ጥቅም አለው?

ሀ. ውፍረት ለመቀነስ
ለ. እድገትን ለማፋጠን
ሐ. በሰዎች ለመወደድ
መ. ጤንነትን ለመጠበቅ

8. ኮቪድ - 19 በዋናነት መተላለፊያ መንገዱ ምንድን ነው?

ሀ. ውሃ አለመጠጣት
ለ. የንጽሕና ጉድለት
ሐ. የምግብ እጥረት
መ. የጸሐይ ብርሃን እጥረት

9. ከመጸዳጃ ቤት ስንመለስ አለመታጠባችን ምን አይነት በሽታ ሊያስከትልብን ይችላል?

ሀ. የአንጀት መታጠፍ
ለ. የአንጀት ተስቦ
መ. የራስ ምታት
መ. ወባ

## ተግባር 2

ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ከምንባቡ ሀሳብ በመነሳት አጭር መልስ ስጡ።

ሀ. የግል ንጽህና መጠበቅ ምን ምን ጠቀሜታዎች እንዳሉት በጥንድ በጥንድ

በመሆን ሀሳባችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

ለ. የምንባቡን አጠቃላይ ሀሳብ ለመምህራችሁ ግለጹ።

## ክፍል ሶስት፡- ቃላት

## ተግባር 1

ለሚከተሉት ቃላት ፍቺ ከሰጣችሁ በኋላ ፍቺዎቻቸውን የሚያመለክቱ ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ።

ሀ. ተስቦ ለ. ወስፋት ሐ. ተባይ

መ. ተህዋስያን ሠ. አሜባ ረ. ጠንቅ

ሰ. ግማሽ ስራ

## ተግባር 2

ቀጥሎ በቀረበው ጽሑፍ ውስጥ ለሚገኙት ክፍት ቦታዎች ከአንቀጹ በላይ ከቀረቡት ቃላት በመምረጥ አሟሏቸው።

ሀ. ቢዳረጉ ሐ. ታማኞች

ለ. መሰረት መ. አፍታ ሠ. በማሳሳታቸው

ታማኝነት የመልካም ግንኙነት_______ ነው። ወዳጆች፣ ቤተሰቦች፣ ጎረቤቶችና ድርጅቶች ለተቃና ስራ መተማመንን ይሻሉ። አንዱ ሌላውን ማመን ከቻለ ማንኛውም ነገር ስኬታማ ይሆናል። ሆኖም ታማኝነት በአንድ _______ የምንፈጥረው ሳይሆን ቀስ በቀስ የምናዳብረው ነው። አንዳንድ ሰዎች ፈጥነው ታማኝነትን ያተርፋሉ። አድራጎታቸውና ባህርያቸው በሌሎች ዘንድ እምነትና

ከበሬታን እንዲያተርፉ ይረዷቸዋል፡፡ ______ ለደንበኞቻቸው፣ ለጓደኞቻቸውም ሆነ ለልጆቻቸው ቃላቸውን ይጠብቃሉ፡፡ የተናገሩትን በተግባር ስለሚፈጽሙት በሌሎች ሰዎች በቀላሉ አመኔታ ያገኛሉ፡፡ ለጉዳት ______________ እንኳን እውነትን ከመናገር አይቆጠቡም፡፡ ስህተት በሚፈፅሙበት ወቅትም ፈጥነው ይቅርታ ይጠይቃሉ፡፡ ሌሎችን ______ ከልብ ያዝናሉ፡፡ በውይይት ጊዜ የመናገር ተራውን እስኪረከቡ ድረስ ያለመታከት የሌላውን ሀሳብ ያዳምጣሉ፡፡ ለሌሎች ልባዊ ምስጋና ያቀርባሉ፡፡ የሌሎችን ጥረት በማስተዋል አድናቆት ይለግሳሉ፡፡

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

### ማስታወሻ

#### ቢጋር መንደፍ

ቢጋር የሚባለው አንድን ጽሑፍ ከመጻፋችን በፊት በጽሑፉ ውስጥ መካተት ያለባቸውን ዋናና ዝርዝር ሀሳቦች በንድፍ መልክ የምናቀርብበት ነው፡፡ ጽሑፍ ከመጻፋችን በፊት ቢጋር ማዘጋጀት በርካታ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ ዋና ዋናዎቹ ጠቀሜታዎቹ

የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የጽሑፉን ዋና እና ዝርዝር ሀሳቦች ለመለየት፣
- ሀሳቦችን በተገቢው ቅደም ተከተል ለማቅረብ፣
- ከጽሑፉ ርዕሰ ጉዳይ ውጭ የሆኑ ሀሳቦችን ላለማካተት፣
- በጽሑፉ መካተት ያለባቸውን ሀሳቦች እንዳንዘነጋ፣

ቢጋርን በተለያዩ ቅርጾች ማዘጋጀት የምንችል ሲሆን ቀጥሎ የቀረበው ምሳሌ አንዱ ነው፡፡

የንጽሕና አጠባበቅ

`

የግል ንጽሕና
- የሰውነት ክፍልን መታጠብ
- ልብስን ማጠብ

የአካባቢ ንጽሕና
- ደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻን በአግባቡ ማስወገድ
- አካባቢን በጋራ መጥረግ
- ቆሻሻን ሰብስቦ መቅበር ወይም ማቃጠል

ንጽሕና በሁለት መንገዶች ሊጠበቅ ይችላል። የመጀመሪያው የግል ንጽሕና አጠባበቅ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የአካባቢ ንጽሕና አጠባበቅ ነው። የግል ንጽሕናን ለመጠበቅ የሰውነት ክፍሎችን (እጅ፣ እግር፣ ጸጉር፣ ፊት፣ ገላ፣ ጥርስ) በሚገባ መታጠብ እንዲሁም ልብስን ማጠብ ያስፈልጋል። የአካባቢን ንጽሕና ለመጠበቅ ደግሞ ደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻዎችን በአግባቡ ማስወገድ፣ አካባቢን በጋራ መጥረግና ቆሻሻን ሰብስቦ መቅበር ወይም ማቃጠል ተገቢ ነው።

## ተግባር 1

**ከሚከተሉት ርዕሶች ውስጥ አንዱን በመምረጥ አንድ አንቀጽ ለመጻፍ የሚያስችል ቢጋር አዘጋጅታሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።**

ሀ. የውሃ ጥቅም ለ. የትምህርት ጥቅም ሐ. የንጽሕና ጥቅም

## ክፍል አምስት፡- ሰዋስው

ማስታወሻ

### ምዕላድ

ምዕላድ የሚባለው ራሱን ችሎ ትርጉም ሊኖረውም ላይኖረውም የሚችልና በጣም ትንሹ የቋንቋ አካል ነው፡፡ ትርጉም ያለው የተባለበት ምክንያት ነጻ ምዕላድ ትርጉም አዘል በመሆኑ ነው፡፡ በጣም ትንሹ የቋንቋ አካል የተባለበት ምክንያት ደግሞ አንድ ምዕላድ ወደ ሌሎች ትንንሽ ትርጉም አዘል አካላት ሊከፈል ባለመቻሉ ነው፡፡

ምሳሌ፡- በጎች የሚለው ቃል ውስጥ ሁለት ምዕላዶች አሉ፡፡ እነሱም፡- /በግ/ እና /-ኦች/ የሚሉት ናቸው፡፡

ቃላት በምዕላድ ሲከፋፈሉ የቋንቋውን ስርአት ጠብቀው መሆን ይገባቸዋል፡፡ ለዚህም በሚከተለው ሰንጠረዥ ውስጥ

የቀረበላችሁን ምሳሌዎች አስተውሉ፡፡

| ተ.ቁ | የተጣመረው ቃል | የተነጣጠለው ቃል |
|---|---|---|
| ሀ | ተማሪዎች | ተማሪ-ዎች |
| ለ | ቤትሽ | ቤት-ሽ |
| ሐ | ነጻነት | ነጻ-ነት |
| መ | ደብዳቤዎች | ደብዳቤ-ዎች |
| ሠ | ተራራማ | ተራራ-ማ |

### ተግባር 1

**ቀጥሎ ተነጣጥለው የቀረቡትን ምእላዶች በማጣመር ቃላት መስርቱ፡፡**

ምሳሌ፡- በቅሎ-ዎች    በቅሎዎች

ሀ. ሚዛን-ህ    ሐ. ጆሮ-ው    ሠ. ቆዳ-ው

ለ. ልጅ-ነት    መ. ትምህርት-ሽ

## ተግባር 2

**የሚከተሉትን ቃላት በትክክለኛው የምእላድ አከፋፈል ነጣጥላችሁ ጻፉ።**

ምሳሌ፡- በሬዎች — በሬ-ዎች

ሀ. ደብተርህ

ለ. አልጋዋ

ሐ. ጨረሰች

መ. ቆንጆዎች

ሠ. ሰፊው

### የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ የተለያዩ የትምህርት ይዘቶችን ተምራችኋል፡፡ ይዘቶቹም ማዳመጥና መናገር፣ ማንበብ፣ ቃላት፣ ጽሕፈትና ሰዋስው ናቸው፡፡

- በማዳመጥ ክፍል ታሪክን ስታዳምጡ ሀሳቡን ለመረዳት ትችሉ ዘንድ ማስታወሻ መያዝ ይጠበቅባችኋል፡፡
- አንድን ጽሑፍ ከመጻፋችን በፊት ጽሑፋችንን የሚመራን ቢጋር ማዘጋጀት አለብን፡፡ ይህም በርካታ ጥቅሞች ሲኖሩት በጽሑፉ ለማስተላለፍ ያሰብነውን ሀሳብ በሚገባ ለማድረስ ያስችለናል፡፡
- አነስተኛው ትርጉም አዘል የቋንቋ ቅንጣት ምዕላድ ሲሆን ራሱን ችሎ ትርጉም ሊኖረውም ላይኖረውም ይችላል፡፡

### የክለሳ ጥያቄዎች

**ለሚከተሉት የክለሳ ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡**

1. አዳምጦ የመረዳት ችሎታን ለማሳደግ የሚጠቅሙ ተግባራትን ዘርዝሩ፡፡
2. የቢጋር ጥቅሞች ምን ምን እንደሆኑ አብራርታችሁ ግለጹ፡፡
3. የንጽሕና መጓደል በሰዎች ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት የሚገልጽ አንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡
4. የሚከተሉትን ቃላት በምእላዶች ከፋፍላችሁ አመልክቱ፡፡

| | |
|---|---|
| ሀ. ቤተሰቦቼ | ለ. ልማዳችን |
| ሐ. ጤናን | መ. አስመጣች |

# አማርኛ

## ፭ኛ ክፍል

# ምዕራፍ ሶስት
# ልማድ

ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች:

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- አንድን ታሪክ አዳምጣችሁ ትተርካላችሁ፡፡
- ተገቢውን ድምጸት ጠብቃችሁ ጽሑፍን ድምጻችሁን ከፍ አድርጋችሁ ታነባላችሁ፡፡
- የአንቀጽ አይነቶችን ትለያላችሁ፡፡
- ለቃላት ዓውዳዊ ፍቺ ትሰጣላችሁ፡፡
- በዓረፍተነገር ውስጥ የሚገኙ ተውሳከ ግሶችን ትለያላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥና መናገር

## ቶክ ቤኣ

### ቅድመ ማዳመጥ

ተግባር 1

**ቀጥሎ የቀረቡት ቃላት መምህራችሁ በሚያነቡላችሁ ምንባብ ላይ የሚገኙ ሲሆኑ ምንባቡን አዳምጣችሁ ለመረዳት ያግዛችሁ ዘንድ ፍቺዎቻቸውን በቃል ግለጹ፡፡**

ሀ. መታያ　　ለ. እንሰስላ　　ሐ. ብረዛ　　መ. ቱባ

ተግባር 2

**የሚከተለውን ጥያቄ በቃል መልሱ፡፡**

በኢትዮጵያ ውስጥ የተለያየ የአዲስ ዓመት በዓል አከባበር ታውቃላችሁ? ካወቃችሁ የት አካባቢና በምን ወር እንደሚከበር ግለጹ፡፡

የማዳመጥ ሒደት

ተግባር፡-

**መምህራችሁ ‹‹ቶክ ቤኣ›› የሚል ርዕስ ያለው ምንባብ ያነቡላችኋል፡፡ ምንባቡን በጥሞና አዳምጡ፡፡**

አዳምጦ መረዳት

ተግባር 1

**ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ትክክለኛ መልስ የያዘውን ሆሄ በመምረጥ በጽሑፍ መልሱ፡፡**

1. የዳውሮ ብሔረሰብ ዘመን አቆጣጠር መሰረት ያደረገው ምንን ነው?

   ሀ. የዝናብ ወራትን　　ለ. የጸሐይ ወራትን

   ሐ. የጨረቃ ወራትን　　መ. የበጋ ወራትን

2. በጥንት ጊዜ የ‹‹ቶክ ቤኣ›› ቀናት የሚባሉት የትኞዎቹ ነበሩ?

ሀ. በመስከረም ወር መጨረሻ

ለ. በመስከረም ወር መጀመሪያ

ሐ. ከመስከረም ወር መጨረሻ እስከ ጥቅምት ወር መጀመሪያ

መ. ከነሀሴ መጨረሻ እስከ መስከረም ጨረቃ መታያ

3. በዳውሮ ብሔረሰብ ዘመን መለወጫ በዓል ላይ ሰፈር ለሰፈር በመዞር ገንዘብ የሚለምኑት እነማን ናቸው?

ሀ. ልጃገረዶች

ለ. ወጣት ወንዶች

ሐ. ያገቡ ሴቶች

መ. አዛውንቶች

4. የዳውሮ ብሔረሰብ በዘመን መለወጫ ዋዜማ ሁሉም ሰው ጠግቦ መብላት እንዳለበት የሚያምኑት ለምንድን ነው?

ሀ. ዓመቱን ሙሉ ጥጋብ እንደሚሆን ስለሚታመን

ለ. በብዛት ድግስ ስለሚዘጋጅ

ሐ. ከተለያዩ አካባቢዎች እንግዶች ስለሚመጡ

መ. በሞት የተለዩ ሰዎችን ለማሰብ

5. በአሁኑ ጊዜ የ‹‹ቶክ ቤኣ›› ቀናት የሚባሉት በምን ወር ላይ ይገኛሉ?

ሀ. በመስከረም መጨረሻ

ለ. በጳጉሜ መጨረሻ

ሐ. በጥቅምት መጀመሪያ

መ. በነሀሴ መጨረሻ

## ተግባር 2

**ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት በቃል መልስ ስጡ፡፡**

ሀ. ያዳመጣችሁት ምንባብ የያዘውን ሀሳብ በአጭሩ ግለጹ፡፡

ለ. በአካባቢያችሁ በዘመን መለወጫ በዓል ላይ ምን ምን ተግባራት እንደሚከናወኑ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

ሐ. በአካባቢያችሁ የሚገኙ ትላልቅ ሰዎችን በመጠየቅ በአንድ አካባቢ ስለሚከበር ባህላዊ የበዓል አከባበር ማስታወሻ ይዛችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ፡፡

## ክፍል ሁለት፡- ንባብ

### ዳጉ



### ቅድመ ንባብ

**ተግባር**

**ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ከአሁን በፊት ከምታውቋቸው ነገሮች በመነሳት በቃል መልሱ፡፡**

ሀ. ስለባህላዊ መረጃ ልውውጥ የምታውቁትን ለመምህራችሁ ግለጹ፡፡

ለ. ሀሰተኛ መረጃ መናገር ወይም መቀበል ምን ጉዳት አለው?

### የንባብ ሒደት፡-

**ተግባር**

**ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ ጥንድ ጥንድ በመሆን ድምጻችሁን እያሰማችሁ አንብቡ፡፡**

# ዳጉ

አቶ ሀሰን ዓሊ ዳጉ ስለሚባለው የአፋር ብሄረሰብ አንድ ልማዳዊ ድርጊት ለትምህርት ቤቱ ማኅበረሰብ ለማብራራት ዘላለም ብርሀን በሚባል ትምህርት ቤት አዳራሽ ተገኝተዋል፡፡ ከተማሪዎች ለቀረቡላቸው ጥያቄዎችም የሚከተሉትን ምላሾች ሰጥተዋል፡፡

**መምህርት ዘሪቱ፡-** <<በቅድሚያ እንኳን ወደ ትምህርት ቤታችን በሰላም መጡ፡፡ በመቀጠልም ስለአፋሮች ባህል ሊያስረዱን ፈቃደኛ ስለሆኑ በትምህርት ቤቱ ማኅበረሰብ ስም አመሰግናለሁ፡፡ ተማሪዎች ከአሁኑ ሰዓት ጀምሮ ዳጉን በተመለከተ ለአቶ ሀሰን ዓሊ ጥያቄዎቻችሁን ማቅረብ ትችላላችሁ፡፡>> በማለት ስርዓቱን አስጀመሩት፡፡

**ተማሪ ፍቃዱ፡-** <<ዳጉ ምን ዓይነት ባህል ነው?>> በማለት ጠየቀ፡፡

**አቶ ሀሰን ፡-** <<ዳጉ በአፋር ብሄረሰብ ውስጥ ህብረተሰቡ መረጃ ለመለዋወጥ የሚጠቀምበት ዘዴ ነው፡፡ መረጃ ልውውጡ ከአንዱ ሰው ወደ ሌላው ሰው በቃል የሚተላለፍ ነው፡፡ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ሰዎች ሲገናኙ ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ የመረጃ ልውውጥ ያደርጋሉ፡፡ አንደኛው ወገን በመንገድ ላይ በቤት ውስጥ ከቤት ውጪ ወዘተ. የተመለከተውንና የሰማውን በሙሉ ይናገራል፡፡ አንድም ሳያስቀር ውሸት ሳይጨምር ያወራል፡፡ ሌላው ቀርቶ አሁን በቴሌቪዥንና በሬድዮ የሠማውንና ያየውን ላላየውና ላልሰማው ሰው ያወራል>> አሉ፡፡

**ተማሪ ሜሮን፡-** <<ዳጉ የሚካሄደው እንዴት ነው?>> ብላ ጠየቀች፡፡

**አቶ ሀሰን፡-** <<ዳጉ የሚከናወነው በመንገድ ላይ በተገናኙ ሰዎች መካከል ነው፡፡ አጭር መረጃ ለመለዋወጥ ከሆነ ከሰላምታ በኋላ ቆም ብለው ይጨዋወታሉ፡፡ ረጅም መረጃ ከሆነ ግን ቁጭ ብለው በሰፊው መረጃ ይለዋወጣሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ከቤት ውጭ ከሆነ ቁጢጥ ብለው፣ በቤት ውስጥ ከሆነ ደግሞ ምንጣፍ ላይ አረፍ ብለው ዳጉ ያደርጋሉ>> በማለት ገለፁ፡፡

**ተማሪ ጀሚላ፡-** <<አፋሮች በዳጉ የሚለዋወጡትን መረጃ ትክክለኛነት እንዴት ያረጋግጣሉ?>> የሚል ጥያቄ ሰነዘረች፡፡

**አቶ ሀሰን፡-** <<የአፋር ሰዎች ዳጉ ሲያደርጉ ውሸት የሚጨምር ሰው የለም ውሸት መናገር እጅጉን በጣም የተከለከለ ነው። ምክንያቱም የሀሰት መረጃ የሌሎችን ሰዎች ስም ሊያጎድፍና ጉዳት ሊያደርስ እንደሚችል የአፋር ሰው ከልጅነቱ ጀምሮ እያወቀ ነው የሚያድገው። አንደኛው ወገን ተሳስቶ እንኳን ሀሰት ቢናገር አነጋገሩ ይታወቅበታል። ከዚህም በላይ ማኅበራዊ ክብሩን ያጣል። ስለዚህ በዳጉ መጀመሪያውኑ የሀሰት መረጃ የሚያሰራጭ የለም>> ብለው መልስ ሰጡ።

**ተማሪ ዚነት፡-** <<አፋሮች በዳጉ መረጃ ሲለዋወጡ የሚደማመጡት እንዴት ነው?>> አለችና ጠየቀች።

**አቶ ሀሰን፡-** <<የመረጃ ልውውጡ የሚካሄደው በሁለት ወገን ነው። ይሁን እንጂ በዳጉ ስነስርዓት መሰረት አንዱ ወገን ተናግሮ ሳይጨርስ አቋርጦ መናገር የተከለከለ ነው። የዳጉ ስነስርዓት ጥሬ መረጃዎችን ተራ በተራ በመቀባበል ላይ የተመሰረተ ስለሆነ አፋሮች በጣም እየተደማመጡ ነው መረጃ የሚለዋወጡት>> በማለት ለተማሪዎቹ መልስ ሰጡ።

**ተማሪ ደረጀ፡-** <<ዳጉ ለአፋሮች ያለው ጠቀሜታ ምንድን ነው?>> ብሎ ጠየቀ።

**አቶ ሀሰን፡-** <<የአፋር ህዝብ በአብዛኛው ከብት በማርባትና ከቦታ ቦታ በመንቀሳቀስ የሚኖር ነው። የህብረተሰቡ አኗኗር ከግጦሽ መሬትና ውሐ ወይም ዝናብ ጋር የተያያዘ ነው። በመሆኑም በዳጉ ስነስርዓት አንዱ ግለሰብ ከየት ተነስቶ የት እንደሚደርስና ለምን እንደሚንቀሳቀስ ለሌላው ይገልጻል። በጉዞው ወቅት ያጋጠሙትን መልካምና መጥፎ ሁኔታዎች እንዲሁም አሁን ወደየት እንደሚካሄድ አብራርቶ ይገልጻል>> አሉና አያይዘውም <<የዳጉ መረጃ ልውውጥ ስርዓት ከግል ምስጢር ውጭ ማንኛውንም መረጃ ለመለዋወጥ ያስችላል።

ከመንግስት ሚዲያ የሚሰራጩ መረጃዎች በፍጥነት በህዝቡ ውስጥ ይሰራጫል። በፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ የሚያጠነጥኑ ወቅታዊ መረጃዎች በቀላሉ ለህዝቡ የሚዳረሱት በዳጉ አማካኝነት ነው። ስለወረርሽኞች፣ ግጭቶች፣ የዝርፊያዎችና ስርቆት ወንጀሎች ወዘተ. ህዝቡ መረጃ የሚያገኘው በዳጉ ነው። ሌላው ቢቀር ስለግለሰቦች ጉዳይ ሳይቀር መረጃ የሚገኘው በዳጉ

ነው>> ብለው አስረዱ፡፡

**መምህርት ዘሪቱ፡-** <<ስለዳጉ ተማሪዎቻችን ላቀረቧቸው ጥያቄዎች በሙሉ ተገቢ ምላሽ ስለሰጡልን አቶ ሀሰንን በድጋሜ አመሰግናለሁ፡፡ በአጠቃላይ ዳጉ የአፋር ህዝብ የመረጃ ማዕከል እንደሆነና በእውነት ላይ ተመስርቶ የሚካሄድ መሆኑን ከዚህም በላይ የብሄረሰቡ የሰላምና መረጋጋት ማረጋገጫ ዋነኛ መሳሪያ ስለመሆኑ ተማሪዎች ግንዛቤ ጨብጠዋል የሚል እምነት አለኝ አይደለም እንዴ ተማሪዎች?>> በማለት ወደ ተማሪዎቹ ሲመለከቱ አዳራሹ በጭብጨባ ተናወጠ፡፡

(ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ብሔራዊ የባህል ማዕከል፤ 2006፤ የአፋር ባህላዊ እሴቶች መጠነኛ መሻሻል ተደርጎበት የተወሰደ)

## አንብቦ መረዳት፡-

### ተግባር 1

**ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ባነበባችሁት ምንባብ መሰረት ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛ መልስ የያዘውን ሆሄ በመምረጥ መልሱ፡፡**

1. በምንባቡ ሀሳብ መሰረት የዳጉ ማህበራዊ ጥቅም ምንድን ነው?
   ሀ. መረጃን መለዋወጥ ለ. የገበያ ስነ ስርዓት ማከናወን
   ሐ. ትምህርት መስጠት መ. ምስጢርን ለማካፈል
2. አፋሮች አጭር መረጃ የሚለዋወጡት እንዴት ነው?
   ሀ. መንገድ ላይ እየተንቀሳቀሱ ለ. በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ
   ሐ. በለቅሶ ስነስርዓት ላይ መ. ከሰላምታ በኋላ ቆም ብለው

3. አፋሮች ረጅም መረጃን የሚለዋወጡት በምን ሁኔታ ነው?

ሀ. ቁጭ ብለው ለ. በሬድዮ

ሐ. በቴሌቭዥን መ. በደብዳቤ

4. በዳጉ የሀሰት መረጃ የተናገረ ሰው ምን ይደርስበታል?

ሀ. ከሀገር እንዲወጣ ይደረጋል ለ. ማህበራዊ ክብሩን ያጣል

ሐ. ማረሚያ ቤት ይገባል መ. የገንዘብ ቅጣት ይጣልበታል

5. የዳጉ የመረጃ ልውውጥ የሚደረገው በስንት ወገኖች መካከል ነው?

ሀ. በሁለት ለ. በሶስት ሐ. በአራት መ. በአምስት

## ተግባር 2

**ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች በቃል መልስ ስጡ፡፡**

ሀ. አቶ ሀሰን በሚኖሩበት አካባቢ ለማህበረሰቡ ያላቸው ኃላፊነት ምን ይመስላችኋል?

ለ. አንድ ሰው መረጃ ሲነግራችሁ እውነትነቱን የምታረጋግጡት በምን መንገድ ነው?

ሐ. በአካባቢያችሁ የሚገኙ የዕድር መረዳጃ ማህበራት መልዕክታቸውን የማስተላለፍ ባህላቸው ምን ይመስላል?

መ. በትምህርት ቤታችሁ የሚገኘው ሚኒሚዲያ ክበብ ምን ምን መረጃዎችን ያቀርብላችኋል?

## ክፍል ሶስት፡- ቃላት

### ተግባር 1፡-

**ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላት በምሳሌው መሰረት በምንባቡ ውስጥ ያላቸውን ዓውዳዊ ፍቺ ጻፉ።**

ምሳሌ፡- መባቻ - መጀመሪያ

ሀ. ስርዓቱን　　ለ. ለመለዋወጥ　　ሐ. ቁጢጥ　　ሰ. የሚያጠነጥኑ

መ. ሊያጎድፍ　　ሠ. የሚጨምር　　ረ. ግጦሽ

### ተግባር 2

**በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸው ቃላት ያላቸውን ዓውዳዊ ፍቺ በምሳሌው መሰረት በጽሑፍ ግለጹ።**

ምሳሌ፡-

ሰላምን ለማረጋገጥ ከልብ መጣር ያስፈልጋል።

ከልብ - ከውስጥ/የምር

ሀ. በኢትዮጵያ ውስጥ በስፋት የሚከበሩ በዓሎች አሉ።

ለ. የወንድሜ ልጅ የቤት ስራዋን ከሰራች በኋላ መራገጥ ትወዳለች።

ሐ. ለሀገር እድገት ጠንካራ የስራ ባህል ሊኖር ይገባል።

መ. የችግር ቀን ፈተና ቶሎ አያልፍም።

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

### ተግባር 1

**ከዚህ በታች የቀረቡት አንቀጾች እያንዳንዳቸው በየትኛው የአንቀጽ አጻጻፍ ስልት እንደተጻፉ ግለጹ፡፡**

ሀ. አንድ ቀን አጎቴ ከብት ከሚያግድበት ሜዳ ቁጭ ብሎ ዋሽንት ይጫወታል፡፡ አጎቴ ደግሞ ጥሎበት ዋሽንት ሲነፋ አይኑን ጨፍኖ ነው፡፡ እንደልማዱ አንድ ቀን ዛፍ ስር ቁጭ ብሎና አይኑን ጨፈን አድርጎ ዋሽንቱን ሲነፋ ቆይቶ አረፍ ሲል ጎኑ አንድ ነገር ኳ ኳ... ቧጠጥ ቧጠጥ አደረገው፡፡ ዞር ብሎ ሲመለከት አህያ የሚያህል ነብር እንደ ደህና ወዳጅ አጠገቡ ጋደም ብሎ ተመለከተ፡፡ ነብሩ በአጎቴ ዋሽንት አነፋፍ እንደተመሰጠ አጎቴ ተረዳ፤ በዚህም ተደስቶ በየቀኑ ነብሩን ባገኘበት ሜዳ እየሄደ ዋሽንቱን መንፋቱን ቀጠለበት፡፡ ነብሩም የአጎቴን መምጫ ሰአት እየጠበቀ በአጎቴ ዋሽንት መመሰጡን ቀጠለ፡፡ ይህ የአጎቴና የነብሩ ወዳጅነት በየቀኑ እያደገ፣ እያደገ፣ እያደገ... መጥቶ በጊዜ ሂደት የሚዋደዱ ጓደኛሞች ሆኑ፡፡

(አሌክስ አብርሃም፤ 2011፤ ዙቤይዳ ፣ ገጽ 158 መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበት የተወሰደ፡፡)

ለ. የደቡብ ሕዝቦች ብሔር ብሔረሰቦች ክልል ከምንኖርባት ምድር በፈጣሪ ልዩ ጸጋ ከታደሉት ምርጥ አካባቢዎች አንዱ ነው፡፡ ክልሉ ከ55 በላይ የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦችን ያቀፈ ሲሆን እንደ ሰንሰለት የተያያዙ በርካታ የስምጥ ሸለቆ ሀይቆችና ፍል ውሃዎች፣ ለቁጥር የሚያታክቱ በርካታ ትላልቅ ወንዞች፣ ጅረቶችና ምንጮች ይገኙበታል፡፡ይህ ክልል ባሉት ፓርኮች በአይነታቸው የተለያዩና በቁጥር በርከት ያሉ የዱር እንስሳት እንዲሁም በዓለም ብርቅዬ የሆኑ የአእዋፍ ዝርያዎችንም አቅፎ ይገኛል፡፡

(ታሪኩ ፋንታዬ፤ 2008፤ አማርኛ ሁሉ ለሁሉ፣ ገጽ 157)

ተግባር 2

**ቀጥሎ ከቀረቡት ርእሰ ጉዳዮች ውስጥ አንዱን በመምረጥ ስለባህል የሚያወሳ አንድ በተራኪ ስልት ወይም በገላጭ ስልት የተስፋፋ አንቀጽ በአጫጭር ዓረፍተ ነገሮች ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።**

ሀ. አውደዓመት ለ. ባህላችን ሐ. ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት

## ክፍል አምስት፡- ሰዋስው

ማስታወሻ

### ተውሳከ ግስ

በግእዝ ‹‹ተውሳክ›› ማለት ጭማሪ ማለት ሲሆን በዚህም መሰረት ‹‹ተውሳከ ግስ›› ማለት የግስ ጭማሪ ማለት ነው። ተውሳከ ግሶች ከግስ ጋር እየገቡ በግሱ የሚገለጸው ድርጊት የት፣ መቼ፣ ለምን፣ በምን ሁኔታ እንደተፈጸመ ይገልጻሉ።

ምሳሌ፡-

ክፉኛ፣ ቶሎ፣ ለምን፣ መቼ፣ እዚህ

ተግባር 1

**በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ተውሳከ ግስ የሆኑትን ቃላት ለይታችሁ ጻፉ።**

ምሳሌ፡- ልጁ ክፉኛ ታሟል። በዚህ ዓረፍተነገር ተውሳከ ግስ የሆነው ቃል ‹‹ክፉኛ›› የሚለው ነው።

ሀ. ካሳ ነገ ይመጣል።

ለ. አስቴር ወዲያው ሄደች።

ሐ. ሰብለ በፍጥነት ተመለሰች።

መ.ታታሪዋ ተማሪ ዘወትር ታጠናለች።

ሠ.መጽሐፉ እዚህ አለ።

ተግባር 2

**የሚከተሉትን ተውሳከ ግሶች በመጠቀም ዓረፍተነገር መስርቱ።**

ምሳሌ፡- ጠዋት

ዳንኤል ጠዋት ተመለሰ።

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. ትናንትና | ለ. ቅድም | ሐ. ቶሎ |
| መ. ዘንድሮ | ሠ. ማታ | ረ. ጥንት |

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ የተለያዩ የትምህርት ይዘቶችን ተምራችኋል፡፡ ይዘቶቹም ማዳመጥና መናገር፣ ማንበብ፣ ቃላት፣ ጽሕፈትና ሰዋስው ናቸው፡፡

- በማዳመጥ ክፍል ያዳመጣችሁትን ታሪክ መተረክን
- በማንበብ ክፍል ምንባብን ድምጽ በማሰማት በተገቢው ድምጸት ማንበብን
- በቃላት ክፍል ቃላት በዓረፍተነገሮች ውስጥ የተለያዩ ዓውዳዊ ፍቺዎች ሊኖሯቸው እንደሚችሉ ተምራችኋል፡፡
- በመጻፍ ክፍል የአንቀጽ ማስፋፊያ ስልቶች ስለሆኑት የትረክጃና የገለጻ ስልት ተምራችኋል፡፡ በዚህም የትረካ ስልት ድርጊቶችንና ሁነቶችን የሚተርክ እንደሆነና ገላጭ ስልት ደግሞ ስለአንድ ነገር ምንነት፣ አሰራር፣ ወዘተ. የሚገልጽ እንደሆነ ተገንዝባችኋል፡፡
- በሰዋስው ክፍል ከቃል ክፍሎች ውስጥ አንዱ የሆነውንና ግስን ከጊዜ፣ ከቦታ፣ ወዘተ. ለመግለጽ የሚያገለግለውን ተውሳከ ግስ በተመለከተ ተምራችኋል፡፡

### የክለሳ ጥያቄዎች

**ለሚከተሉት የክለሳ ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡**

1. የተለያዩ ተውሳከ ግሶችን በመሰብሰብ ያሏቸውን አገልግሎቶች ዓረፍተነገሮችን በመመስረት አመልክቱ፡፡
2. በፈለጋችሁት ርዕሰ ጉዳይ በትረካ ወይም በገለጻ ስልት የተዋቀረ አንድ አንቀጽ በመጻፍ በመጻፍ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡
3. ለቃላት ዓውዳዊ ፍች መስጠትን የሚያመለክቱ ዓረፍተነገሮችን መስርቱ፡፡

# አማርኛ
## ፭ኛ ክፍል

# ምዕራፍ አራት
# የትራፊክ ደህንነት

### ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- ምልልስ አዳምጣችሁ አስፈላጊነቱን ትገልጻላችሁ፡፡
- የተለያዩ የማዳመጥ ስልቶችን ተጠቅማችሁ ለተነበበላችሁ ጽሑፍ ትርጉም ትሰጣላችሁ፡፡
- ማህበራዊ አገላለጾችን ትገልጻላችሁ፡፡
- አንቀጽ አንብባችሁ ጭብጡንና አስፈላጊነቱን ትገልጻላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥና መናገር

### ዋናው መኖር

### ቅድመ ማዳመጥ፡-

ተግባር

**መምህራችሁ የተቀረጸ ድምጽ ያሰሟችኋል፡፡ ድምጹን ከማዳመጣችሁ በፊት ለሚከተሉት ጥያቄዎች በጥንድ በጥንድ ሆናችሁ በመወያየት በቃል መልስ ስጡ፡፡**

ሀ. የትራፊክ ደህንነት የሚለው አገላለጽ ምንን የሚያመለክት ነው?

ለ. የትራፊክ ደህንነትን ማስጠበቅ የማን ኃላፊነት ይመስላችኋል?

### የማዳመጥ ሒደት፡-

ተግባር

**ቀጥሎ መምህራችሁ በድምጽ የተቀረጸ ምንባብ ያሰሟችኋል፡፡ የተከፈተላችሁን ምንባብ በጥሞና አዳምጡ፡፡**

አዳምጦ መረዳት

ተግባር 1

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ትክክለኛ መልስ የያዘውን ሆሄ በመምረጥ በቃል መልሱ፡፡**

1. እግረኛውን ሰውዬ ለአደጋ የዳረገው ምንድን ነው?

ሀ. ባልተፈቀደ መንገድ በማቋረጡ

ለ. አሽከርካሪው በፍጥነት ሲያሽከረክር ስለነበረ

ሐ. ታክሲው ብዙ ተሳፋሪዎችን ይዞ ስለነበረ

መ. በእግሩ በመጓዙ

2. መነን ጓደኛዋ ሰዓዳን ለማረጋጋት ምን አደረገች?

ሀ. ቤተሰቦቿን ጠርታ እንዲያረጋጓት አደረገች

ለ. ከጓደኞቿ ጋር ተነጋግራ ወደ ቤቷ ወሰደቻት

ሐ. እንድትረጋጋ መከረቻት

መ. እረፍት እንድትወስድ አደረገቻት

3. በየመገናኛ ብዙኃኑና በየቤቱ ስለትራፊክ ደህንነት በስፋት መወራቱ ለውጥ ያላመጣው ለምንድን ነው?

ሀ. ብዙ ሰዎች መገናኛ ብዙኃንን ስለማይከታተሉ

ለ. በመገናኛ ብዙኃን የሚሰጠው ሽፋን አነስተኛ በመሆኑ

ሐ. ሰዎች የአመለካከት ለውጥ ባለማምጣታቸው

መ. የትራፊክ ደህንነት ባለሙያዎች ስራቸውን በአግባቡ ስለማይሰሩ

4. እንድሪስ፣ አለማየሁና ሰዓዳ ሲናገሩ በጥሞና ሲያዳምጥ ቆይቶ፣ የራሱን ሀሳብ ማቅረቡ ምን ያስተምራል?

ሀ. የሌሎችን ሀሳብ መቃወም ተገቢ አለመሆኑን

ለ. ተራን ጠብቆ መናገር ተገቢ እንደሆነ

ሐ. መጨረሻ መናገር እንደሚገባ

መ. ሳያስፈቅዱ መናገር ተገቢ እንደሆነ

## ተግባር 2

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች ያደመጣችሁትን ምንባብ መሰረት በማድረግ በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ የደረሳችሁበትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።**

ሀ. ሰዓዳ ወደቤቷ በታክሲ የምትመለስ ይመስላችኋል? ለምን?


ለ. የቆመ መኪና ከለላ በማድረግ መንገድ የሚያቋርጥ ሰው ብትመለከቱ ምን ታደርጋላችሁ?

ሐ. ተማሪዎች በጥናት ጊዜያቸው ከትምህርት በተጨማሪ በምን በምን ጉዳዮች ዙሪያ ሊያወሩ ይችላሉ?

መ. በትምህርት ቤታችሁ የትራፊክ ደህንነት ክበብ አባላትን በማነጋገር ስለትራፊክ አደጋ የሚሰጧችሁን ማብራሪያ በክፍል ውስጥ በቃል አቅርቡ፡፡

## ክፍል ሁለት፡- ንባብ

### የትራፊክ አደጋ



**ቅድመ ንባብ፡-**

ተግባር

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃል መልስ ስጡ፡፡**

ሀ. በአካባቢያችሁ የትራፊክ አደጋ ተፈጥሮ ያውቃል? ከተፈጠረ አደጋው ምን ጉዳት እንዳደረሰ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለጹ፡፡

ለ. ከምንባቡ ርዕስ እና ከታች ከቀረበው ስዕል በመነሳት ምንባቡ ስለምን ጉዳይ እንደሚያወሳ ግለጹ፡፡

## የትራፊክ አደጋ

ዓለምን ስጋት ላይ ከጣሉ አበይት አጀንዳዎች አንዱ የመንገድ ላይ የትራፊክ አደጋ ነው፡፡ በዓለማችን በመንገድ ትራፊክ አደጋ ምክንያት በየ24 ሴኮንድ የአንድ ሰው ሕይወት ያልፋል፡፡ በየዓመቱ 1.3 ሚሊዮን በላይ ሰዎች ሕይወታቸውን ያጣሉ፡፡ ወደ 50 ሚሊዮን የሚጠጉ በአደጋው ምክንያት አካል ጉዳተኛ ይሆናሉ፡፡ አደጋው እያጠቃ የሚገኘው ከ5 እስከ 29 ዓመት የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎችን መሆኑን የዓለም ጤና ድርጅት መረጃ ያመለክታል፡፡

በአዲስ አበባ በ2011 ዓ.ም 458 የሞት፣ 1,926 ከባድ የአካል ጉዳት እና 1,143 ቀላል የአካል ጉዳት አደጋዎች ተመዝግበዋል፡፡ እንዲሁም በ2012 ዓ.ም 448 የሞት፣ 1,873 ከባድ የአካል ጉዳት እና 938 ቀላል የአካል ጉዳት አደጋዎች ደርሰዋል፡፡ በሌላ በኩል የ2013 ዓ.ም የ9 ወሩን የአደጋ ሁኔታ ብንመለከት 287 የሞት አደጋዎች ሲመዘገቡ 1,343 ከባድ የአካል ጉዳት እና 757 ቀላል የአካል ጉዳቶች ተመዝግበዋል፡፡ በ9 ወሩ 21,234 የንብረት ጉዳቶች ተከስተዋል፡፡

ጊዜና ቦታ እድሜና ጾታ ሳይለይ ዘወትር የሰው ልጆችን ሕይወት እየቀጠፈ እና አካል እያጎደለ የሚገኘውን የመንገድ ላይ የትራፊክ አደጋ ለመከላከልና ለመቀነስ ዘርፈ ብዙ ስራዎች በባለድርሻ አካላት እየተሰሩ ይገኛሉ፡፡ ይሁን እንጂ ይህንን ስራ ህብረተሰቡ ካልደገፈው አደጋው ይቀንሳል ተብሎ አይጠበቅም፡፡

በከተሞች አካባቢ ያለው የአሽከርካሪዎችና የእግረኞች የመንገድ አጠቃቀም የተስተካከለ አለመሆን ለአደጋው መባባስ እንደ ምክንያት ሊታይ ይችላል፡፡ አሁን አሁን በብዙዎች ዘንድ እንደሚገለጸው የአንዳንድ አሽከርካሪዎች ባህሪ አስቸጋሪ መሆንና የእግረኞች ቸልተኛነት ብዙ መስዋዕትነትን እያስከፈለ ይገኛል፡፡

(አዲስ ፖሊስ መጽሔት ቁጥር 10፤ ሰኔ 2013፤ ገጽ 8 በመጠኑ ተሻሽሎ የተወሰደ)

## አንብቦ መረዳት፡-

### ተግባር 1

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ ሀሳብ መሰረት "እውነት" ወይም "ሀሰት" በማለት በቃል መልሱ፡፡**

1. የመንገድ ትራፊክ አደጋ እያጠቃ የሚገኘው ከ30 ዓመት በላይ ያሉ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ነው፡፡
2. በአዲስ አበባ በ2011 ዓ.ም በትራፊክ አደጋ የተመዘገበው የሞት አደጋ ከ2012 ዓ.ም የበለጠ ነው፡፡
3. በ2012 ዓ.ም የተመዘገበው ከባድ የአካል ጉዳት በ2011 ዓ.ም ከተመዘገበው ያነሰ ነው፡፡
4. በከተሞች አካባቢ ለትራፊክ አደጋ መባባስ ዋነኛው ምክንያት የአሽከርካዎችና የእግረኞች መንገድ አጠቃቀም የተስተካከለ መሆኑ ነው፡፡
5. የትራፊክ አደጋን ለመቀነስ የሕብረተሰቡ ድጋፍ አስፈላጊነቱ አናሳ ነው፡፡

### ተግባር 2

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጡ፡፡**

ሀ. አንድ አይነ ስውር ልጅ ለእግረኛ ባልተፈቀደ መንገድ ሲያቋርጥ ብትመለከቱ ምን ታደርጋላችሁ?

ለ. ያነበባችሁትን ምንባብ ዋና ሀሳብ አሳጥራችሁ በጽሑፍ ግለጹ፡፡

## ክፍል ሶስት፡- ቃላት

### ተግባር 1

**የሚከተሉት ቃላት ያላቸውን ፍቺ ከመዝገበ ቃላት ፈልጋችሁ በመጻፍ ፍቺዎቻቸውን የሚያመለክቱ ዓረፍተ ነገሮች ስሩባቸው፡፡**

ምሳሌ፡-

ብርታት - ጥንካሬ

የተመጣጠነ ምግብ መመገብ ለአካል ጥንካሬ ይጠቅማል፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. ስጋት | ለ. መስዋዕትነት | ሠ. አሉታዊ |
| ሐ. መቅጠፍ | መ. ዘርፈ ብዙ | ረ. አጸፋ |

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት


### ተግባር 1

**ቀጥሎ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 5 የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች በትክክለኛው ቅደም ተከተል በማስቀመጥ የተሟላ መልዕክት ያለው አንቀጽ ጻፉ፡፡**

1. ይህም የሚመረጠው ከፊት ለፊት የሚመጣን መኪና ለመመልከት ነው፡፡
2. የእግረኛ መንገድ ከሌለ ሌላው አማራጭ የመንገዱን ግራ ጠርዝ ይዞ መጓዝ ተገቢ ነው፡፡
3. በአጠቃላይ ሰዎች የመንገድ አጠቃቀማቸውን በማሻሻል ከትራፊክ አደጋ መጠበቅ ይችላሉ፡፡
4. የመጀመሪያው ጥንቃቄ ለእግረኛ የተዘጋጀ መንገድ ካለ በዚያ መጠቀም ነው፡፡
5. ሰዎች በመንገድ ላይ ሲጓዙ የእግረኛ መንገድ አጠቃቀም መመሪያዎችን መተግበር አለባቸው፡፡

## ተግባር 2

**ቀጥሎ ያለውን ቢጋር በመጠቀም በገላጭ የአንቀፅ ማስፋፊያ ስልት በመጠቀም አንድ አንቀፅ ፅፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።**




## ክፍል አምስት፡- ሰዋስው

**ማስታወሻ**

**የሁኔታ ተውሳከ ግስ**

በምዕራፍ 3 እንደተማራችሁት ተውሳከ ግስ ግስን ከቦታ፣ ከሁኔታ፣ ከጊዜ ወዘተ. አንጻር የሚገልጽ ነው። በዚህ ምእራፍ ደግሞ ከተውሳከ ግስ አይነቶች አንዱ ስለሆነው የሁኔታ ተውሳከ ግስ ትማራላችሁ።

የሁኔታ ተውሳከ ግስ አንድ ድርጊት የተፈጸመበትን ሁኔታ ለመግለጽ የሚያገለግል የተውሳከ ግስ አይነት ነው። ይህ የተውሳከ ግስ አይነት ድርጊቱ በምን ያህል ደረጃ እንደተፈጸመ ያመለክታል።

ምሳሌ፡-

- አየለ ከሄደበት በፍጥነት ተመለሰ። በዚህ ዓረፍተነገር ውስጥ ‹‹በፍጥነት›› የሚለው ተውሳከ ግስ አየለ የተመለሰበትን ሁኔታ ስለሚያመለክት የሁኔታ ተውሳከ ግስ ነው።
- ሰአዳ በወንድሟ ሞት ክፉኛ ተጎዳች። በዚህ ዓረፍተነገር ውስጥ ‹‹ክፉኛ›› የሚለው ተውሳከ ግስ ሰአዳ የተጎዳችበትን ደረጃ ስለሚያመለክት የሁኔታ ተውሳከ ግስ ነው።

## ተግባር 1

**ቀጥሎ በ‹‹ሀ›› ስር ለቀረቡት ሀረጎች በ‹‹ለ›› ስር ከቀረቡት የሚስማሟቸውን በመምረጥ ዓረፍተነገሮቹን አሟሏቸው።**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. አቢጊያ ከዘመዶቿ ቤት | ሀ. በፍጥነት ተመለሰ |
| 2. ማርታ ወደ ትምህርት ቤት | ለ. ክፉኛ ተጎዳ |
| 3. ሰይድ በመውደቁ | ሐ. እየሮጠች ሄደች |
| 4. አቤል ከገበያ | መ. አምርራ ተቆጣችው |
| 5. ሳሊሀ ወንድሟን | ሠ. በድንገት መጣች |

## ተግባር 2

**በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የሚገኙትን የሁኔታ ተውሳከ ግሶች አውጥታችሁ የሁኔታ ተውሳከ ግስ የተባሉበትን ምክንያቶች አብራርታችሁ በመጻፍ መልሱ።**

ሀ. ትህትና ተንደርድራ ዘለለች።

ለ. መሀመድ በድንገት ወጣ።

ሐ. ሄኖክ እየሮጠ ሄደ።

መ. ረሂማ በቁጣ ተናገረች።

ሠ. ልዑል አምርሮ አለቀሰ።

## ተግባር 3

**ሁኔታን የሚገልጹ አምስት ተውሳከ ግሶችን ፈልጋችሁ በደብተራችሁ ላይ በመጻፍ ሁኔታዎችን የሚገልጹ ዓረፍተነገሮችን መስርቱባቸው።**

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ የተለያዩ የትምህርት ይዘቶችን ተምራችኋል፡፡ ይዘቶቹም ማዳመጥና መናገር፣ ማንበብ፣ ቃላት፣ ጽሕፈትና ሰዋስው ናቸው፡፡

- አንድን ምንባብ ስናዳምጥ ትኩረት ሰጥተን ማዳመጥ ተገቢ ሲሆን ላዳመጥነው መልእክት ትርጉም መስጠትም ተገቢ ነው፡፡
- በማንበብ ሒደት ውስጥ ለሚነበበው ጽሑፍ ትርጉም መስጠት ተገቢ ነው
- መዝገበ ቃላዊ ፍቺ ቃላት በቀጥታ ያላቸውን ፍቺ ያመለክታል፡፡
- የነገሮችንና ሁነቶችን ምንነት፣ አሰራር፣ ወዘተ. ለመግለጽ የሚያገለግለንን አንቀጽ በገላጭ የአጻጻፍ ስልት መጻፍ እንችላለን፡፡
- አንድ ድርጊት የተፈጸመበትን ደረጃ የሚያመለክት ቃል የሁኔታ ተውሳከ ግስ ይባላል፡፡

### የክለሳ ጥያቄዎች

**ለሚከተሉት የክለሳ ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡**

1. ከተለያዩ መጻሕፍት አንቀጾችን በማንበብ ሀሳቡን ለመገንዘብ ሞክሩ፤

   መገንዘባችሁንም የተለያዩ ዘዴዎችን ተጠቅማችሁ አረጋግጡ፡፡

2. ከሚከተሉት መንደርደሪያ ርዕሶች አንዱን በመምረጥ ገላጭ ድርሰት ጻፉ፡፡

   ሀ. የቡና አፈላል ሂደት ለ. የትምህርት ጠቀሜታ ሐ. የሀገር ፍቅር

3. የተለያዩ የሁኔታ ተውሳከ ግሶችን በመፈለግ ዓረፍተነገር መስርቱባቸው፡፡

# አማርኛ

## ፩ኛ ክፍል

# ምዕራፍ አምስት

# የአካባቢ ጥበቃ

ከምዕራፉ የሚጠበቅ ውጤት

ይህንን ምዕራፍ ተምራችሁ ከጨረሳችሁ በኋላ፡-

- የቀደመ እውቀታችሁን ከአሁኑ ጋር ታዛምዳላችሁ
- በጽሑፍ ውስጥ የቀለም መለያ ምልክቶችን ትጠቀማላችሁ።

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥና መናገር

# ብርቱዋ እናት



ቅድመ ማዳማጥ:-

ተግባር

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃላችሁ አጭር መልስ ስጡ፡፡**

ሀ. ከላይ የቀረበውን ስዕል በመመልከት ‹‹ብርቱዋ እናት›› በሚለው ርዕስ ስር ምን ምን ሀሳቦች ሊነሱ እንደሚችሉ ግምታችሁን ለመምህራችሁ ግለጹ፡፡

ለ. በአካባቢያችሁ በመኖሪያ ግቢያቸው ውስጥ እጽዋትን የሚያለሙ ሰዎችን ታውቃላችሁ? ምን ምን እጽዋትን ያለማሉ?

## የማዳመጥ ሒደት

ቀጥሎ ባለው ሰንጠረዥ የቀረቡትን ቃላትና ሀረጋት መምህራችሁ በሚያነቡላችሁ ምንባብ ውስጥ የሚገኙ ሲሆኑ ምንባቡን በማዳመጥ ላይ እያላችሁ መምህራችሁ በመሀል ማንበባቸውን በማቆም ፍቺ እንድትሰጧቸሁ ይጠይቋችኋል፤ እናንተም ለቃላቱ ፍቺ ስጧቸው፡፡

| ቃል | ፍቺ |
|---|---|
| ደፋ ቀና | |
| አርዓያነት | |
| ተቆጨ | |
| ተቋደሰ | |
| አጸፋ | |
| ይደጉማሉ | |

### አዳምጦ መረዳት:-

### ተግባር 1

**በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ የደረሳችሁበትን ሀሳብ በተወካያችሁ አማካኝነት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡**

ሀ. ‹‹ልጆቻችን በእድላቸው ይደጉ›› የሚለው አባባል የሚያስተላልፈው መልእክት ምንድን ነው?

ለ. የሰፈሩ ሰዎች ወይዘሮ አስካለን ‹‹እነዚህን የፍራፍሬ ዛፎች የሚተክሉት ለምንድን ነው?›› ብለው መጠየቃቸው ተገቢ ነው? ለምን?

ሐ. አንድን ሰው ብርቱ የሚያሰኙት ተግባራት ምን ምን ናቸው ብላችሁ ታስባላችሁ?

መ. ያዳመጣችሁትን ታሪክ በአጭሩ ግለጹ፡፡

ሠ. ከወይዘሮ አስካለ ተግባር ምን ተማራችሁ?

## ተግባር 2

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛ መልስ የያዘውን ሆሄ በመምረጥ በጽሑፍ መልሱ።**

1. ወይዘሮ አስካለ የሚኖሩበት ቤት የተሰራው ከምንድን ነው?

ሀ. ከእንጨት ለ. ከቆርቆሮ ሐ. ከብሎኬት መ. ከሳር

2. ወይዘሮ አስካለ ብዙውን ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት የት ነው?

ሀ. ከቤታቸው አካባቢ ባለው የአትክልት ቦታ

ለ. ቀበሌ አካባቢ ባለ የአትክልት ቦታ

ሐ. በመንግስት መስሪያ ቤት

መ. ብዙ እጽዋት በሚገኙበት መዝናኛ

3. ወይዘሮ አስካለ እንደ ጎመን፣ ቃሪያ፣ ቲማቲም የመሳሰሉትን የእለት የምግብ ፍጆታቸውን የሚያገኙት ከየት ነው?

ሀ. ከገበያ ለ. ከገጠር ቤተሰቦቻቸው

ሐ. ከግቢያቸው ውስጥ አልምተው መ. ከጎረቤት ተበድረው

4. ወይዘሮ አስካለ ቀድመው ከሚሰሩበት የመንግስት መስሪያ ቤት በምን ምክንያት ወጡ?

ሀ. በጡረታ ተገልለው ለ. ከአለቃቸው ጋር ተጋጭተው

ሐ. ረፍት ፈልገው መ. በህመም ምክንያት

5. ወይዘሮ አስካለን የሰፈሩ ሰዎች ምን ብለው ይጠሯቸዋል?

ሀ. ጀግናዋ እናት ለ. የድሃዎች እናት

ሐ. የዛፎች እናት መ. ብርቱዋ እናት

ክፍል ሁለት፡- ንባብ

# ዓሳ መገራ ፓርክ



## ቅድመ ንባብ

### ተግባር 1

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።**

ሀ. ዓሳ መገራ የሚባለው ቦታ በሀገራችን የትኛው አካባቢ የሚገኝ ይመስላችኋል?

ለ. በኢትዮጵያ ምን ምን የሚባሉ ፓርኮች አሉ?

ሐ. ከላይ ያለው ስዕል ዓሳ መገራ ብሔራዊ ፓርክ ምን አይነት ገጽታ እንዳለው ያመለክታል?

የንባብ ሒደት፡-

## ተግባር

የሚከተለውን ምንባብ በየግላችሁ በለሆሳስ አንብቡ፡፡

### ጓሳ መገራ ፓርክ

ጓሳ መገራ ከአዲስ አበባ 288 ኪ.ሜ ርቀት ላይ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በሰሜን ሸዋ ዞን በመንዝና ጌራ ምድር ወረዳ ውስጥ የሚገኝ ለዘመናት በኅበረተሰቡ ሲጠበቅ የኖረ የተራራ ሥነ-ምሕዳር ያለው ስፍራ ነው፡፡ ይህ ስፈራ፡-

‹‹አገሯ ጓሳ መገራ አገሯ ጓሳ መገራ፣
ምነው አልሰማ አለች ብጣራ ብጣራ፡፡››

ተብሎ የተዘፈነለት አካባቢ ነው፡፡ የዘፈኑ መልዕክትም መንዜዎች ኩሩ ስለሆኑ የምትወዳትን ልጅ ጠርተሃት የምትመጣልህ አይደለችም፤ ሄደህ ደጅ ጠንተህም በተሳካልህ የሚል ይመስላል፡፡

አጠቃላይ የፓርኩ ስፋት 10,000 ሄክታር አካባቢ ሲሆን ከፍታው ከባህር ጠለል በላይ ከ3,200 እስከ 3,600 ሜትር ነው፡፡ አካባቢው ጓሳ በሚባል ሳር በተፈጥሮ የተሸፈነ በመሆኑ መሬቱ ሲረግጡት እንደ ስፖንጅ ይመቻል፡፡ የሳሩ ባህርይ በዓመት ከ1,400 ሚ.ሜ በላይ የሚዘንበውን ዝናብ ወደ ውስጥ በማስረግና እንደስፖንጅ መጥጦ ይይዘዋል፡፡ በዚህም የተነሳ ከአካባቢው እርጥበት እንዳይጠፋ ከማድረጉም በላይ እንደይፋትና ሸዋሮቢት ባሉት የአካባቢው ዝቅተኛ ቦታዎች አመቱን በሙሉ የማያቋርጥ የምንጭና ወንዞች ፍሰት እንዲኖር ያደርጋል፡፡ ከተሜዎች በቤታቸው ጣራ ላይ የውሃ ማጠራቀሚያ ጋን ሰቅለው የቧንቧ ውሃ በሚኖርበት ሰዓት ሞልተው የቧንቧው ውሃ ሲቋረጥ የጋኑን ውሃ ይጠቀሙበታል፡፡ ጓሳ መገራም ተራራ ላይ ያለ ተፈጥሯዊ የውሃ ጋን ነው፡፡ መንዞች ለዘመናት ይህንን ምስጢር ስለሚያውቁ ጓሳውን ጠብቀውና ተንከባክበው እስከአሁን አቆይተውታል፡፡ ሌሎች እንደዚህ ዓይነት ሥነ ምሕዳሮች ያላቸው እንደ ጉና ተራራ፣ የባሌ ተራሮችና ራስ ዳሽን የመሳሰሉትን ስፍራዎች የየአካባቢው ማሕበረሰብ ጥበቃና እንክብካቤ ያደርግላቸዋል፡፡ ይህ ባይሆን ኖሮ አካባቢውም እንዳለ በረሃማ ይሆን ነበር፡፡

ምክንያቱም ያለ ጉና ተራራ ጣና ሐይቅን ማሰብ፣ ያለ ጣና ደግሞ አባይን ማሰብ አይቻልም፡፡







በጓሳ ፓርክ የበርካታ ብዝኀ ሕይወት መገኛ ከዕፅዋት መካከል በተጠንቀቅ የቆሙ የቤተመንግስት የክብር ዘቦችን የሚመስለው ጅብራ በብዛት የሚገኝ ሲሆን እንስሳት ደግሞ በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙት ብርቅዬዎቹ ቀይ ቀበሮዎችና ጭላዳ ዝንጀሮዎች እንዲሁም ታይተው የማይጠገቡ በርካታ አዕዋፍ ይኖሩበታል፡፡

አካባቢው ሰላምና ፀጥታ የሰፈነበት ስለሆነ ጓሳውን ነፋስ ሲያስተኛውና ሲያቃናው ከሚፈጠረው ለስላሳ ፉጨት፣ አልፎ አልፎ ከሚሰማው የዝንጀሮዎችና የአዕዋፍ እንዲሁም ወደማታና ሌሊት ከሚሰማው የቀበሮዎች ጩኸት በስተቀር ሌላ ድምፅ ስለማይሰማ የሚረብሽ ነገር በአካባቢው የለም፡፡ በከተማ ውዥንብር፣ ውካታና ግርግር የሰለቸው ሰው መንፈሱን ሰላምና እፎይታ ለመመገብ ጓሳ ፓርክ ተመራጭ ቦታ ነው፡፡

(ዓለማየሁ ዋሴ፤ እመጓ፤ 2008 ዓ.ም፣ ገጽ 145-149 በመጠኑ ተሻሽሎ የተወሰደ)

## አንብቦ መረዳት፡-

### ተግባር 1

**ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ባነበባችሁት ምንባብ መሰረት ትክክለኛ መልስ የያዘውን ሆሄ በመምረጥ በጽሑፍ መልሱ፡፡**

1. በጓሳ መገራ ፓርክ የሚገኘውና የቤተ-መንግስት የክብር ዘቦችን የሚመስለው ተክል ምን ይባላል?

   ሀ. ጽድ　　ለ. ጅብራ　　ሐ. ዋንዛ　　መ. ጓሳ

2. ከሚከተሉት የዱር እንስሳት ውስጥ በጓሳ መገራ ፓርክ የሚገኘው የትኛው ነው?

   ሀ. ቀጭኔ　　ለ. ዝሆን　　ሐ. ቀይ ቀበሮ　　መ. አንበሳ

3. በፓርኩ አልፎ አልፎ የቀበሮ ጩኸት የሚሰማው መቼ ነው?

   ሀ. በማታ　　ለ. በቀን　　ሐ. በበጋ　　መ. በክረምት

4. የጣና ሐይቅ የውሃ ምንጭ የሆነው ተራራ የትኛው ነው?

   ሀ. ራስ ዳሽን　　ለ. ባሌ　　ሐ. ጉና　　መ. ቱሉ ዲምቱ

5. የአባይ ወንዝ ከፍተኛውን የውሃ ምንጭ የሚያገኘው ከየት ነው?

   ሀ. ከጣና ሐይቅ　　ለ. ከጉና ተራራ

   ሐ. ከራስ ዳሽን ተራራ　　መ. ከጎርጎራ

6. በፓርኩ ለስላሳ ፉጨት የሚፈጠረው በምን ምክንያት ነው?

   ሀ. ወጣቶች ሲዘፍኑ　　ለ. ቀበሮዎች ሲጮሁ

   ሐ. ዝንጀሮዎች ሲጣሉ　　መ. ጓሳውን ነፋስ ሲያንቀሳቅሰው


7. የጓሳ መገራ ፓርክ ምን አይነት አካባቢ ነው?

   ሀ. ጫጫታ የበዛበት　　ለ. ከብቶች የሚውሉበት

   ሐ. ወጣቶች የሚጫወቱበት　　መ. ጸጥታ የሰፈነበት

## ተግባር 2

ሀ. የተሰጣችሁን ምሳሌ መሰረት በማድረግ ቀጥሎ የቀረበውን ቢጋር አሟልታችሁ ጻፉ፡፡




ለ. ከላይ ያነበባችሁት ምንባብ ስንት አንቀጾች አሉት?

ሐ. ‹‹… ያለ ጉና ተራራ ጣና ሀይቅን ማሰብ ያለ ጣና ደግሞ አባይን ማሰብ አይቻልም›› የሚለውን ሀሳብ በራሳችሁ አገላለጽ ጻፉ፡፡

መ. የምንባቡ የመጨረሻ አንቀጽ የያዘውን ሀሳብ በአጭሩ ግለጹ፡፡

ሠ. የምንባቡን ዋና ሀሳብ በአጭሩ ጽፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ

## ክፍል ሶስት፡- ቃላት

ማስታወሻ

### ቃላትን መነጠልና ማጣመር

ቃላትን መነጠልና ማጣመር፡- ውስብስብ የሆኑ ቃላትንና ሐረጋትን በትክክል የምናነብበት ስልት ሲሆን አቀላጥፈን ለማንበብ ትልቅ ሚና አለው፡፡

መነጠል፡- ውስብስብ ቃላትንና ሐረጋትን ለመነጣጠል የምናነብበት ዘዴ ነው፡፡

ማጣመር፡- ተነጣጥለው የቀረቡ ልዩ ልዩ የቃላትና የሐረጋት ክፍሎችን በማጣመር ማንበብ ነው፡፡

ምሳሌ፡-

| | ነጣጥሎ ማንበብ | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|---|
| ሀ | በ-ባህል-ኣዊ | በባህላዊ |
| ለ | ለ-ባለ-ጉዳይ-ኣችን | ለባለጉዳያችን |
| ሐ | በ-መጨረሻ-ም | በመጨረሻም |
| መ | ዝንጀሮ-ዎች | ዝንጀሮዎች |

### ተግባር 1

**የሚከተሉትን ቃላት አጣምራችሁ በመጻፍ አንብቡ፡፡**

ሀ. ግድብ-ኣችን     ለ. የም-ት-መጣ-በት

ሐ. በ-ተሳካ-ልህ     መ. የ-ምንጭ-ና

### ተግባር 2

**የሚከተሉትን ቃላት ነጣጥላችሁ በደብተራችሁ ላይ በመጻፍ አንብቡ፡፡**

ሀ. አስመጣች     ለ. የጎደለው

ሐ. የስነ ምግባር     መ. ተሰብሳቢዎች

## ተግባር 3

**ቀጥሎ በሚገኘው ሰንጠረዥ ውስጥ ቀደም ሲል ካነበባችሁት ምንባብ የወጡ ሲሆን በአግድም የቀረቡትን ቃላትና ሐረጋት በቁልቁል ከቀረቡት ፍቺዎቻቸው ጋር የሚስማሟቸውን በመምረጥ የ‹‹√›› ምልክት እያደረጋችሁ አዛምዱ፡፡**

| የቃላት/ሀረጋት ፍቺ | ቃላት/ሐረጋት | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ደጅ ጠና | አሰረገ | ብዝሀ ሕይወት | ጋን | ኩሩ | የባህር ጠለል | ስነ ምህዳር | ጓሳ | መጠጠ |
| የፈሳሽ መጠራቀሚያ ዕቃ | | | | | | | | | |
| በአንድ ላይ የሚገኙ ልዩ ልዩ ፍጥረታት | | | | | | | | | |
| የሳር ዓይነት | | | | | | | | | |
| ወደ ውስጥ አስገባ | | | | | | | | | |
| የቦታ ከፍታ መነሻ | | | | | | | | | |
| ፈሳሽ ነገር ቋጥሮ ያዘ | | | | | | | | | |
| ተለማመጠ | | | | | | | | | |
| የቦታ አቀማመጥና የአየር ሁኔታ | | | | | | | | | |

## ተግባር 4

**ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላት መዝገበ ቃላዊ ፍቺ ስጡ፡፡**

ሀ) ዘብ

ለ) ቃና

ሐ) ስነምግባር

መ) ውዥንብር

ሠ) ምንጭ

## ክፍል አራት፦ ጽሕፈት

### ተግባር 1

**በምዕራፍ አንድ ስለአንቀጽና የአንቀጽ ተዋቃሪዎች የተማራችሁትን መሰረት በማድረግ ቀጥሎ በቀረበው አንቀጽ ላይ የሚገኘውን ኃይለ ቃል አውጡ፤ ኃይለ ቃል የተባለበትን ምክንያትም ግለጹ።**

ኢትዮጵያ የብዙ እምቅ ባህላዊ እሴቶች ባለቤት ናት። ከባህላዊ እሴቶቿ መካከል ሀዘን፣ ደስታ፣ ባህላዊ ጨዋታ እና የዳኝነት ስርዓቶች ለአብነት ተጠቃሾች ናቸው። እነዚህ ባህላዊ ክንዋኔዎች የሚገለጹበት መንገድ ደግሞ እንደየአካባቢው ወግና ልማድ የተለያየ ነው። እሴቶቹ የሚለያዩበት ምክንያትም በአንድ አካባቢ የሚኖር ሕዝብ ካዳበረው የሕይወት ልምዱ የሚመነጩ በመሆናቸው ነው።

### ተግባር 2

**ከሚከተሉት መንደርደሪያ ዓረፍተነገሮች ውስጥ አንዱን በመምረጥ የኃይለ ቃሉን ሀሳብ የሚያብራሩ መዘርዝራዊ ዓረፍተነገሮችን በመጨመር አንድ አንቀጽ ጻፉ።**

ሀ. ችግኞችን መትከልና መንከባበከብ በርካታ ጠቀሜታዎች አሉት።

ለ. አንድ ሰው ራሱንና ሌሎች ሰዎችን ከኮሮና ቫይረስ ለመጠበቅ የተለያዩ የመከላከያ ተግባራትን ማከናወን አለበት።

ሐ. ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎችን በየጊዜው ማድረግ አካላዊና አዕምሯዊ ጠቀሜታዎች አሉት።

## ክፍል አምስት፡- ሰዋስው

### ማስታወሻ

### ነጠላ እና ብዙ ቁጥር ስሞች

ስም ከአማርኛ ቋንቋ የቃል ክፍሎች ውስጥ አንዱ ሲሆን በነጠላና በብዙ ቁጥር ሊቀርብ ይችላል፡፡ ነጠላ ቁጥር ስም የሚባለው አንድን ነገር ብቻ በነጠላው የሚገለጽበት ነው፡፡ ብዙ ቁጥር ስም የሚባለው ደግሞ ከአንድ በላይ ለሆኑ ተመሳሳይ ስሞች መገለጫ ነው፡፡

ምሳሌ፡-

| ነጠላ ቁጥር | ብዙ ቁጥር |
| --- | --- |
| ዶሮ | ዶሮዎች |
| ተማሪ | ተማሪዎች |

### ተግባር 1

**ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላት በደብተራችሁ ላይ በመጻፍ ነጠላ ወይም ብዙ ቁጥር መሆናቸውን ከለያችሁ በኋላ ዓረፍተነገር መስርቱባቸው፡፡**

ምሳሌ፡-

ደብተር - ነጠላ ቁጥር

የሒሳብ ደብተር አልቆብኛል፡፡

ደብተሮች - ብዙ ቁጥር

ሰናይት በዚህ ወር ሶስት ደብተሮች ገዝታለች፡፡

ሀ. አያት

ለ. ቤቶች

ሐ. ወፎች

መ. መምህሮች

ሠ. እንስሳዎች

## ተግባር 2

**ቀጥሎ በቀረቡት ዓረፍተነገሮች ውስጥ የሚገኙትን ስሞች ካወጣችሁ በኋላ ነጠላ ወይም ብዙ ቁጥሮች መሆናቸውን ለይታችሁ አመልክቱ፡፡**

ምሳሌ፡-

1. ሰዎች በስራ ላይ ናቸው፡፡ (በዚህ ዓረፍተነገር ውስጥ ያለው ስም ‹‹ሰዎች›› የሚለው ሲሆን ብዙ ቁጥርን ያመለክታል፡፡)
2. አዲስ ጠረጴዛ ገዛሁ፡፡ (በዚህ ዓረፍተነገር ውስጥ ያለው ስም ‹‹ጠረጴዛ›› የሚለው ሲሆን ነጠላ ቁጥርን ያመለክታል፡፡)

ሀ. ሸማግሌዎች የተጣላን ያስታርቃሉ፡፡

ለ. መጽሐፍ ማንበብ ይጠቅማል፡፡

ሐ. አይጥ ያገኘችውን ነገር ትበላለች፡፡

መ. ልጆች መጫወት ይወዳሉ፡፡

ሠ. ትልቅ ቦርሳ አለኝ፡፡

## ተግባር 3

**የሚከተሉትን ነጠላ ቁጥር ስሞች ወደ ብዙ ቁጥር ቀይራችሁ ጻፉ፡፡**

ሀ. ቀበሮ

ለ. ሀገር

ሐ. ምግብ

መ. በሽታ

ሠ. ችግኝ

## ተግባር 4

**ቀጥሎ የቀረቡትን ብዙ ቁጥር ስሞች ወደ ነጠላ ቁጥር በመቀየር ጻፉ፡፡**

ሀ. ባህሎች

ለ. ፈረሶች

ሐ. ተራራዎች

መ. ወንዞች

ሠ. ቅጠሎች

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ የተለያዩ የትምህርት ይዘቶችን ተምራችኋል፡፡ ይዘቶቹም ማዳመጥና መናገር፣ ንባብ፣ ቃላት፣ ጽሕፈትና ሰዋስው ናቸው፡፡

- በማዳመጥ ክፍል ያዳመጣችሁትን ታሪክ መግለጽን ተመልክታችኋል፡፡
- በንባብ ክፍል ምንባብን በለሆሳስ በማንበብ ሀሳቡን መረዳትን ተረድታችኋል፡፡
- ቃላትን ነጣጥሎ ማንበብ የሚያመለክተው ውስብስብ ቃላትን በምዕላዶች ከፋፍሎ ማንበብን ሲሆን አጣምሮ ማንበብ ደግሞ ተነጣጥለው የቀረቡ ምዕላዶችን በማጣመር በአንድ ላይ ማንበብን ያመለክታል፡፡
- አንቀጽ የሚዋቀረው የአንቀጹን ዋና ሀሳብ የሚይዘውን ኃይለ ቃል እና ደጋፊ የሆኑትን መዘርዝራዊ ዓረፍተነገሮችን በመጻፍ ነው፡፡
- ነጠላ ስሞች የአንድ ነገር ነጠላ መጠሪያ ሲሆኑ ብዙ ቁጥር ስሞች ደግሞ ከአንድ በላይ የሆኑ ስሞች በጋራ የሚጠሩበት ነው፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

**ለሚከተሉትን የክለሳ ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡**

1. የሚከተሉትን ቃላት ነጣጥላችሁ አንብቡ፡፡

ሀ. ሰውነት　　　　ሐ. ከልምዳቸው

ለ. ስርዓታዊ　　　　መ. አንደበታችንን

2. ቀጥሎ ተነጣጥለው የቀረቡትን ቃላት አጣምራችሁ አንብቡ

ሀ. በ-መኪና-ው　　　　ሐ. ከ-ተግባር-አዊ-ው

ለ. ሲ-መለስ-ኡ　　　　መ. በ-ድርሰት-ኣችን

3. በዚህ ምዕራፍ ከቀረበው ምንባብ ውስጥ በአንደኛውና በሁለተኛው አንቀጽ ውስጥ የሚገኙትን ኃይለቃሎች በማውጣት አመልክቱ፡፡

4. የሚከተሉት ስሞች ነጠላ ወይም ብዙ ቁጥር መሆናቸውን ለይታችሁ አመልክቱ፡፡

ሀ. ቦርሳ

ለ. ግመሎች

ሐ. እርሳሶች

መ. ሳጥን

# አማርኛ

## ፭ኛ ክፍል

# ምዕራፍ ስድስት

# ጸረ አደንዛዥ እፆችና ንጥረ ነገሮች

ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- አዳምጣችሁ አደንዛዥ እጽን እንዴት መዋጋት እንዳለባችሁ ትገልጻላችሁ፡፡
- ጽሑፉ ስለምን እንደሆነ ትገምታላችሁ፡፡
- ምልክቶችንና መግለጫዎችን በማንበብ የጽሑፉን መልእክት ትረዳላችሁ፡፡
- የመሸጋገሪያ ቃላትን ትለያላችሁ፡፡
- ለቃላት ፍቺ ትሰጣላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥና መናገር

# ትውልድን መታደግ



### ቅድመ ማዳመጥ

**በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ የደረሳችሁበትን ሀሳብ ለመምህራችሁ ግለጹ፡፡**

ሀ. ዜጎችን ከአደንዛዥ እጽ ሱሶች የመከላከል ድርሻ የማን ነው ብላችሁ ታስባላችሁ?

ለ. ከሱስ የጸዳ ዜጋን ማፍራት ለሀገርና ለወገን ያለውን ጠቀሜታ አብራርታችሁ ግለጹ፡፡

## የማዳመጥ ሒደት

### ተግባር

**ቀጥሎ መምህራችሁ ‹‹ትውልድን መታደግ›› የሚል ምንባብ ያነቡላችኋልና በጥሞና አዳምጡ፡፡**

## አዳምጦ መረዳት

### ተግባር 1

**ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ ከተወያያችሁ በኋላ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡**

ሀ. ‹‹የኅብረተሰብ መፍለቂያ›› ሲባል ምን ማለት ነው?

ለ. ወጣቶች በመልካም ስብዕና ማደግ አለባቸው ሲባል ምን ማለት ነው?

ሐ. የጎዳና ተዳዳሪዎች በአደንዛዥ እጾች ሱስ የሚጠመዱት ለምን ይመስላችኋል?

መ. ‹‹የሁሉም ርብርብ ያስፈልጋል›› የሚለው ሀሳብ ምንን ያመለክታል?

ሠ. ወላጆች በማይፈቅዱባቸው ቦታዎች መገኘት ትክክል ነው ብላችሁ ታስባላችሁ? ለምን?

## ተግባር 2

ቀጥሎ የቀረበውን ሰንጠረዥ በደብተራችሁ ላይ በማስፈር ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት አሟሉ፡፡

| | ባለድርሻ አካላት | | |
| --- | --- | --- | --- |
| | በመንግስት | በትምህርት ቤቶች | በወላጆች |
| ታዳጊዎችንና ወጣቶችን ከአደንዛዥ እጽ ሱሰኛነት ነጻ ለማድረግ መከናወን ያለባቸው ተግባራት | | | |

## ተግባር 3

ሱስ በአካላዊ እና አዕምሯዊ እድገት ላይ የሚያሳድረውን አሉታዊ ተጽዕኖ የጤናና የሰውነት ማጎልመሻ መምህራችሁን በመጠየቅ ፅፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡ የጻፋችሁትን መምህራችሁ ሲፈቅዱላችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

## ክፍል ሁለት፡- ንባብ

### ሱስ ደህና ሰንብት



### ቅድመ ንባብ

#### ተግባር

**በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ የደረሳችሁበትን መደምደሚያ ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል ግለጹ፡፡**

ሀ. አደንዛዥ ዕጽ ማለት ምን ማለት ነው?

ለ. በሱስ የተጠመዱ ሰዎች እራሳቸውን ከሱሰኛነት ለማላቀቅ ምን ምን ተግባራትን ማከናወን ያለባቸው ይመስላችኋል?

ሐ. ከላይ የቀረበውን ስዕል በመመልከትና ርዕሱን መሰረት በማድረግ፣ ምንባቡ ስለምን ጉዳይ እንደሚያወሳ ግለጹ፡፡

## የንባብ ሒደት

### ተግባር

**ቀጥሎ ‹‹ሱስ ደህና ሰንብት ›› የሚል ምንባብ ቀርቦላችኋል፡፡ ድምጻችሁን ሳታሰሙ በግላችሁ አንብቡ፡፡**

## ሱስ ደህና ሰንብት

ሱስ የሚባለው አንድ ሰው አንድን ንጥረ ነገር ደጋግሞ ሲወስድ፤ የአወሳሰድ መጠኑን በየጊዜው እየጨመረ ሲሄድ፤ መውሰዱን ለማቆም ሲቸገር እና ሙሉ ትኩረቱን በንጥረ ነገሩ ላይ ሲያደርግ የሚከሰት ነው፡፡ ለዛሬ በዚህ ሂደት ውስጥ ያለፈ አንድ ባለታሪክ ቀርቦላችኋል፡፡ ፍሬዘር ይባላል፤ በሱሰኝነት ሲሰቃይ የነበረ ወጣት ነው፡፡ ይህ ወጣት በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ስር ከሚገኘው አዲስ ሕይወት  የሱስ ተጠቂዎች  ማገገሚያ ማዕከል ለሁለት ወር ከአስራ አምስት ቀን ህክምናውን ሲከታተል ቆይቶ የወጣው ዛሬ ነው፡፡ ይህንን የሰሙ የጎረቤት ሰዎችና ጓደኞቹ ‹‹እንኳን ለዚህ አበቃህ!›› በማለት ደስታቸውን ለመግለጽ በፍሬ ዘር ቤተሰቦች ቤት ተገኝተዋል፡፡

ፍሬዘር ጓደኞቹና የጎረቤት ሰዎች በእሱ ከሱሰኝነት ማገገም ተደስተው ሲያይ ልቡ ተነካ፤ ስሜቱን ለመግለጽ ተቸገረ፡፡ እንደምንም ራሱን አረጋግቶ ከመቀመጫው ተነሳና ዙሪያ ገባውን ቃኘ፡፡ በዙሪያው ያሉት ሰዎች ይጫወታሉ፤ ይስቃሉ፡፡ በጨዋታቸው መሀል አጨበጨበና ዝም እስኪሉ ጠብቆ መናገር ጀመረ‹‹በቅድሚያ ሁላችሁንም አመሰግናለሁ፡፡ እንደምታውቁት እኔ የተለያዩ ሱሶች ማለትም፡- የጫት፣ የሲጋራ፣ የአልኮል መጠጥና ሌሎች ሱሶች ተጠቂ ነበርኩ፡፡ በነዚህ ሱሶች ለበርካታ ዓመታት ስሰቃይ የነበርኩ ምስኪን ሰው ነበርኩ፡፡ በሱሰኝነቴም ምክንያት በማደርጋቸው ነገሮች ቤተሰቤን ጎረቤቶቼንና ጓደኞቼን አሳዝኛለሁ፡፡ እናንተ ግን ያንን ሁሉ እረስታችሁ ከነበረብኝ ሱስ አገግሜ ከማገገሚያ ማዕከል በመውጣቴ የደስታዬ ተካፋይ ለመሆን ከጎኔ በመቆማችሁ በድጋሚ አመሰግናለሁ›› አለ፡፡

በቤቱ ውስጥ የነበሩት ሰዎች በፍሬዘር እርጋታና የአነጋገሩ ብስለት ተገርመው በዝምታ ያደምጡት ነበር፡፡ አንዳንዶቹም የሚናገረው ያ የሚያውቁት ፍሬዘር አልመስል ብሏቸው በትኩረት ይመለከቱታል፡፡ ፍሬዘር መናገሩን ቀጠለ ‹‹አውቃለሁ ብዙዎቻችሁ በህክምናው ባሳየሁት ለውጥ ተገርማችኋል፡፡ እኔም ወደ ማገገሚያ

ማዕከሉ ስገባ እንዲህ በአጭር ጊዜ አስገራሚ ለውጥ የማመጣ አልመሰለኝም ነበር፡፡ የቤተሰቦቼ ጭቅጭቅ በተለይም ደግሞ የእናቴ ልመናና ለቅሶ ስለበዛብኝ ‹እስኪ ደስ ይበላቸው› ብዬ ነበር የሄድኩት፡፡ እኔንም በጣም ባስገረመኝ መልኩ የሀኪሞቹ እንክብካቤና ፍቅር እንዲሁም በከፍተኛ ጥንቃቄ የሚሰጡት የህክምና አገልግሎት ለዚህ አብቅቶኛል፡፡ ስለሆነም የማገገሚያ ማዕከሉን ሀኪሞችና ሌሎች ሰራተኞች በእናንተ ፊት ላመሰግን እወዳለሁ›› ሲል ሁሉም አጨበጨቡ፡፡

ፍሬዘር ጭብጨባው ጋብ ሲል ጠብቆ ንግግሩን ቀጠለ፡፡ ‹‹በዚህ አጋጣሚ ሌሎች ሰዎች ሊያውቁልኝ የምፈልገው ነገር አለ፡፡ ሱስ የሚጀመረው እንደ ቀልድ ነው፡፡ እስኪ ልሞክረው እየተባለ፣ ከጓደኞቼ ጋር ልመሳሰል እየተባለ፣ ለጥናትና ለስራ ነቃ ያደርጋል እየተባለ፣ ደስታ ያስገኛል እየተባለ ወዘተ. ሱስ እንደዋዛ ይጀመራል፡፡ ይሁን እንጂ በቀላሉ የምንገባበት ሱስ ሕይወታችንን በሙሉ ያመሰቃቅለዋል፡፡ ምንም እንኳን ሱስ ይህን ያህል መጥፎ ነገር ቢሆንም ፍላጎቱና ቁርጠኝነቱ ያለው ሰው በግል ጥረቱ ካልቻለም ወደ ማገገሚያ ማዕከላት በመሄድ በአጭር ጊዜ ውስጥ ራሱን ከሱሰኝነት ነጻ ማድረግ ይችላል›› በማለት ሀሳቡን ቋጨ፡፡

በመጨረሻም የጎረቤት ሰዎች እየተነሱ ፍሬዘርን እየመረቁ ወጡ፡፡ የፍሬዘር ጓደኞች ግን አብረውት መጫወታቸውን ቀጠሉ፡፡ ብዙዎቹም የእሱን አርአያነት በመከተል ራሳቸውን ከሱሰኝነት ለማላቀቅ ቃል ገቡ፡፡

## አንብቦ መረዳት፡-

### ተግባር 1

**ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በደብተራችሁ ላይ ከጻፋችሁ በኂላ በምንባቡ ሀሳብ መሰረት ትክክለኛ መልስ የያዘውን ሆሄ በማክበብ መልሱ፡፡**

1. ፍሬዘር የሱስ ማገገሚያ ማዕከል የገባበት ምክንያት ምንድን ነው?

ሀ. የስፖርት ልምምድ ማድረግ ስለነበረበት
ሐ. የትራፊክ አደጋ ደርሶበት ስለነበረ
ለ. የሱስ ተጠቂ ስለነበረ
መ. ወንጀል ሰርቶ ስለነበረ

2. የፍሬዘር ጓደኞች ቃል የገቡት ምን ለማድረግ ነው?

ሀ. ራሳቸውን ከሱስ ለማላቀቅ
ሐ. ጓደኝነታቸውን ለመቋረጥ
ለ. ሀኪም ለመሆን
መ. ችግኞችን ለመትከል

3. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ሰዎች ወደ ሱስ ውስጥ ከሚገቡባቸው ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ነው፡፡

ሀ. በህግ ስለተደነገገ
ሐ. በመምህራን ጫና
ለ. ጊዜው ስለሚፈቅድላቸው
መ. በጓደኛ ግፊት

4. የማገገሚያ ማዕከላት የሚባሉት ምንድን ናቸው?

ሀ. ትምህርት ቤቶች
ሐ. ማረሚያ ቤቶች
ለ. የህክምና መስጫ ቦታዎች
መ. የህግ ተቋማት

5. ፍሬዘር ጓደኞቹንና ጎረቤቶቹን አሳዝኗቸው የነበረው በምን ምክንያት ነው?

ሀ. ወጣት በመሆኑ
ሐ. በታታሪነቱ
ለ. በሱሰኛነቱ
መ. በስፖርተኛነቱ

6. ፍሬዘር ያጨበጨበው ለምንድን ነው?

ሀ. ደስተኛ ስለሆነ　　　　　ሐ. መናገር ስለፈለገ

ለ. ክብረ በዓል ስለሆነ　　　　መ. መዝፈን ስለፈለገ

7. ፍሬዘር ስሜቱን ለመግለጽ የተቸገረው በምን ምክንያት ነው?

ሀ. በሱስ ስለተጠመደ　　　　ሐ. ሌሎቹ ተደስተው በማየቱ

ለ. በፍጥነት በማገገሙ　　　　መ. ፍርሃት ስለያዘው

## ተግባር 2

**ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች በምንባቡ ሀሳብ መሰረት በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ የተስማማችሁበትን ሀሳብ በተወካያችሁ አማካኝነት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለፁ፡፡**

ሀ. ‹‹እንኳን ለዚህ አበቃህ!›› የሚለው አባባል በምን በምን አይነት ማህበራዊ አጋጣሚዎች ሊባል ይችላል?

ለ. ‹‹...በዚህ አጋጣሚ ሌሎች ሰዎች ሊያውቁልኝ የምፈልገው ነገር አለ›› በማለት ሲገልጽ ‹‹በዚህ አጋጣሚ›› በማለት የገለጸው ምን አይነት አጋጣሚን ነው?

ሐ. የምንባቡን አጠቃላይ ሀሳብ በራሳችሁ አገላለጽ በአጭሩ አስረዱ፡፡

መ. በምትኖሩበት አካባቢ የተለያዩ የአደንዛዥ እጾች ሱሰኛ የሆኑ ሰዎችን ታውቃላችሁ? የምታውቁ ከሆነ በምን በምን አይነት ሱሶች እንደተጠመዱና በአካባቢው ኗሪዎች ያላቸው ተቀባይነት ምን እንደሚመስል አብራርታችሁ ግለጹ፡፡

## ክፍል ሶስት፡- ቃላት

### ተግባር 1

**የሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት ቀደም ሲል ካነበባችሁት ምንባብ የወጡ ናቸው፡፡ ቃላቱና ሐረጋቱ በምንባቡ ውስጥ ያላቸውን ዓውዳዊ ፍቺ ግለጹ፡፡**

ምሳሌ፡-

ልቡ ተነካ - አዘነ

ሀ. ምስኪን

ለ. ዙሪያ ገባውን

ሐ. ጋብ ሲል

መ. እርጋታ

ሠ. አብቅቶኛል

### ተግባር 2

**ቀጥሎ የቀረቡት ቃላትና ሐረጋት ከምንባቡ ውጭ ያላቸውን ፍቺ በመግለጽ በፍቺዎቻቸው ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡፡**

ምሳሌ፡-

ማዕከሉ - አማካኝ

የተማሪው አማካኝ ውጤት ከፍተኛ ነው፡፡

ሀ. እንደዋዛ

ለ. ያመሰቃቅለዋል

ሐ. ብስለት

መ. አገግሜ

ሠ. ከጎኔ ቆማችሁ

ተግባር 3

**ቀጥሎ በቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸው ቃላትና ሐረጋት ያላቸውን ዓውዳዊ ፍቺ ግለጹ፡፡**

ሀ. ሰሚራ ምች ስለመታት እናቷ ዳማከሴ አሽታ በሻይ አጠጣቻት፡፡

ለ. ኃይለኛ ዝናብ በመዝነቡ አካባቢው በጭቃ ተጨማልቋል፡፡

ሐ. ታሪኩ ልብሱን በእንዶድ ሙልጭ አድርጎ አጠበ፡፡

መ. ጌታሁን የለየለት አጭበርባሪ ነው፡፡

ሠ. ረድኤት በቆሎ እሸቱን ሽልቅቃ ጠበሰችው፡፡

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

**ማስታወሻ**

**የአንቀጽ መሸጋገሪያ ቃላት**

የአንቀጽ መሸጋገሪያ ቃላት በአንድ ዓረፍተነገር ውስጥ ያሉ ንዑሳን ሀሳቦችን ወይም የሀሳብ ትስስር ያላቸውን ዓረፍተነገሮች ያያይዛሉ፡፡ መሸጋገሪያ ቃላት እንደሚያጣምሩት ሀሳብ ለሁለት ሊከፈሉ ይችላሉ፤ እነሱም ተደጋጋፊ ሀሳቦችን የሚያገናኙ እና ተቃራኒ ሀሳቦችን የሚያገናኙ ናቸው፡፡

ተደጋጋፊ ሀሳቦችን የሚያገናኙ መሸጋገሪያ ቃላት ተመሳሳይ ሀሳቦች የያዙ ዓረፍተ ነገሮችን ለማጣመር ያገለግላሉ፡፡

ምሳሌ፡-

ደመናው ጠቋሯል፤ ስለዚህ ዝናብ መዝነቡ አይቀርም፡፡

ሁለቱ ዓረፍተ ነገሮች ተመሳሳይ (ተደጋጋፊ) ሀሳብ የያዙ ናቸው፡፡ ዓረፍተ ነገሮቹ ተደጋጋፊ መሆናቸውን ለማመልከት ደግሞ ‹‹ስለዚህ›› የሚለው የመሸጋገሪያ ቃል ገብቷል

ተመሳሳይ ሀሳብ ያላቸውን ዓረፍተ ነገሮች ለማጣመር ከሚያገለግሉት የመሸጋገሪያ ቃላት ውስጥ የሚከተሉት በምሳሌነት ቀርበዋል፡፡

| | | |
|---|---|---|
| በተጨማሪም | በመሆኑም | በዚህ አይነት |
| በዚህ የተነሳ | ስለሆነም | በተመሳሳይ |

የተቃረኑ ሀሳቦችን የሚያያይዙ መሸጋገሪያ ቃላት እርስ በርስ የሚፋለሱ ሀሳቦች ያሏቸው ዓረፍተነገሮችን ለማጣመር ያገለግላሉ፡፡

ምሳሌ፡-

ዛሬ በጣም ርቦኛል፤ ነገር ግን የሚበላ ነገር አላዘጋጀሁም፡፡

ሁለቱ ዓረፍተ ነገሮች በያዟቸው ሀሳቦች ይቃረናሉ፡፡ ይህንን ለማመልከትም ተቃርኖን የሚያመለክተው ‹‹ነገር ግን›› የሚለው የመሸጋገሪያ ቃል በመካከላቸው ገብቷል፡፡

ተቃራኒ ሀሳብ ያላቸውን ዓረፍተ ነገሮች ለማያያዝ ከሚያገለግሉ የመሸጋገሪያ ቃላት ውስጥ የሚከተሉት በምሳሌነት ይጠቀሳሉ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ይሁንና | ሆኖም ግን | ቢሆንም |
| ዳሩ ግን | ነገር ግን | ይሁን እንጂ |

ተግባር

**ቀጥሎ ያሉትን የመሸጋገሪያ ቃላት ከስር ባለው አንቀጽ ውስጥ በሚገኙት ክፍት ቦታዎች ውስጥ በመጠቀም አንቀጹ የተሟላ ሀሳብ እንዲኖረው አድርጉ፡፡**

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሆኖም ግን | ምንም እንኳን | ምክንያቱም | በዚህም የተነሳ |

ከድር በዊልቸር የሚንቀሳቀስ አካል ጉዳተኛ ሲሆን በትምህርቱ በጣም ጎበዝ ተማሪ ነው፡፡ ____________ ቤተሰቦቹና መምህሮቹ ደስተኞች ናቸው፡፡ በቤት ውስጥ የሚገኙት የቤተሰቡ አባላት ድጋፍ ያደርጉለታል፡፡ __________ ብዙውን ጊዜ ድጋፋቸውን አይወደውም፡፡_______በእሱ አመለካከት ማንኛውንም ነገር ያለማንም እገዛ ማድረግ እንዳለበት ስለሚያምን ነው፡፡ ቤተሰቦቹ ይህንን አመለካከቱን ቢወዱለትም የእነሱ ድጋፍ የግድ አስፈላጊው እንደሆነ ያስረዱታል፡፡ ______ በተወሰነ ደረጃ ሀሳባቸውን ለመቀበል ወስኗል፡፡

## ክፍል አምስት፡- ሰዋሰው

**ማስታዎሻ**

**ስምና ግስ**

ዓረፍተነገር ሙሉ ሀሳብን የሚያስተላልፍ አነስተኛ የድርሰት ክፍል ነው፡፡ዓረፍነገር ሙሉ ሀሳብ ለማስተላለፍ ቢያንስ ባለቤትና ማሰሪያ አንጽ ሊኖረው ይገባል፡፡ በዓረፍተነገር ውስጥ በባለቤትነት የሚያገለግለው የቃል ክፍል ስም ሲሆን በማሰሪያ አንቀጽነት የሚያገለግለው ደግሞ ግስ ነው፡፡

ለምሳሌ፡-

ሳራ መጣች፡፡ በዚህ ዓረፍተነገር ውስጥ ‹‹ሳራ›› የሚለው ቃል ስም ሲሆን ‹‹መጣች የሚለው ደግሞ ግስ ነው፡፡

## ተግባር 1

**ቀጥሎ በ‹‹ሀ››ስር የቀረቡት ስሞችን በ‹‹ለ›› ስር ከቀረቡት ግሶች በመምረጥ ሙሉ ሀሳብ የሚያስተላልፉ ዓረፍተነገሮች አድርጓቸው።**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ሰዎቹ | ሀ. ሰራው |
| 2. ቴዎድሮስ | ለ. ትሄጃለሽ |
| 3. ሰርኬ | ሐ. ያከማሉ |
| 4. እኛ | መ. እንዋደዳለን |
| 5. አንቺ | ሠ. ትመጣለች |

## ተግባር 2

**ከዚህ ቀጥሎ በቀረበው ሰንጠረዥ ውስጥ ባሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ የሚገኙትን ስምና ግሶች በማውጣት ለይታችሁ በየቃል ክፍሎቻቸው መድቧቸው።**

| ተ.ቁ | ዓረፍተነገር | ስም | ግስ |
|---|---|---|---|
| ምሳሌ | ልጆቹ ደከሙ። | ልጆቹ | ደከሙ |
| ሀ | አስቴር ተመለሰች። | | |
| ሐ | መብረቅ መታው። | | |
| መ | ማር እወዳለሁ። | | |
| ሠ | ዝናቡ መጣ። | | |
| ረ | ጸሐይዋ ታቃጥላለች። | | |

## ተግባር 3

**የሚከተሉትን ቃላት በመጠቀም ዓረፍተነገር መስርቱ።**

ሀ. ዝሆን　　ሐ. ውሃ　　ሠ. ወደቀ

ለ. አሰመረ　　መ. ደጀኔ　　ረ. ቆረጠች

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ የተለያዩ የትምህርት ይዘቶችን ተምራችኋል፡፡ ይዘቶቹም ማዳመጥና መናገር፣ ማንበብ፣ ቃላት፣ ጽሕፈትና ሰዋስው ናቸው፡፡

- በማዳመጥና በመናገር ክፍል አዳምጦ መናገርን ተመልክታችኋል፡፡
- በማንበብ ክፍል ምንባብን አንብቦ ጭብጡን መግለጽን ተረድታችኋል፡፡
- ቃላት የተለያዩ ፍቺዎች ሊኖራቸው ይችላል ዓውዳዊ ፍቺ የሚያመለክተው ቃሉ በዓረፍተነገር ውስጥ ገብቶ የሚኖረውን ፍቺ ነው፡፡
- የመሸጋገሪያ ቃላት ተመሳሳይ ወይም ተቃራኒ ሀሳቦችን የያዙ ዐረፍተነገሮችን ለማጣመር ያገለግላሉ፡፡
- ስም እና ግስ ዋና ዋናዎቹ የዓረፍተነገር ተዋቃሪዎች ሲሆኑ ስም በባለቤትነት እንዲሁም ግስ በማሰሪያ አንቀጽነት ያገለግላሉ፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

**ለሚከተሉት የክለሳ ጥያቄዎች መልስ ስጡ።**

1. ልዩ ልዩ ይዘት ያላቸውን ጽሑፎች አንብባችሁ ጽሑፎቹ የያዙትን ሀሳብ ለመረዳት ሞክሩ፤ ሀሳቡን መረዳታችሁንም እርስ በእርሳችሁ በመጠያየቅ አረጋግጡ።
2. ቀጥሎ ጥንድ ጥንድ ሆነው የቀረቡትን ዓረፍነገሮች የመሸጋገሪያ ቃላትን በመጠቀም አጣምራችሁ እንደገና ጻፏቸው።

   ሀ. በክረምቱ በቂ ዝናብ ዘንቧል።
      በቀጣዩ ዓመት ብዙ ምርት ይገኛል።

   ለ. ሳራ ጎበዝ ተማሪ ናት።
      ሳራ ከትምህርት ቤት መቅረት ታዘወትራለች።

   ሐ. ጤናዳም በቡና ይጠጣል።
      ጤናዳም ለተለያዩ የባልትና ውጤቶች በቅመምነት ያገለግላል።
3. በሚከተሉት ቃላት ውስጥ የተሰመረባቸው ቃላት ያላቸውን ዓውዳዊ ፍቺ ግለጹ።

   ሀ. ሲመክሩት ያልሰማ ሰው መከራ ያስተምረዋል።

   ለ. አጎቴ የነገሩን ጫፍ እንዳስይዘው ጠየቀኝ።

   ሐ. ሀያት የወጣችው በእናቷ ነው።

   መ. ዛሬ በየቴሌቪዥኑ አስደሳች ዜና ሲዘዛር ዋለ።
4. የሚከተሉትን ስሞችና ግሶች ተጠቅማችሁ ሙሉ ሀሳብ የሚያስተላልፉ ዓረፍነገሮች መስርቱ።

   ሀ. ሰበዝ ሐ. ወረወረች

   ለ. ወሰደ መ. እንስሳት

# አማርኛ

## ፭ኛ ክፍል

# ምዕራፍ ሰባት
# ምግብ

### ከምዕራፉ የሚጠበቅ ውጤት

ይህንን ምዕራፍ ተምራችሁ ከጨረሳችሁ በኋላ፡-

- አንድን ገላጭ ጽሁፍ አዳምጣችሁ መልዕክቱን ትገልፃላችሁ፡፡
- ስርዓተ ነጥቦችን ትጠቀማላችሁ፡፡
- አስተካላችሁ ታነባላችሁ፡፡
- ሂደታዊ ተንታኝ አንቀጾችን ተረድታችሁ ትገልጻላችሁ፡፡
- የምዕላድ ዕውቀታችሁን ተጠቅማችሁ እንግዳ ቃላትን ታነባላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥና መናገር

# የምግብ አዘገጃጀት



### ቅድመ ማዳማጥ፡-

### ተግባር

**ቀጥሎ በቀረበው ሠንጠረዥ ውስጥ የምታውቋቸውን ሶስት የምግብ ዓይነቶችና ምግቦቹን ለማዘጋጀት የሚያስፈልጉ ጥሬ ዕቃዎችን ዘርዝሩ፡፡**

| የማውቀው የምግብ ዓይነት | ምግቡን ለማዘጋጀት የሚያስፈልጉ ጥሬ ዕቃዎች |
|---|---|
| | |

## ማዳመጥ ሒደት

### ተግባር

**መምህራችሁ ‹‹የምግብ አዘገጃጀት›› በሚል ርዕስ የተዘጋጀ አንድ ምንባብ ያነቡላችኋልና ማስታወሻ እየያዛችሁ አዳምጡ፡፡**

አዳምጦ መረዳት፡-

### ተግባር 1

**ባዳመጣችሁት ምንባብና ምንባቡን ስታዳምጡ የያዛችሁትን ማስታወሻ መሠረት በማድረግ ለሚከተሉት ጥያቄዎች የቃል ምላሽ ስጡ፡፡**

ሀ. ምግብ ከሚሰጠው ጥቅም አኳያ በስንት ይከፈላል? ምን ምን ተብሎ?

ለ. ከዕፅዋት ምን ምን የምግብ አይነቶች ይገኛሉ?

ሐ. የወተት ተዋጽዖ የሚባሉት ምን ምን ናቸው?

መ . ምግብ ማዘጋጀት ምን ምን ተግባራትን ያካትታል?

ሠ. ‹‹ምግብ ለሰው ልጆች ከሚያስፈልጉ መሠረታዊ ነገሮች አንዱ ነው›› ሲባል ምን ማለት ይመስላችኋል?

ረ. ካዳመጣችሁት ምንባብ ምን ምን ቁም ነገሮችን ተገነዘባችሁ?

### ተግባር 2

**እናንተ የምታውቋቸውን ሰላጣን ለማዘጋጀት የሚያስፈልጉ ግብአቶችን በመዘርዘር እንዴት እንደሚዘጋጅ በቡድን በመወያየት የደረሳችሁበትን ሃስብ በተወካያችሁ አማካኝ ነት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡**

## ክፍል ሁለት፡- ንባብ

# ጤናማ አመጋገብ




### ቅድመ ንባብ

### ተግባር

**ከአሁን በፊት ያላችሁን እውቀት በመጠቀም የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡**

ሀ. ጤናማ አመጋገብ ሲባል ምን ማለት ይመስላችኋል?

ለ. ጤናማ አመጋገብ ምን ምን ጠቀሜታዎችን ያስገኛል?

የንባብ ሒደት፡-

**ተግባር**

**የሚከተለውን ምንባብ በለሆሳስ አንብቡ፡፡**

## ጤናማ አመጋገብ

ምግብ ለሰዎች አስፈላጊና ጠቃሚ ነገር ነው፡፡ ያም ሆኖ ምግብ ለሰው ልጆች ጠቃሚ የሚሆነው በተገቢው መንገድ ስንመገበው ነው፡፡ ምግብን በአግባቡ ካልተመገብነው ከምግብ ማግኘት ያለብንን ተገቢ ጥቅም ማግኘት ካለመቻላችንም ባለፈ ለተለያዩ ችግሮች ሊዳርገን ይችላል፡፡

ዶክተር በጋሻው ሰዎች የአመጋገባቸውን ባህል በማሻሻል ጤናማ ህይወት እንዲመሩ አበክረው ከሚመክሩ የጤና ባለሙያዎች አንዱ ናቸው፡፡ ‹‹ሰዎች የተለያየ የአመጋገብ ልማድ አላቸው›› የሚሉት ዶክተር በጋሻው ‹‹አንዳንዶች ምግብ ስለተገኘ ብቻ ይመገባሉ፡፡ እነዚህ ሰዎች ምግብ የሚበሉት ምግብ ስላስፈለጋቸው ወይም ስለራባቸው ሳይሆን የሚበላ ነገር ስላጋጠማቸው ብቻ ነው፡፡ ስለሆነም ምግብ ከተገኘ በማንኛውም ጊዜና ቦታ ይመገባሉ፤ ካልተገኘ ደግሞ ራሳቸውን በርሀብ ይጎዳሉ ማለት ነው›› ሲሉ ያስረዳሉ፡፡ አያይዘውም ‹‹የሀዘን፣ የደስታ፣ የብቸኝነት ወዘተ. ስሜታቸውን ለመቆጣጠር ሲሉ የሚመገቡም አሉ፡፡ እንደነዚህ ያሉ ሰዎች ምግብን ለምግብነቱ ሳይሆን ለስሜት ማብረጃነት የሚጠቀሙ ናቸው፡፡ ከነዚህ በተቃራኒ የምግብን ምንነትና ጠቀሜታ በሚገባ ተረድተው በተገቢው ጊዜ ተስማሚ ምግብን በተመጠነ መልኩ የሚመገቡ ጠንቃቃ ሰዎችም አሉ›› በማለት ዶክተሩ ሀሳባቸውን ይገልፃሉ፡፡

ዶክተር በጋሻው ስለጤናማ አመጋገብ ሲገልጹ ‹‹ጤናማ አመጋገብ ከተመጣጠነ ምግብ እጥረት ከሚመጡ በሽታዎች ይጠብቀናል፡፡ ከዚህም በላይ ለስኳር ህመም ፣ ለልብ ህመምና መሰል በሽታዎች እንዳንጋለጥ ያደርገናል›› ይላሉ፡፡ በማስከተልም ‹‹ጤነኛ ምግብ ማለትም ከዕፅዋትና ከእንስሳት የተውጣጣ ሆኖ በውስጡም በቂ

ንጥረ ነገሮችን የያዘ ኃይል የሚሰጥና ዕድገትን የሚያፋጥን በሽታን የሚከላከል እንዲሁም ረሀብን የሚያስታግስ ነው፡፡ በውስጡ የሚይዘው የስብ፣ የጨውና ኮሌስትሮል መጠን መጠነኛ መሆን አለበት ጤነኛ ምግብ በውስጡ ከአስር እጅ ያላነሰ ቫይታሚኖችንና ማዕድናትን ሊይዝ ይገባል›› እያሉ ያስረዳሉ፡፡

‹‹ የሚያስፈልጉንን ነገሮች ሁሉ ማሟላት የሚችል አንድ ምግብ የለም›› የሚሉት ዶክተር ‹‹የተመጣጠነ ምግብ ማግኘት የምንችለው ከተለያዩ የምግብ ዓይነቶች ነው፡፡ እነዚህም፡- አትክልትና ፍራፍሬ፣ ጥራጥሬ፣ የእንስሳት ውጤቶችና ውሃ ናቸው›› በማለት ይጠቅሳሉ፡፡

ዶክተር በጋሻው ‹‹ጤነኛ አመጋገብ የአኗኗር ልምድ መሆን አለበት፤ ለቀናት ወይም ለሳምንታት ብቻ ያዝ ለቀቅ እየተደረገ የሚተገበር መሆን የለበትም›› በማለት ያሳስባሉ፡፡ ‹‹ጤነኛ አመጋገብ ሲባል ለአንዳንዶች የተመጣጠነ ምግብ የመመገብ ጉዳይ ሲሆን ለሌሎች ደግሞ ክብደት የማይጨምሩ ምግቦችን የመመገብ ጉዳይ ነው፡፡ ጤነኛ አመጋገብ የተመጣጠነ ምግብ ከመመገብ አኳያ ሲታይ አቅማችን በፈቀደ መልኩ ከአትክልትና ፍራፍሬ፣ ጥራጥሬና የእንስሳት ውጤቶች በየቀኑ መመገብ ነው›› ይላሉ፡፡

ዶክተሩ በማስከተል ‹‹ጤነኛ አመጋገብ ውፍረትን ከመቆጣጠር አኳያ ሲታይ ደግሞ ራስን ሊያወፍሩ ከሚችሉ ምግቦችና የአመጋገብ ልምዶች መቆጠብ ነው፡፡ ለመክሳት ከሚረዱ ጤናማ የአመጋገብ ስልቶች አንዱና ዋነኛው በጣም ሳይራቡ መመገብ ነው፡፡ ምክንያቱም እስኪርበን ጠብቀን የምንመገብ ከሆነ ቶሎ ቶሎ ስለምንጎርስና ሳይታወቀን ብዙ ስለምንመገብ ለውፍረት እንጋለጣለን›› ይላሉ፡፡ ‹‹ሌላው የአመጋገብ ስልት መጠናቸው ትልቅ የሆኑ ቶሎ ሆድን የሚሞሉ፤ ግን ደግሞ አነስተኛ ካሎሪ ያላቸውን ቅጠላ ቅጠል አትክልትና ፍራፍሬ መመገብ ነው›› በማለት ይመክራሉ፡፡

በአጠቃላይ ጤናማ አመጋገብ የተመጣጠነ ምግብ ከመመገብና ውፍረትን ከመቆጣጠር አኳያ ሊታይ ይችላል፡፡ ከሁለቱም አቅጣጫ ስናየው ጥሩ አመጋገብ የምንለው አስፈላጊ ንጥረ ነገሮችን ያሟላና አነስተኛ ካሎሪ ይዘት ያለውን ምግብ በተገቢው ጊዜና መጠን መመገብ ነው፡፡

(ዶ/ር በጋሻው፤ 2012፤ ‹‹ውፍረት›› የተሰኘ ጽሑፍን መነሻ በማድረግ ተቀነባብሮ የተጻፈ)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር 1

**የሚከተሉት ከምንባቡ የወጡ ዓረፍተነገሮች ይዘት ትክክል ከሆነ ‹‹እዉነት›› ስህተት ከሆነ ደግሞ ‹‹ሐሰት›› በማለት በቃል መልሱ፡፡**

1. የሰዎች አመጋገብ ልማድ ተመሳሳይ ነው፡፡
2. ምግብ ለሰው ልጆች ጥቅም እንጂ ጉዳት የለውም፡፡
3. የአመጋገብ ባህልን በማሻሻል ጤናን መጠበቅ ይቻላል፡፡
4. ጠንቃቃ ሰዎች ምግብ ባጋጠማቸው ጊዜ ሁሉ ይመገባሉ፡፡
5. ጤነኛ ምግብ በውስጡ ከአስር እጅ ያላነሰ ቫይታሚኖችንና ማዕድናትን ሊይዝ ይገባል፡፡
6. በጣም ሳይራቡ መመገብ ጤናማ አመጋገብ ነው፡፡

### ተግባር 2

**ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በምንባቡ ሀሳብ መሰረት በጽሁፍ መልሱ፡፡**

1. የመጀመሪያው አንቀጽ ከስንት ዐረፍተ ነገሮች የተዋቀረ ነው?
2. ምንባቡ ስንት አንቀጾችን ይዟል?
3. በአንቀጽ ሁለት ‹‹እነዚህ›› የሚለው ቃል እነማንን ያመለክታል?

4. የስድስተኛው አንቀጽ ትኩረት ምንድን ነው?

5. በአንቀጽ አምስት ውስጥ ‹‹ያዝ ለቀቅ›› ሲል ምን ማለቱ ነው?

## ተግባር 3

**የምንባቡን ሁለተኛ አንቀጽ በጥንድ በጥንድ ሆናችሁ ተራ በተራ በትክክል አንብቡ፡፡ ጓደኞቻችሁ ሲያነብ በትክክል ያላነበባቸውን ቃላት ብዛት ቀጥሎ ያለውን ሠንጠረዥ በደብተራችሁ ላይ በማዘጋጀትና የእዝባር (/) ምልክት በማድረግ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡**

| በመጀመሪያ ንባብ በትክክል ያልተነበቡ ቃላት ብዛት | በሁለተኛ ንባብ በትክክል ያልተነበቡ ቃላት ብዛት |
|---|---|
| | |

ክፍል ሶስት፡- ቃላት

## ተግባር 2

**ቀጥሎ በ‹‹ሀ›› ረድፍ የቀረቡትን ቃላት በ ‹‹ለ›› ረድፍ ከሚገኘው መዝገበ ቃላዊ ፍቺዎቻቸው ጋር አዛምዱ፡፡**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. አሽቆለቆለ | ሀ. አሳምሮ ሰራ |
| 2. አቁላላ | ለ. ወሰን |
| 3. ነከረ | ሐ. ዘፈቀ |
| 4. ከሸነ | መ. አዘቀዘቀ |
| 5. ድንበር | ሠ. አደገ |
| | ረ. ሀገር |
| | ሰ. ጠባበሰ |

## ተግባር 2

**ከዚህ በታች በቀረቡት ዓረፍተነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን ቃላት አውዳዊና መዝገበ ቃላዊ ፍቺ በሠንጠረዥ ውስጥ በመጻፍ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡**

1. ሶፎኒያስ ማለፊያ ቡና በማፍላቱ እናቱ መረቀችው፡፡
2. በክረምቱ ዝናብ ወንዙ ሞልቶ አንድ ሰው በላ፡፡
3. ሰውየው የሚሰጠው አስተያየት ቃሪያ ነው፡፡
4. ልጅቷ በሳል ሀሳብ አቀረበች፡፡
5. ተማሪው ለጓደኞቹ ‹‹ነገ ፈተና አለ›› ብሎ ቀጠፈ፡፡

| የተሰመረበት ቃል | የቃሉ አገባባዊ ፍቺ | የቃሉ መዝገበ ቃላዊ ፍቺ |
|---|---|---|
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

ማስታወሻ

**ሒደታዊ የአንቀጽ ማስፋፊያ ስልት**

ሒደታዊ የአንቀጽ አጻጻፍ ስልት አንድ ነገር እንዴት እንደሚሰራ የሚገለጽበት አንቀጽ የሚጻፍበት ስልት ነው። በዚህ ስልት የተጻፈ አንቀጽ ዓላማው ለመግለፅ የተፈለገው ጉዳይ የሚያልፍባቸውን ደረጃዎችና ሒደቶች በቅደም ተከተል ዘርዝሮ ማቅረብ ነው። የምግብ አዘገጃጀት መመሪያ፣ የጎብኚዎች መመሪያ፣ የምርት አመራረት ወዘተ. በሂደታዊ ስልት ለተጻፈ አንቀጽ ምሳሌዎች ናቸው።

የሚከተለው አንቀጽ በሒደታዊ የአንቀጽ መጻፊያ ስልት የተጻፈ ነው።

**የሾላ ወተት አመራረት**


የሾላ ወተት ፋብሪካ የሚሸጠው ወተት ሕዝብ ዘንድ ከመድረሱ በፊት ብዙ ሂደቶችን ማለፍ አለበት። በመጀመሪያ ወተቱ በአዲስ አበባና በዙሪያ ያሉ ገበሬዎች ከሚያረቧቸው ላሞች ይሰበሰባል። ይህ ወተት በትላልቅ የብረት ጋኖች ተሞልቶ በተሽከርካሪ ተጭኖ ፋብሪካው ዘንድ ይደርሳል። ከዚያም ወተቱ እየተመዘነ ወደ ማፍያ ጋን ውስጥ ይገለበጣል። ወተቱ ጋኑ ውስጥ
በመቶ ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ ይፈላና ወደ ሁለተኛው ማሽን በትላልቅ ቱቦ ይተላለፋል። በሁለተኛው ማሽን ውስጥ ወተቱ በሀያ ሁለት ድግሪ ሴንቲ ግሬድ እንደገና ይፈላና ወተቱ ውስጥ ያለውን ክሬም ይለያል። ክሬሙ ወደ ሌላ ማሽን ሲሄድ ወተቱ ደግሞ ወደ መጨረሻው ማሽን ይላካል በመጨረሻው ማሽን ወተቱ ይቀዘቅዝና በቧንቧ አማካኝነት በጠርሙስና በላስቲክ እየተሞላ ይታሸጋል። ከዚያም በጉልበት ሰራተኞች አማካኝነት በሳጥን ውስጥ እየተደረገ ተቆጥሮ መኪና ላይ ይጫናል። በመጨረሻም ለነጋዴዎች ይሰጥና ለገበያ ቀርቦ ጥቅም ላይ ይውላል።

(ምንጭ ደረጀ ገብሬ፣ 1997፣ ገጽ 164)

## ተግባር 1

**ቀጥሎ ባለው የቢጋር ሠንጠረዥ ውስጥ የእንጀራ ፍርፍር ለማዘጋጀት በቅደም ተከተል የሚተገበሩ ተግባሮችን አስፍሩ፡፡ በመቀጠልም የቢጋር ሠንጠረዡን ተከትላችሁ አንድ አንቀፅ ጻፉና ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡**

የእንጀራ ፍርፍር አዘገጃጀት



## ስርዓተ ነጥቦች

ስርዓተ ነጥቦች የጽሁፍ መልዕክት የተሟላና የማያሻማ እንዲሆን የሚያደርጉ የጽህፈት አጋዥ ምልክቶች ናቸው፡፡ ከነዚህም መካከል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፡

| ምልክቱ | የምልክቱ ስያሜ | የምልክቱ አገልግሎት ምሳሌ |
|---|---|---|
| . | ይዘት | አዲስ አበባ - አ.አ. |
| ፣ | ነጠላ ሰረዝ | አማርኛ፣ሂሳብ፣ ሳይንስ |
| ፤ | ድርብ ሰረዝ | ልጁ እጁን ታጠበ፤ ይሁን እንጂ አልበላም፡፡ |
| ፡፡ | አራት ነጥብ | ኢትዮጵያ ትልቅ ሀገር ናት፡፡ |
| ? | ጥያቄ ምልክት | በአማርኛ ፈተና ስንት አመጣህ? |
| ‹‹ ›› | ትዕምርተ ጥቅስ | ፀሐይ ‹‹መጸሀፍ ማንበብ እወዳለሁ›› አለች ፡፡ |
| / | እዝባር | አዲስ አበባ አ/አ<br>በየጊዜው በሚገባ መብላት / መመገብ አለብን፡፡ |
| ( ) | ቅንፍ | በየጊዜው በሚገባ መብላት(መመገብ) አለብን፡፡ |

### ተግባር 2

**ከዚህ በታች ባሉት ባዶ ቦታዎች ውስጥ ተገቢውን ሥርዓተ ነጥብ (የጽህፈት አጋዥ ምልክት) በማስገባት ዓረፍተነገሮቹን አሟሉ፡፡**

1. በግ__ላም___ ፍየልና በሬ የቀንድ ከብቶች ናቸው፡፡
2. ዶ_ር አክሊሉ ለማ የተወለዱት በ1928 ዓ_ም_ ነው፡፡
3. ፌዝ ያስንቃል___ ያስነውራልም፡፡
4. አንተ ልጅ ጨዋታ የምትጠግበው መቼ ነው________
5. የት እንደሄደ___ ምን እንደሰራ ___ አጣርተሽ እንድትነግሪኝ፡፡
6. የኔ ሙያተኛ ልጅ ልብሱን በካውያ ተኮሰው_______________
7. ገንዘብ ያገኘው አስር ሺህ ብር አጉድሎ ዘበጥያ ___ ወህኒ___ ወረደ፡፡

አኅፅሮተ ቃል ( ቃላትን ማሳጠር)

አኅፅሮተ ቃል በብዙዎች ዘንድ የተለመዱ ቃላትን ወይም ስያሜዎችን በጥቂት ሆህያት ወክሎ መጻፍ ነው። አሳጥረን ለመጻፍ ይዘትን ወይም እዝባርን እንጠቀማለን።

ምሳሌ፡-

| ቃሉ (ስሙ) ተሟልቶ ሲጻፍ | ቃሉ (ስሙ) በአኅጽሮተ ቃል ሲጻፍ |
|---|---|
| ዶክተር | ዶ.ር |
| መምህር | መ.ር |
| የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር | ኢ.መ.ማ. |
| አጣዳፊ ተቅማጥና ትውከት | አ.ተ.ት. |

## ተግባር 3

**የሚከተሉትን ቃላት( ስሞች) በምኅጻረ ቃል ጻፉ።**

1. ወታደር ------------------------
2. ዐረፍተ ነገር ---------------------
3. የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት --------------------
4. የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌደሬሽን -------------------------
5. የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ -------------------
6. የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ---------------------

## ተግባር 4

**የሚከተሉትን በምኅጻረ ቃል የተጻፉ ቃላት( ስሞች) በሙሉ አገላለፅ ጻፉ።**

1. ኢ.መ.ማ.------------------------------------------------------------------
2. ር.መ.ር ------------------------------------------------------------------
3. ተ.ቁ. ------------------------------------------------------------------
4. ኢ.መ.ባ. ------------------------------------------------------------------
5. ኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ. ------------------------------------------------------------

## ክፍል አምስት፡- ሰዋስው

**ማስታወሻ**

**የሚቆጠሩና የማይቆጠሩ ስሞች**

ስም የሚቆጠር ወይም የማይቆጠር ሊሆን ይችላል።

**የሚቆጠሩ ስሞች፡-** በነጠላና በብዙ ቁጥር ሊነገሩ የሚችሉ ስሞች ናቸው።

**የማይቆጠሩ ስሞች፡-** በብዙ ቁጥር ሊነገሩ የማይችሉ ስሞች ናቸው።

**ምሳሌ፡-**

| የሚቆጠሩ ስሞች | የማይቆጠሩ ስሞች |
|---|---|
| በግ - በጎች | ጨለማ |
| ቃል - ቃላት | ዱቄት |
| በሬ - በሬዎች | ዕውቀት |
| መጽሐፍ - መጻሕፍት | ብርሀን |

የማይቆጠሩ ስሞች አንድ ሁለት ተብለው ሊቆጠሩ አይችሉም። በብዙ ቁጥር ሊነገሩ ስለማይችሉም -ኦች ወይም -ዎች የሚለውን ጥገኛ ምዕላድ አያስከትሉም።

## ተግባር

**ከዚህ በታች በቢጋሩ ውስጥ የተዘረዘሩትን ስሞች የሚቆጠሩና የማይቆጠሩ በማለት መድቡ።**

ዛፍ፣ንፋስ፣ዣንጥላ፣ፍቅር፣ሠዓት፣ውሃ፣ጠርሙስ፣አገልግል፣ፍርሀት፣ወተት፣ቢራቢሮ፣እሳት፣ብርቱካን፣ዝናብ፣ኮከብ፣ብስኩት፣ልጅ፣መንደር

| የሚቆጠሩ ስሞች | የማይቆጠሩ ስሞች |
| --- | --- |
| | |

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

**በዚህ ምዕራፍ የተለያዩ የትምህርት ይዘቶችን ተምራችኋል፡፡ ይዘቶቹም ማዳመጥና መናገር፣ ንባብ፣ ቃላት፣ ጽሕፈትና ሰዋስው ናቸው፡፡**

- አንድን የሚደመጥ ነገር ስታዳምጡ ማስታወሻ እየያዛችሁ ማዳመጥ ሀሳቡን ለመረዳት ይረዳችኋል፡፡
- ምንባብ በሚነበብበት ወቅት እያቀላጠፉ ማንበብ ተገቢ ሲሆን አንድን ምንባብ ስታነቡ የፈጸማችኋቸውን የቃላት ግድፈቶች እርስ በእርሳችሁ በማስታወሻ በመያዝ በሚቀጥለው ንባባችሁ ያለግድፈት ለማንበብ ሞክሩ፡፡
- ለቃላት ፍቺ ለመስጠት በዓረፍተነገር ውስጥ የገባበትን ዐውድ መገንዘብ ተገቢ ነው፡፡ ይህም የሚያስፈልገው ቃላት እንደየአገባባቸው ፍቺዎቻቸውም ስለሚለያይ ነው፡፡
- የአንድን ነገር አሰራር ወይም አካሄድ ቅደም ተከተል ለመግለጽ አንቀጽን በቅደም ተከተላዊ አጻጻፍ ስልት መጻፍ ተገቢ ነው፡፡
- አንድን ሀሳብ በጽሑፍ ለማስተላለፍ የስርዓተ ነጥቦች ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ የስርዓተ ነጥቦች ዋና አገልግሎት አንድ ጽሑፍ የተሟላ ሀሳብ እንዲያስተላልፍ ማድረግ ነው፡፡
- ስም የሚቆጠርና የማይቆጠር ሊሆን ይችላል፡፡ የሚቆጠር ስም በነጠላም ሆነ በብዙ ሊጠራ የሚችል ሲሆን የማይቆጠር ስም ደግሞ በብዙ ቁጥር ሊጠራ የማይችል ነው፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

ለሚከተሉት የክለሳ ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡

1. ከሚከተሉት ርዕሰ ጉዳዮች ውስጥ አንዱን መርጣችሁ በቅደም ተከተላዊ የአጻጻፍ ስልት አንቀጽ ጻፉ፡፡

ሀ. የቡና አፈላል ሒደት

ለ. የዶሮ ወጥ አሰራር

ሐ. የቡሄ ጭፈራ አጨፋፈር

መ. የጥጥ አፈታተል

ሠ.የዳንቴል አሰራር

ረ. በቆሎ አዘራር

2. ቀጥሎ በቀረቡት ዓረፍተነገሮች ተገቢዎቹን የስርዓተ ነጥብ አይነቶች በትክክለኛ ቦታቸው በማስገባት ዓረፍተነገሮቹ ሙሉ ሀሳብ እንዲያስተላልፉ አድርጓቸው

ሀ. በጊዜ መተኛት እፈልጋለሁ ነገር ግን ገና ስራዬን አልጨረስኩም

ለ. አስካለ እናቷን በጊዜ እመለሳለሁ ብላት ወደ ቤተ መጻሕፍት ሄደች

ሐ. ደረጀ ትምህርቱን የጨረሰው እኤአ በ1997 ዓም ነው

መ. ማርኮን ራሔል እና እኔ አብረን እንመጣለን

ሠ. ትናንትና ለምን ከትምህርት ቤት ቀረህ

3. የሚከተሉትን ስሞች የሚቆጠሩ ወይም የማይቆጠሩ መሆናቸውን ለይታችሁ አመልክቱ፡፡

| | |
|---|---|
| ሀ. ሀገር | መ. ቅባት |
| ለ. ሰማይ | ሠ. ሙዚቃ |
| ሐ. ቡና | ረ. ስራ |

# አማርኛ

## ፭ኛ ክፍል

# ምዕራፍ ስምንት

# በኢትዮጵያ የሚገኙ የዱር እንስሳት

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- ውስብስብ ቃላት በምዕላድ እንዴት እንደሚከፋፈሉ ትገልጻላችሁ፡፡
- ውስብስብ ቃላትን ታነባላችሁ፡፡
- አወዳዳሪና አነጻጻሪ አንቀጽ ትጽፋላችሁ፡፡
- ለቃላት ዓውዳዊ ፍቺ ትሰጣላችሁ፡፡
- ተሻጋሪና የማይሻገሩ ግሶችን ትጠቀማላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥና መናገር

# በቀቀኖችን ስሙን



### ቅድመ ማደመጥ

#### ተግባር

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃል መልስ ስጡ፡፡**

ሀ. ስለ በቀቀን የምታውቁትን ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

ለ. በኢትዮጵያ ብቻ ከሚገኙ የዱር እንስሳት ውስጥ የምታውቋቸውን ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

ሐ. የዱር እንስሳት ከሰዎች ጋር መኖር የሚችሉ ይመስላኗል?

### የማዳመጥ ሒደት

#### ተግባር

**መምህራችሁ ‹‹በቀቀኖችን ስሙን›› የሚል ርዕስ ያለው ምንባብ ያነቡላችኋል፡፡ ምንባቡን በጥሞና አዳምጡ፡፡**

### አዳምጦ መረዳት

## ተግባር 1

**ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ፡፡**

ሀ. በአካባቢያችሁ ስንት አይነት የወፍ ዝርያዎችን ታውቃላችሁ? የምታውቋቸውን የወፍ ዝርያዎች ዘርዝራችሁ ተናገሩ፡፡

ለ. የበቀቀኖች የአኗኗር ዘይቤ እንዴት እንደሆነ አብራርታችሁ ግለጹ?

ሐ. በቀቀኖች የዱር እንስሳት ሆነው ሳለ በአንዳንድ ሰዎች መኖሪያ ቤት ውስጥ እንዴት ሊኖሩ የቻሉ ይመስላችኋል?

መ. በሀገራችን የዱር እንስሳት የሚያላምዱ ሰዎች ያሉበት አካባቢዎች ያሉ ይመስላችኋል? መልሳችሁ አዎ ከሆነ የት አካባቢ እና ምን አይነት እንስሳ እንደሚያላምዱ ግለጹ፡፡

ሠ. በቤት እንስሳት እና በዱር እንስሳት መካከል ያለውን አንድነት እና ልዩነት የሳይንስ መምህራችሁን በመጠየቅ ማስታወሻ ይዛችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አብራርታችሁ ግለጹ፡፡

## ተግባር 2

**ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ትክክለኛ መልስ የያዘውን ሆሄ በመምረጥ መልስ ስጡ፡፡**

1. አብዛኛዎቹ የበቀቀን ዝርያዎች የመጥፋት አደጋ የተጋረጠባቸው በምን ምክንያት ነው?

   ሀ. በዱር ድመቶች በመበላታቸው　　　ሐ. እንቁላል ጣይ በመሆናቸው

   ለ. ለሰው ልጆች መጫወቻ በመሆናቸው　መ. ሀ እና ለ መልሶች ናቸው፡፡

2. ወንድ በቀቀኖች የሕይወት አጋሮቻቸውን ለማግኘት ምን አይነት ዘዴዎችን ይጠቀማሉ?

ሀ. ምግብ ያቀርባሉ　　　　ሐ. ይፋለማሉ

ለ. ዘፈንና ዳንስ ያሳያሉ　　　　መ. ይጮኻሉ

3. ሰዎች በቀቀኖችን በቤታቸው ውስጥ ማስቀመጥ የሚወዱት ለምንድን ነው?

ሀ. ድምጽ ስለሚቀዱ　　　　ለ. ስለሚያዝናኑ

ሐ. ማራኪ ውበት ስላላቸው　　　　መ. ሁሉም

4. በቀቀኖች ጎጇቸውን በምን ላይ ሊሰሩ ይችላሉ?

ሀ. በበረዶ ላይ　　　　ለ. በጉድጓድ ውስጥ

ሐ. በውሃ ላይ　　　　መ. በቤት ውስጥ

5. በቀቀኖች በአመጋገባቸው ከየትኛው የእንስሳት ምድብ ይመደባሉ?

ሀ. ከስጋ በል　　　　ሐ. ከሁሉ በል

ለ. ከእጽ በል　　　　መ. ከቅጠል በል

6. በቀቀኖችን የሰማይ ላይ ፈርጦች ያስባላቸው ምንድን ነው?

ሀ. በራሪ በመሆናቸው　　　　ሐ. ደማቅ ቀለማቸውና ዝማሬያቸው

ለ. እንቁላል ጣይ በመሆናቸው　　　　መ. ድምጽ ማስመሰል በመቻላቸው

7. የጫካ በቀቀኖች በምን አይነት የአየር ንብረት መኖር ይመርጣሉ?

ሀ. በደጋማ　　ለ. በሞቃታማ　　ሐ. በብርዳማ　　መ. በውርጭ

8. በቀቀን ስንት የእግር ጣቶች አሉት?

ሀ. ሁለት　　　　ሐ. አምስት

ለ. አራት　　　　መ. ስምንት

## ክፍል ሁለት፡- ንባብ

## የዱር እንስሳት ጥቅም



### ቅድመ ንባብ

#### ተግባር

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃል መልስ ስጡ።**

ሀ. የዱር እንስሳት የሚባሉት ምን አይነት ባህርይ አላቸው?

ለ. የዱር እንስሳት ምን ምን ጥቅም ያላቸው ይመስላችኋል?

ሐ. ከላይ ያለውን ስዕልና የምንባቡን ርዕስ መሰረት በማድረግ ምንባቡ ስለምን የሚያወሳ እንደሆነ ገምቱ።

### የንባብ ሒደት፡-

#### ተግባር

**የሚከተለውን ምንባብ በየግላችሁ በለሆሳስ አንብቡ።**

## የዱር እንስሳት ጥቅም

የዱር እንስሳት አጥቢ፣ አእዋፍ፣ በደረት ተሳቢ፣ በከፊል በየብስና በውኃ የሚኖሩ፣ ዓሣና ነፍሳት እየተባሉ በዓይነት ይከፋፈላሉ። እነዚህ የተለያዩ ዓይነት

የዱር እንስሳት በርካታ ጠቀሜታዎችን ይሰጣሉ፡፡ ጥቅሞቹም ሥነ-ምህዳራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ሳይንሳዊ፣ ማህበራዊና ፈውሳዊ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

የዱር እንስሳት የተፈጥሮ ሚዛንን ለመጠበቅና የተስተካከለ የአየር ንብረት እንዲኖር በማድረግ ሥነ-ምህዳራዊ ጥቅም ይሰጣሉ፡፡ የአፈር መከላትን በመከላከል የአፈር ለምነትን ያሻሽላሉ፡፡ በዚህም ወንዞች፣ ጅረቶች፣ ረግረጎችና ሐይቆችን የመሳሰሉ የውኃ አካላት እንዲፈጠሩ ያደርጋሉ፡፡ የእፅዋት ዘር ስርጭት እንዲካሄድና የደንና ዕፅዋት ሽፋን እንዲጨምር እንዲሁም ዝርያቸው ተጠብቆ እንዲቆይ የዱር እንስሳት የላቀ ሚና አላቸው፡፡ ተፈጥሯዊ የምግብ ሰንሰለትን ተከትለው አንዱ ሌላውን በመመገብ የእንስሳት ቁጥር የተመጣጠነ እንዲሆን ያደርጋሉ፡፡

በተጨማሪም የቱሪስት መስህብ በመሆንና የተለያዩ የስራ ዕድሎችን በመፍጠር የዱር እንስሳት ምጣኔ ሀብታዊ ጠቀሜታ ያስገኛሉ፡፡ በዱር እንስሳትና በመኖሪያ አካባቢያቸው የሚደረግ ጉብኝት ለሰው ልጅ የአዕምሮ ደስታን የሚሰጥ ከመሆኑም በላይ የገቢ ምንጭ በመሆን ያገለግላል፡፡ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ጎብኝዎች ወደ ዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች በመጓዝ የተፈጥሮን ውበት ይጎበኛሉ፡፡ የዱር እንስሳትንና መኖሪያቸውን ለመጎብኘት የሚንቀሳቀሱ ጎብኝዎች ሆቴል ሲያርፉ፣ ምግብ ሲጠቀሙ፣ የተለያዩ ዕቃዎችን ሲገበያዩና ሕጋዊ የአደን ቱሪዝም ሲያከናውኑ ለሀገር ገቢ ያድጋል፡፡ ሕብረተሰቡ በዘርፉ የተሰማሩ ባለሙያዎችና ባለሀብቶችም ይጠቀማሉ፡፡ እንደየአካባቢው ባህልና ሃይማኖት አንዳንድ የዱር እንስሳት ስጋቸው፣ እንቁላላቸው እንዲሁም ማራቸው ለሰው ልጆች ምግብነት ይውላል፡፡ ለአብነትም ከርከሮ፣ የሜዳ ፍየል፣ ድኩላ፣ አጋዘን፣ አሳማ፣ ጅግራ፣ ዳክዬና ቆቅ የመሳሰሉትን የዱር እንስሳትን መጥቀስ ይቻላል፡፡

በተጨማሪም የዱር እንስሳት ለመማሪያነት ለጥናትና ምርምር ስራ በመዋል ለሳይንሳዊ ዕውቀት መስፋፋት ከፍ ያለ አስተዋፅዖ አላቸው ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ የዱር እንስሳት ለመድኃኒትነት ጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡ ሰማንያ እጅ የሚሆነው የባህል መድኃኒትም የሚዘጋጀው ከዱር እንስሳትና እፅዋት ነው፡፡ እንዲሁም ሃያ እጅ የሚሆነው በፋብሪካዎች የሚመረተው መድኃኒትም ቢሆን ከተፈጥሮ ሀብት የሚዘጋጅ እንደሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

የዱር እንስሳት ማኅበራዊ ጥቅምም አላቸው፡፡ በጎብኚዎችና በቱሪስት መስህብ አካባቢዎች በሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር በሚያደርጉት ግንኙነት ጠቃሚ ልምዶችና እውቀቶችን ይቀስማሉ፤ የልምድ ልውውጥ ያደርጋሉ፡፡ በተጨማሪም የተለያዩ የንግድ ድርጅቶች የዱር እንስሳት ስምና ምስል ለድርጅቶቻቸው መጠሪያነትና አርማነት ሲጠቀሙ ይታያሉ፡፡ ለምሳሌ አንበሳ አውቶቡስ፣ ኒያላ ኢንሹራንስ፣ አንበሳ ባንክ፣ የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ፡፡ የኢትዮጵያ የወንዶች እግር ኳስ ቡድንም ‹‹ዋሊያዎቹ›› በመባል ይታወቃል፡፡ እነዚህም የዱር እንስሳቱ ከሚሰጡት ማህበራዊ ጥቅም ይመደባሉ፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ መልኩ ሊጠቀስ የሚገባው በሀገራችን የሚገኙ አንዳንድ ብሔረሰቦች ባህላቸውን ለመግለጽ የዱር እንስሳት ውጤቶችና የመኖሪያ አካባቢያቸውን እንደሚጠቀሙ ነው፡፡ ለምሳሌ የአንበሳ ቆዳ፣ የነብር ቆዳ፣ የአቦ ሸማኔ ቆዳ፣ የሰጎን ላባ፣ የአንበሳ ጎፈር፣ የአጋዘን ቀንድ የመሳሰሉትን የዱር እንስሳት ውጤት በመጠቀም ባህላዊ ሥርዓታቸውን ይገልጻሉ፡፡ ይህም የዱር እንስሳት ባህላዊ ጥቅም ይባላል፡፡

ጠቅለል ባለ አገላለፅ የዱር እንስሳት ጥቅም ዘርፈ ብዙ ስለሆኑ ዘርዝሮ መጨረስ አይቻልም፡፡ በመሆኑም የዱር እንስሳት ይህን ያህል ጠቀሜታ እንዳላቸው በሚገባ ተረድተን በአግባቡ ልንጠቀምባቸውና ህልውናቸው አደጋ ላይ እንዳይወድቅ አስፈላጊውን እንክብካቤና ጥበቃ ልናደርግላቸው ይገባል፡፡

ምንጭ፡- ( የኢትዮጵያ የዱር እንሰሳት ሀብት ገፅታ፤ ህዳር 2010 ዓ.ም)

## አንብቦ መረዳት፡-

### ተግባር 1

**ቀጥሎ የቀረበውን ሰንጠረዥ ካዘጋጃችሁ በኋላ የዱር እንስሳት ያላቸውን ጠቀሜታዎች በተሰጡት ክፍት ቦታዎች ዘርዝራችሁ ግለጹ፡፡**

| ምሳሌ | የዱር እንስሳት ጠቀሜታዎች | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ማህበራዊ | ኢኮኖሚያዊ | ፈውሳዊ | ስነ ምህዳራዊ |
| | ባህልን ለመግለጽ | ከጎብኝዎች ገቢ ለማስገኘት | ልዩ ልዩ መድኃኒቶችን ለመቀመም | አፈር እንዳይሸረሸር ለማድረግ |
| | ➢ | ➢ | ➢ | ➢ |
| | ➢ | ➢ | ➢ | ➢ |
| | ➢ | ➢ | ➢ | ➢ |
| | ➢ | ➢ | ➢ | ➢ |
| | ➢ | ➢ | ➢ | ➢ |

## ተግባር 2

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች መምህራችሁ በሚያሏችሁ መሰረት በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ በተወካያችሁ አማካኝነት በቃል መልስ ስጡ፡፡**

ሀ.በምንባቡ ውስጥ የአንቀጽ አንድ መልዕክት ምንድን ነው?

ለ. ‹‹የምግብ ሰንሰለት›› የሚለው ሀረግ የሚያስተላፈው መልዕክት ምንድን ነው?

ሐ. በምንባቡ ላይ ከአንቀጽ ሶስት ወደ አንቀጽ አራት የተጠቀመው መሸጋገሪያ ምንድን ነው?

መ. ‹‹አንዱ ሌላውን በመመገብ የእንስሳት ቁጥር የተመጣጠነ እንዲሆን ያደርጋሉ›› ሲባል ምን ለማለት ተፈልጎ ነው ?

## ተግባር 3

**የሚከተለውን የቢጋር ሰንጠረዥ በደብተራችሁ አዘጋጁ፡፡ ከዚያም በአካባቢያችሁ የምታውቋቸውን የዱር እንስሳት አይነቶች መሰረት በማድረግ በምሳሌው መሰረት ቢጋሩን በማሟላት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንግግር አድርጉ፡፡**

| | |
|---|---|
| አጥቢ | ጎሽ |
| እንቁላል ጣይ | ቆቅ |
| በራሪ | ጭልፊት |
| ተሳቢ | ዘንዶ |
| የሚበሉ | ሚዳቋ |
| የማይበሉ | አንበሳ |

## ክፍል ሶስት፡- ቃላት

### ተግባር 1

**በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ላይ የተሰመረባቸው ቃላት ያላቸውን ዓውዳዊ ፍቺ በመጻፍ መልሱ፡፡**

ሀ. ተማሪዋ ቁልፍ ጥያቄ አነሳች፡፡

ለ. የታመመ ሰውን መጠየቅ ከጥንት የመጣ ባህላችን ነው፡፡

ሐ. በመኪናዎች ጥሩንባ የአካባቢው ሰላም ተበጠበጠ፡፡

መ. ምግብ የረሃብ መድኃኒት ነው፡፡

ሠ. ቤት ከመዋል ስራ መስራት የተሻለ ነው፡፡

ረ. ሁሉም መረጃ ሰንሰለቱን ጠብቆ መሄድ አለበት፡፡

ሰ. ሁሉም ሰው በተሰማራበት የሙያ ዘርፍ ጠንክሮ ይሰራል፡፡

### ተግባር 2

**ቀጥሎ የቀረበውን ምሳሌ መሰረት በማድረግ በቃላቱ ውስጥ የሚገኙትን ፊደላት ቦታቸውን በመቀያየር የትርጉም ለውጥ እንዲያመጡ ያድርጓቸው፡፡**

ምሳሌ፡- ለመለመ - መለመለ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሀ. ጠበሰ | ሐ. ደረሰ | ሠ. ቀጠቀጠ | ሰ. ገነፈለ |
| ለ. መከተ | መ. ደገመች | ረ. አልቦ | |

### ተግባር 3

**ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላት በትክክለኛው የምዕላድ አከፋፈል ስርአት በመከፋፈል አማልክቱ፡፡**

ምሳሌ፡- ሰማችኋት = ሰም-ኣችሁ-ኣት

ሀ) ስለመጣች

ሐ) በቶቹን

ለ) ሰዎቻችን

መ) ለምለሟ

ማስታወሻ

**በማወዳደርና በማነጻጸር ስልት አንቀጽ መጻፍ**

ከአንቀጽ ማስፋፊያ ዘዴዎች ውስጥ ገላጭ እና ተራኪ ስልቶችን በምዕራፍ ሶስት ተምራችኋል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ደግሞ በማወዳደርና በማነጻጸር ስልት አንቀፅ መጻፍን ትማራላችሁ፡፡

**የማወዳደርና የማነጻጸር ስልት፡-** የሁለት ነገሮችን አንድነትና ልዩነት በመግለጽ የሚብራራበት የአንቀጽ ማስፋፊያ ስልት ነው፡፡

**ማወዳደር፡-** በሁለት የተለያዩ ነገሮች መካከል ያለውን ተመሳሳይነት ማሳየት ነው፡፡


**ማነጻጸር፡-** በተመሳሳይ ነገሮች መካከል ያለውን ልዩነት በመግለጽ ላይ ያተኩራል፡

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

### ተግባር 1

ቀጥሎ የቀረበውን ቢጋር በደብተራችሁ አዘጋጁ፡፡ በመቀጠልም በቤት እንስሳት እና በዱር እንስሳት መካከል ያለውን ልዩነት እና አንድነት የሚገልጹ ሀሳቦችን ዘርዝሩ፡፡

የቤት እንስሳ ልዩነታቸው    የዱር እንስሳ ልዩነታቸው




ተግባር 2

**ከላይ በቢጋሩ ላይ ያቀረባችኋቸውን ሀሳቦች በማቀናጀት በማወዳደርና በማነጻጸር ስልት የተስፋፋ አንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡**

ተግባር 3

**ቀጥሎ ከቀረቡት መንደርደሪያ ሀሳቦች አንዱን በመምረጥ ወይም የራሳችሁን መንደርደሪያ ሀሳብ በመውሰድ በማነጻጸርና በማወዳደር ስልት አንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡**

ሀ. የኮሮና እና የጉንፋን ቫይረስ የሚያመሳስሏቸው እና የሚያለያዩዋቸው ምልክቶች አሉ፡፡

ለ. ነጭ ሽንኩርትና ቀይ ሽንኩርት የሚያመሳስላቸው ነገሮች እንዳሉ ሁሉ የሚያለያዩዋቸው ነገሮችም አሉ፡፡

ሐ. ጀልባና መርከብ የሚያሳስሏቸው ነገሮች እንዳሉ ሁሉ የሚያመሳስላቸው ነገሮችም አሉ፡፡

## ክፍል አምስት፡- ሰዋሰው

### ማስታወሻ

**ተሻጋሪ እና የማይሻገሩ ግሶች**

ግስ ድርጊትን የሚያመለክት የቃል ክፍል እንደሆነ ቀደም ባሉት ክፍሎች ተምራችኋል፡፡ ድርጊትን የሚገልጹት ግሶች እንደሚከናወነው ድርጊት ተሻጋሪ እና የማይሻገሩ ግሶች በመባል በሁለት ይከፈላሉ፡፡

**ተሻጋሪ(ሳቢ) ግሶች፡-** የሚባሉት ድርጊቱ ከአንድ አካል ወደ ሌላ አካል ሲተላለፍ (ሲሻገር) የሚያሳዩ ናቸው፡፡

ምሳሌ፡-

ዚነት ደብተር ገዛች፡፡

በዚህ ዓረፍተነገር ግሱ ‹‹ገዛች›› የሚለው ሲሆን ድርጊቱ ከዚኒት ወደ ደብተር ተሸጋግሯል፡፡

**የማይሻገሩ(ኢ-ሳቢ) ግሶች፡-** የሚባሉት በባለቤቱ ላይ የሚያልቁ ድርጊቶችን ለመግለጽ የሚያገለግሉ ግሶች ናቸው፡፡

ምሳሌ፡-

ማክቤል ከትምህርት ቤት መጣ፡፡

በዚህ ዓረፍተነገር ውስጥ ‹‹መጣ›› የሚለው ቃል ድርጊቱ ወደ ሌላ አካል አለመተላለፉን (በባለቤቱ ላይ ማለቁን) ያመለክታል፡፡

### ተግባር 1

**በሚከተለው ሰንጠረዥ ውስጥ የሚገኙትን ግሶች ተሻጋሪ ወይም የማይሻገሩ ግሶች መሆናቸውን ለይታችሁ አመልክቱ፡፡**

| ተ.ቁ | ግስ | ተሻጋሪ | የማይሻገሩ |
|---|---|---|---|
| ሀ | ለመደ | | |
| ለ | መጣች | | |
| ሐ | ተጫወተ | | |
| መ | ረበሻት | | |
| ሠ | በላ | | |
| ረ | ናፈቀች | | |
| ሰ | ተከዘ | | |

## ተግባር 2

**በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ላይ ያሉት ግሶች ተሻጋሪ ወይም የማይሻገሩ መሆናቸውን ለይታችሁ አመልክቱ።**

ምሳሌ፡-

1. አቤል ብርጭቆውን ሰበረው።
   ግሱ - ሰበረው
   የግስ አይነት - ተሻጋሪ ግስ
2. ውሻው ሁልጊዜ ይጮኻል።
   ግሱ - ይጮኻል

   የግሱ አይነት - የማይሻገር ግስ

ሀ. ቤዛ ወንድሟን ገሰጸችው።

ለ. ክብሮም ለወንድሙ ደብዳቤ ጻፈ።

ሐ. ሀውለት በጣም ተደሰተች።

መ. አሜን አባቷን ትወዳለች።

ሠ. ሰብለ እየተቻኮለች መጣች።

ረ. ጎርፍ ሰፈሩን አጥለቀለቀው።

ቀ. ልጅቷ ተከዛለች።

## ተግባር 3

**የሚከተሉት ግሶች ተሻጋሪ ወይም የማይሻገሩ መሆናቸውን ከገለጻችሁ በኋላ ግሶቹን በመጠቀም አረፍተነገሮችን መስርታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡**

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. ደረሰ | ሐ. ለመነች | ሠ. ተደረገ |
| ለ. ያዘ | መ. ገባች | ረ. ገሰገሰ |

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ የተለያዩ የትምህርት ይዘቶችን ተምራችኋል፡፡ ይዘቶቹም ማዳመጥና መናገር፣ ማንበብ፣ ቃላት፣ ጽሕፈትና ሰዋስው ናቸው፡፡

- በሁለት የተለያዩ ነገሮች መካከል ያለውን ተመሳሳይነት ለማሳየት የሚጠቅም የአንቀጽ ማስፋፊያ ስልት ማወዳደር ሲሆን በተመሳሳይ ነገሮች መካከል ያለን ልዩነት ለማሳየት የሚያገለግለው ደግሞ ማነጻጸር ይባላል፡፡
- አንድ ድርጊት ከአንድ አካል ወደ ሌላ አካል መተላለፉን ለማመልከት የሚጠቅም ግስ ተሻጋሪ ግስ ሲባል ድርጊቱ በባለቤቱ የሚያልቅ መሆኑን የሚያመለክት ግስ የማይሻገር ግስ ይባላል፡፡

### የክለሳ ጥያቄዎች

ለሚከተሉት የክለሳ ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡

1. ልዩ ልዩ ይዘት ያላቸውን ጽሑፎች አንብባችሁ ጽሑፎቹ የያዙትን ሀሳብ ለመረዳት ሞክሩ፤ ሀሳቡን መረዳታችሁንም እርስ በእርሳችሁ በመጠያየቅ አረጋግጡ፡፡
2. በፈለጋችሁት ርዕሰ ጉዳይ የሚያተኩር በማወዳደርና ማነጻጸር ስልት አንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡
3. ቀጥሎ የቀረቡትን ግሶች ተሻጋሪ ወይም የማይሻገሩ መሆናቸውን ለይታችሁ አመልክቱ፡፡

| | |
|---|---|
| ሀ. ሰራ | መ. ወረደ |
| ለ. ሰነፈ | ሠ. ጠወለገ |
| ሐ. ተበደለ | ረ. ተሰባሰቡ |

# አማርኛ
## ፭ኛ ክፍል

# ምዕራፍ ዘጠኝ
# ባህላዊ ጨዋታዎች

ከምዕራፉ የሚጠበቅ ውጤት

ይህንን ምዕራፍ ተምራችሁ ከጨረሳችሁ በኋላ፡-

- ባህላዊ ጨዋታዎችን ትጫወታላችሁ፡፡
- የስርዓተ ነጥብን አገባብና ትርጉም ተረድታችሁ ትጠቀማላችሁ፡፡
- ባለብዙ ቀለም ቃላትን ታጣምራላችሁ፡፡
- ደብዳቤ ትጽፋላችሁ ፡፡
- የአሁን ጊዜ ግስን ትጠቀማላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥና መናገር

# ባህላዊ ጨዋታዎችና አጨዋወታቸው



### ቅድመ ማዳማጥ፡-

#### ተግባር

ቀጥሎ በቀረበው ሠንጠረዥ ውስጥ በመጀመሪያ ስለባህላዊ ጨዋታዎች የምታውቋቸውን አስፍሩ፡፡ በመቀጠልም ማወቅ የምትፈልጉትን ጻፉ፡፡ ምንባቡን አዳምጣችሁ ከጨረሳችሁ በኋላ ደግሞ አሁን ያወቃችሁትን መዝግቡ፡፡

| የማውቀው | ማወቅ የምፈልገው | ያወቅሁት |
|---|---|---|
| | | |

## የማዳመጥ ሒደት

### ተግባር

**ቀጥሎ ያለውን ሠንጠረዥ በደብተራችሁ ላይ አዘጋጁ፡፡ ከዚያም መምህራችሁ ባህላዊ ጨዋታዎችና አጨዋወታቸው በሚል ርዕስ የተዘጋጀን አንድ ምንባብ ሲያነቡላችሁ እያዳመጣችሁ ማስታወሻ ያዙ፡፡**

| ኃይልንና ልምምድን የሚጠይቁ ጨዋታዎች | ማሰላሰልንና ቅልጥፍናን የሚጠይቁ ጨዋታዎች | የተፈጥሮ ስጦታን/ ዝንባሌን የሚጠይቁ ጨዋታዎች |
|---|---|---|
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |

## አዳምጦ መረዳት

### ተግባር

**ባዳመጣችሁት ምንባብና ምንባቡን ስታዳምጡ የያዛችሁትን ማስታወሻ መሠረት በማድረግ ለሚከተሉት ጥያቄዎች የቃል ምላሽ ስጡ፡፡**

ሀ. ገበጣ ጨዋታ ከየትኞቹ ባህላዊ ጨዋታዎች ይመደባል?

ለ. ‹‹ኳስ አበደች›› ጨዋታ ምን ጠቀሜታ ያለው ይመስላችኋል?

ሐ. ‹‹ኳስ አበደች›› ጨዋታ ከየትኛው ዘመናዊ ጨዋታ ጋር ይመሳሰላል?

መ. ከወረቀት ወይም ከሌላ ለስላሳ ነገር በማዘጋጀት የ‹‹ኳስ አበደች›› ጨዋታን አጨዋወት በክፍል ውስጥ አሳዩ፡፡

ሠ. በትምህርት ቤት በዕረፍት ሰዓትና በቤታችሁ ጉዳት የማያደርስ ኳስ በመጠቀም ‹‹ኳስ አበደች›› ጨዋታን ተጫወቱ፡፡

ክፍል ሁለት፡- ንባብ

## ባህላዊ የልጆች ጨዋታ



### ቅድመ ንባብ

**ተግባር**

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡**

ሀ. ከላይ በስዕሉ ላይ ያሉት ልጆች የሚጫወቱት ጨዋታ ምን ዓይነት ጨዋታ ነው?

ለ. በአካባቢያችሁና በትምህርት ቤታችሁ የምታውቋቸውን ጨዋታዎች ዘርዝሩ

ሐ. የልጆች ጨዋታ ምን ጠቀሜታ ያለው ይመስላችኋል?

### የንባብ ሒደት

**ተግባር**

**ቀጥሎ የቀረበውን ሠንጠረዥ በደብተራችሁ ላይ አዘጋጁ፡፡ ምንባቡን በለሆሳስ እያነበባችሁ የሚያጋጥሟችሁን አዳዲስ ቃላት መዝግቡ፡፡ ንባባችሁን ስትጨርሱ መምህራችሁን በመጠየቅ የቃላቱን ፍቺ ጻፉ፡፡**

| ቃል | ፍቺ |
| --- | --- |
| | |

## ባህላዊ የልጆች ጨዋታ

በሐገራችን የተለያዩ አካባቢዎች በልጆች የሚዘወተሩ ልዩ ልዩ ባህላዊ ጨዋታዎች አሉ፡፡ ልጆች በቤታቸው፣ በሰፈራቸው፣ በትምህርት ቤታቸው እንዲሁም በገጠራማ አካባቢዎች ከብት በሚያግዱባቸው ቦታዎች በሚፈጥሯቸው አጋጣሚዎች እየተሰበሰቡ እንደየባህላቸው የሚጫወቷቸው ልዩ ልዩ ጨዋታዎች አሏቸው፡፡ ጨዋታዎቹ የራሳቸው ደምብና ስርዓት ያላቸው ናቸው፡፡

አንዳንዶቹ ጨዋታዎች ወንዶችና ሴቶች ልጆች በጋራ የሚጫወቷቸው ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ ለየብቻቸው የሚጫወቷቸው ናቸው፡፡

በአጠቃላይ የልጆች ጨዋታዎች እንደማንኛውም የባህል ዘርፍ ከአንዱ ወደሌላው በማየትና በመስማት ሲተላለፉ የሚኖሩ ናቸው፡፡

ብዙዎቹ የልጆች ጨዋታዎች በግጥምና በዜማ የሚቀርቡ ሲሆኑ አንዳንዶቹ ደግሞ በእንቅስቃሴ የተሞሉ ናቸው፡፡ እንደጨዋታው አይነትና እንደ ልጆቹ እድሜ የተለያዩ መልኮች ቢኖሩትም የልጆች ጨዋታ በአብዛኛው በክዋኔ (በአካል እንቅስቀሴ) የታጀበ ነው፡፡

ልጆች ብዙ ጊዜ የሚጫወቱት በመዝለል፣ በመሮጥ፣ በመቀመጥ፣ በመነሳት፣ እርስ በርስ በመነካካት፣ እጅ ለእጅ በመያያዝ፣ ዓይንን በመጨፈን፣ እጅና እግርን በመዘርጋት፣ ክብ ሰርቶ በመቀመጥ ወይም በመቆም፣ በመስመር በመደርደር፣ በመንበርከክ እና በሌሎችም እንቅስቃሴዎች ነው፡፡

በጨዋታ ጊዜ የሚሏቸውም ዜማዎች ከእንቅስቃሴዎች ጋር በጥምረት የሚሄዱ ናቸው፡፡ በልጆች ጨዋታ ጊዜ የሚዜሙት ግጥሞች አብዛኞቹ አጠር አጠር ያሉና ፍጥነት የሚታይባቸው ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የጨዋታዎቹ ግጥሞች በአብዛኛው ቃላትን፣ ሀረጋትንና አረፍተ ነገሮችን የሚደጋግሙ ሲሆን ጥቂቶቹ ደግሞ ረዘም ረዘም ያሉና የመተረክ ባህሪ ያላቸው ናቸው፡፡ ከአጫጭሮቹ መካከል ‹‹መሀረቤን ያያችሁ›› ‹‹ጉልበቴ በርታ በርታ›› እና ‹‹እንቡሼ ገላ›› የተሰኙትን በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል፡፡ ‹‹ኸረ አምሳለ›› ‹‹መሶበ ወርቁ›› እና ‹‹እቴሜቴ›› ደግሞ ረዘም ካሉት የሚመደቡ ናቸው፡፡

እዚህ ላይ አብሮ መነሳት ያለበት እናቶች ሕፃናት ልጆቻቸውን አባብለው ለማስተኛት የሚጠቀሙበት ዜማና ግጥም ነው፡፡ በቁመታቸው ልክ ተለክቶ ከታች በኩል አንድ ክንድ የሚሆን በቀጭኑ ተተልትሎና በእያንዳንዱ ትልታይ ዛጎል የተባለ የባህር ሼል በታሰረበት ከቆዳ በተሰራ አንቀልባ ሕፃን ታዝላለች እናትየዋ ስትወዛወዝም ሆነ ስትራመድ ዛጎሉ እርስ በርስ እየተጋጨ የሆነ ሥርዓት ያለው የሚመስል ድምፅ ያወጣል፡፡ እናትየዋም በአንድ እጇ የሕፃኑን መቀመጫ እየመታች በልዩ ዜማ ታንጎራጉራለች፡-

> ‹‹እሽሩሩ… ማሙሽ/ሚሚ እሽሩሩ… ማሙሽ/ሚሚ እሽሩሩ
> የማሙሽ/የሚሚ እናት የት ሄዳለች?
> ማርና ወተት ልታመጣ ሄዳለች›› እያለች፡፡

የዜማው ይዘት ሕፃኑን እያባበለ የሚያስተኛ በመሆኑ አፍታ ሳይቆይ ሕጻኑን እንቅልፍ ይወስደዋል፡፡ ከዚያም ወደ ሌላው ሥራዋ ትገባለች፡፡

በሀገራችን በልጆች የሚዘወተሩ ልዩ ልዩ ጨዋታዎች አሉ፡፡ ጨዋታዎቹ ደስታን ከማስገኘታቸውም በላይ ለአካላዊ፣ አዕምሯዊና መንፈሳዊ ዕድገት ከፍ ያለ አስተዋፅዖ አላቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ህጻናት ወግና ባህላቸውን ይዘው እንዲያድጉ ከማድረግ አኳያ የሚሰጡት ጠቀሜታ ላቅ ያለ ነው፡፡ በመሆኑም ከዘመኑ ጋር እንዲዘምኑና እንዲሻሻሉ እየተደረገ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሊተላለፉ ይገባል፡፡ ምንጭ (ዘሪሁን አስፋው፤ 2004፤ የስነጽሁፍ መሰረታውያን፤ ገጽ- 56 ዳብሮ የቀረበ፡፡)

## አንብቦ መረዳት


### ተግባር 1

**ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት በማድረግ በጽሁፍ መልሱ፡፡**

1. ልጆች የት የት ቦታ ሊጫወቱ ይችላሉ?
2. በአካባቢያችሁ የምትጫወቷቸውን ጨዋታዎች እንዴት ለመዳችኋቸው?
3. የልጆች ጨዋታ የሚከናወነው በምን በምን መንገድ ነው?
4. ባህላዊ የልጆች ጨዋታዎች እንዲዘምኑና እንዲሻሻሉ ምን መደረግ አለበት?
5. በአንቀልባ ጫፍ ላይ ዛጎሎች የሚደረጉት ለምንድን ነው?
6. በምንባቡ ከተጠቀሰው ሌላ የምታውቁትን እናቶች ልጆችን ለማባበልና ለማስተኛት የሚጠቀሙበት ዜማና ግጥም ግለጹ፡፡

### ተግባር 2

የሚከተለውን የቢጋር ሠንጠረዥ በምንባቡ መሰረት አሟሉ፡፡



ተግባር 3

**ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በትዕዛዛቸው መሰረት መልሱ፡፡**

ሀ. ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ በምንባቡ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉትን ሥርዓተ ነጥቦችን ሳትደጋግሙ ደብተራችሁ ላይ በመጻፍ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

ለ. በአካባቢያችሁ ከምታውቋቸው ባህላዊ ጨዋታዎች ውስጥ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ለመተግበር የሚመቸውን በመምረጥ ተጫወቱ፡፡

ሐ. ስለአንድ ባህላዊ ጨዋታ መረጃ አሰባስባችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ዘገባ አቅርቡ፡፡

## ክፍል ሶስት፡- ቃላት

ተግባር 1

**ከዚህ በታች በምዕላድ ተነጣጥለው የተጻፉትን ቃላት በደብተራችሁ ላይ እያጣመራችሁ በመጻፍ አንብቡ፡፡**

ምሳሌ፡-

| | |
|---|---|
| እየ-አጨበጨብ-ኣችሁ-ልን | እያጨበጨባችሁልን |
| እንደ-አይ-ጨናገፍ-ብኝ | እንዳይጨናገፍብኝ |

ሀ. በ-ቅብብል-ኦሽ

ለ. አሰ-መዘገብ-ኡ-ኝ

ሐ. ስለ-ቅመም-ኣ-ቅመም

መ. ከ-መማገር-ኢያ-ዎች-ኣችን

ሠ. እንደ-ቢራቢሮ-ዎች

ተግባር 2

**ከዚህ በታች በቀረበው አንቀጽ ውስጥ ያሉትን ክፍት ቦታዎች ቀጥሎ ባለው ሳጥን ውስጥ ከተዘረዘሩት ቃላት በመምረጥ አሟሉ፡፡**

| | | | |
|---|---|---|---|
| ጋደም | አብረሽኝ | ትዝ | ተለይቼ |
| ንፍቅ | በቁልምጫ | በብቸኝነት | |

ሠላምዬ እናቴ እንዴት ነሽልኝ? በጣም__________ብለሽኛል፡፡ ከአንቺ ከውድ እናቴ ከተለየሁ ጀምሮ________እየተሰቃየሁ እገኛለሁ፡፡ እኔ ከአንቺ ________ ምንም ባደርግ እንደማያምርብኝ እና ምንም ማድረግ እንደማልችል ታውቂያለሽ አይደል? ወደ ትምህርት ቤት ስሄድ አንቺ__________ስትሆኚ እንዴት ደስ ይለኝ እንደነበረ______________ ሲለኝ አልቅሽ አልቅሽ ይለኛል፡፡ ሕይወትዬ እያልሽ________________የምትጠሪበት ድምጽሽ ሁሌም ጆሮዬ ላይ ያቃጭልብኛል፡፡ እናቴ አልጋዬ ላይ______ስል እንቅልፍ ይዞኝ ጭልጥ የሚለው እንኳን ስላንቺ ሳስብ ነው፡፡ በአጠቃላይ ምን ያህል እንደናፈቅሽኝ በዚች አጭር ጽሁፍ ለመግለፅ አልችልም፡፡ በቃ! ነይልኝ እናቴ፡፡

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

**ማስታወሻ**

ደብዳቤ ሰዎች ስለግላዊና ቤተሰባዊ ጉዳዮች እንዲሁም ስለስራ ጉዳዮች በጽሁፍ መልዕክት የሚላላኩበት መንገድ ነው፡፡ ደብዳቤ በዋናነት የሰላምታ ደብዳቤና የስራ ደብዳቤ ተብሎ በሁለት ዓይነቶች ሊመደብ ይችላል፡፡ የሠላምታ ደብዳቤ ሶስት ክፍሎች ሲኖሩት እነሱም መግቢያ፣ ሐተታ እና መደምደሚያ ናቸው፡፡

ሀ. የላኪ አድራሻ
ስም
የመኖሪያ/ስራ
ቦታ
የመልዕክት
ሣጥን
ቁጥር
ከተማ
ቀን

ለ. የተቀባይ አድራሻ
ስም
የመኖሪያ/ስራ ቦታ
የመልዕክት ሣጥን ቁጥር
ከተማ

ሐ. መግቢያ ፡-ሠላምታና ወዳጅነትን፣ ጓደኝነትን፣... የሚያመላክቱ አገላለጾች
መ. ሐተታ ፡- በደብዳቤው ሊጠቀሱ የተፈለጉ ዝርዝር ጉዳዮች
ሠ. መደምደሚያ ፡-የመሰናበቻ ቃላትናመልካም ምኞት

ከአሜን ምትኩ

ዳግማዊ ምንሊክ የመጀመሪያ
ደረጃ ት/ቤት
መ.ሣ.ቁ.______

አ.አ.
ቀን

ለያሲን ኢብራሂም
ደብረ ብርሀን ዩንቨርሲቲ
መ.ሣ.ቁ.
ደብረ ብርሀን

ውድ ጓደኛዬ ያሲን በጣም ናፍቀኸኛል፤ ለጤናህ እንደምን አለህልኝ? ፈጣሪ ይመስገን እኔ ደህና ነኝ።

ያሲኖ እኔ ትምህርቴን በሚገባ እየተከታተልኩ ነው። ከጓደኞቼ ጋር በቡድን የማጥናት ልምድ እያዳበርኩ ነው። በዚሁ ዘዴ ሳጠና በመቆየቴ በአንደኛው ወሰነ ትምህርት ከክፍል ጓደኞቼ የሁለተኛ ደረጃን ይዤ በማጠናቀቄ ተሸላሚ ሆኛለሁ። ይህንን ደብዳቤ የጻፍኩልህ ደስታዬን ላካፍልህ ስለፈለግኩ ነው። በሁለተኛው መንፈቀ ዓመት ደግሞ ከዚህ የተሻለ ውጤት በማምጣት የበለጠ እንደማኮራህ ይታየኛል።

አንተስ የዩንቨርሲቲ ትምህርትህን እንዴት ተያይዘኸዋል? የደብረ ብርሀን ብርድስ እንዴት እያደረገህ ነው? መቼም ሁሉንም ነገር ተቋቁመህ በጥሩ ውጤት እንደምትመረቅ ሙሉ እምነት አለኝ። በተረፈ ምንም እንዳታስብ፤ ቤተሰቦችህና የሰፈሩ ሰው በሙሉ ሰላም ናቸው።

በል እንግዲህ ትምህርትህን ጨርሰህ ስትመጣ እስከምንገናኝ ድረስ ደህና ሁን።

ጓደኛህ
ፊርማ
አሜን ምትኩ

## ተግባር 1

**ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በጽሁፍ መልሱ።**

ሀ. በአንድ የሰላምታ ደብዳቤ ላይ በላኪው አድራሻ ላይ የሚገለጹት ምን ምን ናቸው?

ለ. በተቀባይ አድራሻ ላይ ምን ምን ጉዳዮች ይገለጻሉ?

ሐ. የስንብትና የመልካም ምኞት መግለጫ የሚሰፍረው በየትኛው የደብዳቤ ክፍል ነው?

መ. የላኪ አድራሻ የሚጻፈው በደብዳቤ መጻፊያው ወረቀት የትኛው ቦታ ላይ ነው?

ሠ. አንድ የሠላምታ ደብዳቤ ጽፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡ።

## ተግባር 2

**የሚከተሉትን ዐረፍተነገሮች ከቀረቡት ሥርዓተ ነጥቦች በመምረጥ አሟልታችሁ ጻፉ።**

| ፤ | . | ፡ | ? | ( ) |
|---|---|---|---|---|

1. መኪናው ዱቄት_____ ዘይት_____ሳሙና_____እና ልብስ ጭኖ ሄደ።
2. ተማሪዎች መጫወት ያለባቸው መቼ ነው__________
3. ሁል ጊዜ ጠዋት 12______30 ከመኝታዬ የመነሳት ልምድ አለኝ።
4. የእረፍት ጊዜዬን አቅመ ደካሞችን በመርዳት _____በማገዝ_____ ማሳለፍ እርካታ ይሰጠኛል።
5. የአምስተኛ ክፍል ተማሪዎች ለተቸገሩ ወገኖቻችን መርጃ የሚሆን ስምንት መቶ አስራ አምስት ብር ከሰባ አምስት ሣንቲም 815 ____75 ለክፍል ኃላፊ መምህራቸው አስረከቡ።

## ክፍል አምስት፡- ሰዋስው

### ማስታወሻ

**የአሁን ጊዜ ግስ**

ጊዜ አንድ ድርጊት መቼ እንደተፈጸመ ወይም መቼ እንደሚፈጸም የሚገልጽ የግስ ባህሪ ነው፡፡ ጊዜ በሶስት ሊከፈል ይችላል፤ እነሱም፡-

1. የአሁን ጊዜ
2. የሃላፊ ጊዜ
3. የትንቢት ጊዜ ናቸው፡፡

ይህንን ተከትሎ ግሶችም የአሁን ጊዜ ግስ፣ የኃላፊ ጊዜ ግስ እና የትንቢት ጊዜ ግስ በመባል በሶስት ዐበይት ክፍሎች ይመደባሉ፡፡

የአሁን ጊዜ ግስ፡- የሚባለው አንድ በአሁን ጊዜ የሚፈጸም ወይም በመፈፀም ላይ ያለ ድርጊትን ወይም ሁኔታን የሚያመለክት የጊዜ ዓይነት ነው፡፡ የአሁን ጊዜ ግስ "እየ-" የሚል ምዕላድ ሊያስቀድምና "ነው" የሚል ረዳት ግስ ሊያስከትል ይችላል፡፡

ምሳሌ፡-

ተማሪዋ ወደ ትምህርት ቤት እየሄደች ነው፡፡

ልጁ ልብሱን እያጠበ ነው፡፡

ከላይ በሁለቱ ምሳሌዎች ላይ እንደሚታየው "እየሄደች ነው" እና "እያጠበ ነው" የሚሉት የአሁን ጊዜ ግስ ናቸው፡፡ "እየ-" የሚለው ምዕላድ የመሄድና የማጠብ ድርጊቱ ተፈፅሞ ያላለቀና በመካሄድ ላይ ያለ መሆኑን ይጠቁማል፡፡

## ተግባር 1

**ከዚህ ቀጥሎ በቀረቡት ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን ግሶች በምሳሌው መሰረት ወደ አሁን ጊዜ ቀይሯቸው፡፡**

ምሳሌ፡-

ጠርሙሱ ውስጥ ያለው ወተት ቀዝቅዟል፡፡

ጠርሙሱ ውስጥ ያለው ወተት እየቀዘቀዘ ነው፡፡

ሀ. የቤቱ ዋልታ በስብሷል፡፡

ለ. ፈረስ መጋለብ ለምዷል፡፡

ሐ. የወተት ማጠራቀሚያው እንስራ በወይራ ታጥኖ ነበር፡፡

መ. በዛብህ ፍቅር እስከ መቃብር የሚባለውን ልቦለድ መጽሐፍ አንብቧል፡፡

ሠ. ልጆቹ በመስኩ ላይ ገና ተጫውተዋል፡፡

## ተግባር 2

**ከዚህ በታች የቀረቡትን ግሶች በምሳሌው መሰረት ወደ አሁን ጊዜ በመቀየር ዐረፍተ ነገር መስርቱባቸው፡፡**

ምሳሌ፡-

1. አገዘ — ሱለይማን ወላጆቹን በስራ <u>እያገዘ ነው፡፡</u>
2. ተጫወተች — ማስተዋል ከጓደኞቿ ጋር እግር ኳስ <u>እየተጫወተች ነው፡፡</u>

ሀ. ደረቀ

ለ. ተማሩ

ሐ. ጠጡ

መ. ኮተኮተች

ሠ. ዘመሩ

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ የተለያዩ የትምህርት ይዘቶችን ተምራችኋል፡፡ ይዘቶቹም ማዳመጥና መናገር፣ ንባብ፣ ቃላት፣ ጽሕፈትና ሰዋስው ናቸው፡፡

- ምንባብን አቀላጥፎ ለማንበብ ውስብስብ ቃላትን ነጣጥሎና አጣምሮ በማንበብ መለማመድ ተገቢ ነው፡፡ ቃላትን ነጥለንና አጣምረን ስናነብም ትክክለኛውን የምዕላድ አከፋፈል ስርዓት ተከትለን መሆን አለበት፡፡
- ስርዓተ ነጥቦች በጽሑፍ የሚተላለፍን ሀሳብ ግልጽ ለማድረግ የሚጠቅሙ ምልክቶች ሲሆኑ በትክክለኛው አጠቃቀማቸው በመጠቀም ሀሳባችንን የተሟላ ያደርጉታል፡፡
- ከመልእክት መለዋወጫ መንገዶች አንዱ ደብዳቤ ሲሆን የሠላምታ ደብዳቤ ሶስት ዋና ዋና ክፍሎችን ይይዛል፡፡ እነሱም መግቢያ፣ ሐተታ እና መደምደሚያ ናቸው፡፡
- በዓረፍነገር ውስጥ የሚገኝ ግስ ድርጊቱ (ሁነቱ) የተከሰተበትን ጊዜ ያመለክታል፡፡ ከግስ ጊዜዎች ውስጥ አንዱ ተናጋሪው በሚናገርበት ጊዜ እየተከናወነ ያለን ተግባር የሚገልጸው የአሁን ጊዜ ነው፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

**ለሚከተሉት የክለሳ ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡**

1. የሚከተሉትን ቃላት ነጣጥላችሁ አንብቡ፡፡

ሀ. ተውለብላቢዎቹ

ሐ. በሰላማዊነታችን

ለ. ስለእርሻችሁ

መ. እያስተሳሰረች

2. ቀጥሎ ተነጣጥለው የቀረቡትን ቃላት አጣምራችሁ አንብቡ

ሀ. የ-ተማሪ-ዎች-ኡ

ለ. ስለ-መንፈስ-ኣዊ-ነት-ኣችን

ሐ. መንከባከብ-ኣችሁ-ን

መ. ከ-ልምድ-ኦች-ኡ

3. በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ የተጓደሉትን የስርዓተ ነጥብ አይነቶች በማስገባት ዓረፍተነገሮቹ ሙሉ ሀሳብ እንዲያስተላልፉ አድርጓቸው፡፡

ሀ. ለምለም የተወለደችው በስንት ዓ ም ነው

ለ. የትምህርት ቤታችን የእግር ኳስ ሜዳ ሳር ተተከለበት

ሐ. ለገና ጨዋታ ከሚያስፈልጉ ነገሮች መካከል ጥንግ ቁልፍ ዱላ ሩር እና መጫዎቻ ሜዳ ዋና ዋናዎቹ ናቸው

4. በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን ግሶች ወደ አሁን ጊዜ ቀይሯቸው፡፡

ሀ. ተማሪዎች ከትምህርት ቤት በታክሲ <u>ይመለሳሉ</u>፡፡

ለ. የሰፈሩ ሰላም <u>ተጠብቋል</u>፡፡

ሐ. መልካሙ ጓደኛው ሲናገር በጥሞና <u>አዳምጧል</u>፡፡

መ. የውሃ ማጠራቀሚያ ጋኑ <u>ተሞልቷል</u>፡፡

# አማርኛ
## ፭ኛ ክፍል

# ምዕራፍ አስር
# ስነቃል


ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- ስነቃሎችን አዳምጣችሁ ምላሽ ትሰጣላችሁ፡፡
- ራሳችሁን መግለጽ ትለማመዳላችሁ፡፡
- አፈታሪክን በማንበብ ታሪኩን ትገልጻላችሁ፡፡
- የራሳችሁን ህይወት ታሪክ ትጽፋላችሁ፡፡
- የስነጽሁፍ አላባውያንን ትገልጻላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥና መናገር

# ዕንቆቅልሽ



### ቅድመ ማዳማጥ፡-

#### ተግባር

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች የቃል ምላሽ ሰጡ፡፡**

ሀ. ዕንቆቅልሽ ተጫውታችሁ ታውቃላችሁ? ተጫውታችሁ የምታውቁ ከሆነ ስለአጨዋወቱ የምታውቁትን ነገር ተናገሩ፡፡

ለ. ስነቃል ሲባል ምን ማለት ይመስላችኋል?

### የማዳመጥ ሒደት

#### ተግባር

**መምህራችሁ ዕንቆቅልሽ በሚል ርዕስ የሚያነቡላችሁን ምንባብ አዳምጡ፡፡ በየመሀሉ ለሚጠይቋችሁ እንቆቅልሾችም የእንቆቅልሽ አጨዋወት ስርዓትን ተከትላችሁ ምላሽ ስጡ፡፡**

## አዳምጦ መረዳት

### ተግባር 1

**ያዳመጣችሁትን ምንባብ መሠረት በማድረግ ለሚከተሉት ጥያቄዎች የቃል ምላሽ ስጡ፡፡**

ሀ. "ዕንቆቅልሽ" የሚለው ቃል ከምን ቋንቋ የተገኘ ነው?

ለ. ‹‹ዕንቆቅልሽ እንደእንቁላል ድፍን የሆነ ነው›› ሲባል ምን ማለት ነው?

ሐ. ዕንቆቅልሽ ምን ዓይነት ችሎታን የሚጠይቅ ጨዋታ ነው?

መ. መልሱን ያላወቀ የዕንቆቅልሽ ተጫዋች ምን ያደርጋል?

ሠ. ‹‹መሸብህ፤ ዕንቆቅልሼ ጠነዛብህ፤ ዋለብህ አደረብህ›› የሚለው አባባል ምንን ያመለክታል?

ረ. የዕንቆቅልሽ ተጠያቂው መልሱን ማወቅ የሚጠበቅበት በምን ያህል ጊዜ ውስጥ ይመስላችኋል?

### ተግባር 2

**የሚከተሉትን ተግባራት ጥንድ ጥንድ በመሆን ተግባሩ፡፡**

ሀ. ዕንቆቅልሽ ተጠያየቁ፡፡

ለ. መምህራችሁ በሚያሳይዋችሁ መሰረት ስለራሳችሁ ለጓደኛችሁ ግለጹ፡፡

## ክፍል ሁለት፡- ንባብ

### ተረት



ተግባር 1

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡**

ሀ. ከላይ የቀረበው ስዕል ምን ያሳያል?

ለ. ተረት መናገር ስትጀምሩና ተናግራችሁ ስትጨርሱ ምን ትላላችሁ?

ሐ. ተረት ለልጆች  ምን ጠቀሜታ ያለው ይመስላችኋል?

## የንባብ ሒደት

ተግባር

**ቀጥሎ የቀረበውን ሠንጠረዥ በደብተራችሁ ላይ አዘጋጁና ምንባቡን በለሆሳስ እያነበባችሁ አሟሉ፡፡**

| ጥያቄ | ምላሽ |
|---|---|
| 1. ተረቱ ውስጥ ያሉትን ባለታሪኮች ግለጹ፡፡ | |
| 2. ታሪኩ የተፈጸመበት የት ነው? | |
| 3. እናቲቱንና ልጂቱን ያጋጫቸው ጉዳይ ምንድን ነው? | |
| 4. በታሪኩ መጨረሻ ምን ተከሰተ? | |

## ተረት

ስነ ቃል በቃል ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ የቆየ ቃላዊ ስነጽሁፍ ነው ሥነ ቃል ልዩ ልዩ ቃላዊ ፈጠራዎችን አካትቶ የሚይዝ የሥነ ጽሁፍ ዓይነት ነው፡፡ በሥነቃል ስር ከሚገኙት መካከል ተረት፣ ዕንቆቅልሽ፣ እንካሰላንቲያና ምሳሌያዊ አነጋገሮች ይገኛሉ፡፡

ተረት እንደጉዳዩ ሁኔታ በሰውና በልዩ ልዩ እንስሳት እየተመሰለ የሚነገር ልብ ወለድ ታሪክ ነው፡፡ ተረት ሕጻናትን የማር፣ የወተትና የስኳር ያህል ስለሚያረካቸው ተረት በሚነገርበት ጊዜ ከስር ጀምረው በፈገግታና በደስታ ያዳምጣሉ፡፡ በዚህም ልጆች ደስታንና እርካታን ያገኛሉ፡፡

ተረት አነጋገሩ እንደቧልት ዓይነት ሆኖ የሚያስቅ፣ የሚያስለቅስ፣ የሚያስገርምና የሚያስደንቅ ቢሆንም መነሻና መድረሻ ያለው ሙሉ ታሪክን የያዘ ነው፡፡ ከውስጡም ትምህርት የሚሆን ጠቃሚ ተግሳፅና ምክር ይገኝበታል፡፡ የሀገራችን አዛውንት፣ አባቶችና እናቶች ማታ ማታ ለሕፃናት ልዩ ልዩ የሆኑ ተረቶችን ማሰማት ልማዳቸው ነው፡፡ እንዲያውም ሕጻናትን ወደ አረጋዊያን ከሚያቀርቧቸውና ከሚስቧቸው ነገሮች ውስጥ ተረት በዋነኛነት ይጠቀሳል፡፡

ተረት በአብዛኛው በቃል የሚወረስ እንጂ በመጽሐፍ መልክ ተዘጋጅቶ የምናገኘው ስላልሆነ ከቦታ ቦታ አነጋገሩ ሊለዋወጥ ይችላል፡፡ ተረት ለልጆች ደግነትን፣ ሩኅሩኅነትንና ታዛዥነትን ለማስተማር፤ ለመገሰጽና ጠቃሚ ምክሮችን ለመስጠት፤ በአጭሩ ግብረ ገብነትን ለማስለመድ ተፈላጊነት አለው፡፡ እስኪ ለምሳሌ ያህል የሚከተለውን ተረት እንመልከት፡፡

ተረት ተረት!

አንዲት የቆቅ ልጅ የደረሰ የስንዴ እሸት በሚገኝበት እርሻ አጠገብ ወጥመድ ተጠምዶ አይታ እናቷን ‹‹እናቴዋ እሸት አምሮኝ ነበር፤ ይሁን እንጂ ወደዚህ ማሳ ገብቼ እንዳልበላ በወጥመዱ እንዳልያዝ ፈራሁ፤ ምን ይሻለኛል?›› አለቻት፡፡

እናቷም ‹‹ተይ ልጄ ይቅርብሽ፤ ትያዣለሽ፤ አይሆንም›› ብላ መከረቻት፡፡ ልጅየዋ ግን ‹‹ግድ የለሽም፤ አይዘኝም፤ ትንሽ ተክ! ተክ! አድርጌ ልውጣ›› አለችና፣ ወደ ስንዴው ማሳ ዘው ብላ ስትገባ ወጥመዱ እግሯን ጥርቅም አድርጎ ያዛት፡፡ መቼም መከራ በመጣብን ጊዜ በመጀመሪያ የሚታሰቡን ወላጆች ስለሆኑ ያች የእናቷን ምክር አልሰማም ያለችው ትንሽዬ ቆቅ ‹‹እናቴ ኧረ ተያዝኩልሽ! ድረሽልኝ!›› አለች፡፡ እናትዬዋም ‹‹ምነው ልጄ አስቀድሜ መክሬሽ አልነበረምን! አሁን ታዲያ ምን ላደርግልሽ እችላለሁ?” ብላ መለሰችላት፡፡

‹‹እማምዬ እባክሽ ፍቺልኝ?››

‹‹በምን እጄ?››

‹‹ታዲያ እንዴት ልሁን ምን ይበጀኝ የኔ እናት?››

በዚህ ጊዜ እናት ለልጅዋ ምን ጊዜም ምክር ዐዋቂ ናትና፤ ‹‹ዝም ብለሽ የሞትሽ መስለሽ ተኚ፡፡ ባለወጥመዱ ሲመጣ ሞታለች ብሎ ፈትቶ ይወረውርሻል፤ ያን ጊዜ ታመልጫለሽ›› አለቻት፡፡

የእርሻው ባለቤት የስንዴውን ማሳ እየተዟዟረ ሲጎበኝ ወጥመዱ ቆቅ ይዞለት ስለተመለከተ ደስ ብሎት ሲጠጋ ቆቋ ዝልፍልፍ ብላ ዓይኗን ጨፍና ስላገኛት የሞተች መስሎት አዘነ፡፡

ከዚያም ገበሬው ማዶ የሚገኘውን ጓደኛውን ተጣርቶ ‹‹ጓዴ! ወጥመዴ ቆቅ ይዞልኝ ነበር፤ ነገር ግን በክታ አገኘኋት›› አለው፡፡

ጓደኛውም ‹‹እስኪ ወደላይ አጉናትና አሳየኝ›› አለው፡፡

ገበሬውም ጓደኛው እንዳለው ‹‹እያት!›› ብሎ ቆቋን ወደሰማይ ውርውር ሲያደርጋት ‹‹ቱርርር...›› ብላ ጫካ ውስጥ ገብታ አመለጠች ይባላል፡፡

‹‹ተረቴን መልሱ አፌን በዳቦ አብሱ››

የአባቶችና የእናቶችን እንዲሁም የሽማግሎችንና የታላላቆቻችሁን ምክር መቀበልና ማክበር ይገባል፡፡ ከእነሱ ፈቃድ ውጪ መውጣት ግን አደጋ ላይ ይጥላል፡፡ በተጨማሪም በምንሰራው ስራ ሁሉ ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል፡፡ ችግር በሚያጋጥመን ጊዜም ብልሀተኛና ትግስተኛ መሆን አለብን፡፡

ከላይ ለአብነት ከቀረበው ተረት ለመረዳት እንደሚቻለው ተረት ህጻናትን እያዝናና በሰነ ምግባር ወይም ግብረ ገብነት አንፃ ለማሳደግ ሲባል እየተፈጠረ በልዩ ልዩ መንገድ የሚነገር የስነቃል ዘርፍ ነው፡፡

(የብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ ወ/መስቀል ስብስብ ሥራዎች 2007 ዓ.ም፤ገጽ- 29-30፣ ተሻሽሎ የተወሰደ፡፡)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር 1

**ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት በማድረግ በቃል መልሱ፡፡**

ሀ. ትንሽየዋ ቆቅ ‹‹ተክ ተክ አድርጌ ልውጣ›› ስትል ምን ማለቷ ነው?

ለ. ተረት ህጻናትንና አዋቂ ሰዎችን የሚያቀራርበው እንዴት ነው?

ሐ. እናንተ ትንሽየዋን ቆቅ ብትሆኑ ኖሮ ምን ታደርጉ ነበር?

መ. የተረት አነጋገሩ ከቦታ ቦታ የሚለዋወጠው ለምንድን ነው?

ሠ. ተረት ህጻናትን በስነ ምግባር ወይም በግብረ ገብነት አንፃ የሚያሳድገው እንዴት ነው?

ረ. ከተረቱ ምን መልካም ነገር ተማራችሁ?


ሰ. በምንባቡ ውስጥ ከተጠቀሱት ሌላ የምታውቋቸውን የስነቃል ዓይነቶች ተናገሩ፡፡

ሸ. እንካሰላንቲያ ምን ዓይነት ጨዋታ ነው?

ቀ. ጥንድ ጥንድ በመሆን ተራ በተራ በምንባቡ ውስጥ ያለውን ተረት ተናገሩ፡፡

## ተግባር 2

**ከታች የቀረቡትን የስነጽሁፍ አላባውያን መሰረት በማድረግ መምህራችሁ ስለአላባዊያኑ የሚሰጧችሁን አጭር ገለፃ ማስታዎሻ እየያዛችሁ በጥሞና ካዳመጣችሁ በኋላ ከታች የቀረበውን የማዛመድ ጥያቄ በደብተራችሁ ላይ ስሩ፡፡**




| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ገጸባህሪ | ሀ. በባለታሪኮቹ መካከል የሚፈጠር አለመግባባት |
| 2. መቼት | ለ. በታሪኩ አማካኝነት የሚተላለፈው ፍሬ ነገር |
| 3. ግጭት | ሐ. የታሪኩ ድርጊቶች የመንስዔና ውጤት ሠንሰለት |
| 4. ጭብጥ | መ. አንድን ታሪክ በጊዜ እና በድርጊት ቅደምተከተል የሚያስቀምጥ |
| 5. ትልም | ሠ. ታሪኩ የተፈፀመበት ጊዜና ቦታ |
| 6 አንፃር | ረ. ደራሲው ታሪኩን የተረከበት አኳያ |
| 7. ታሪክ | ሰ. ባለታሪክ |

ማስታወሻ

አፈ ታሪክ

አፈ ታሪክ ባለፈ ታሪክ ላይ ተመስርቶ የሚነገር ሲሆን በአብዛኛው በአንድ በተወሰነ አካባቢ ከተፈጸመ እውነተኛ ታሪክ አንድ ገጽታ በመውሰድ ስነ ቃላዊ ፈጠራ ተጨምሮበት የሚወሰድ ነው፡፡ የአፈ ታሪክ ዓላማም አሳሳቢ ጥያቄዎችን ለመመለስ ነው፡፡ የአንድን አፈ ታሪክ ምስጢር ለመረዳት የፈለቀበትን ህዝብ ባህል፣ አጠቃላይ የአኗኗር ዘይቤና እምነትን በውል ማወቅ ያሻል፡፡

## ተግባር 3

**ቀጥሎ የቀረበውን አፈ ታሪክ በጥሞና ካነበባችሁ በኋላ ሀሳቡን በራሳችሁ አገላለጽ በአጭሩ ግለጹ፡፡**

በአጼ ምኒሊክ ዘመን የአራዳ ዘበኞች የአራዳን (የአሁኑ ፒያሳን) አካባቢ ብቻ ይጠብቁ በነበረበት ወቅት ይህ ሰፈር ጫካና በርከት ያሉ ሴቶች ይኖሩበት ነበር፡፡ ፡፡እነኝህ ብቻ ሳይሆኑ መሸት ሲል የዘረፋ ተግባር የሚያኪያሂዱ ማጅራት መቺዎች በጫካው ውስጥ ይገኙበት ነበር፡፡

ታዲያ አንድ ወንድ አንዷ ቤት ገብቶ ረብሻ ቢያስነሳ አንዷ ዱላዋን፣ ሌላዋ ዘነዘናዋን የያዙትን ይዘው ይደበድቡታል፡፡ በተጨማም ማጅራት መቺዎችም አላፊ አግዳሚውን እየያዙ የአካል ጉዳት አድርሰው ገንዘብ ያለውን ገንዘቡን፣ የሌለውን ልብሱን እና ጫማውን ይዘርፋታል፡፡

ተጠቂው ሰው ቢጮህ አንድም ሰው ዝር አይልም፡፡ ሊሞክር የሚቃጣው የአራዳ ዘበኛም ቢኖር በዚያው ይቀራል፡፡ በዚህ የተነሳ አካባቢው እሪ በከንቱ ተባለ፡፡

## ክፍል ሶስት፡- ቃላት

### ተግባር 1

**ከዚህ በታች ያለውን ሠንጠረዥ ደብተራችሁ ላይ በማዘጋጀት ተነጣጥለው የተጻፉትን ቃላት እያጣመራችሁ በመጻፍ አንብቡ፡፡**

| | ቃሉ ተነጣጥሎ ሲጻፍና ሲነበብ | ቃሉ ተጣምሮ ሲጻፍና ሲነብ |
|---|---|---|
| ምሳሌ | ኢትዮጵያ - ኣዊ- ነት- ኣችን | ኢትዮጵያዊነታችን |
| ሀ | ስለ - ሄደ - ች | |
| ለ | ጫማ - ዎች - ኣችን | |
| ሐ | ሸማግሌ - ዎች - ኡ - ን | |
| መ | ዘመን - ኣዊ - ነት - ሽ - ን | |
| ሠ | አድናቂ - ዎች - ኣችን - ን | |
| ረ | የ - ተ - መለሰ -ው | |

### ተግባር 2

**ከዚህ በታች ያለውን ሠንጠረዥ ደብተራችሁ ላይ በማዘጋጀት ተጣምረው የተጻፉትን ቃላት ነጣጥላችሁ በመጻፍ አንብቡ፡፡**


| | ቃሉ ተጣምሮ ሲጻፍና ሲነበብ | ቃሉ ተነጣጥሎ ሲጻፍና ሲነበብ |
|---|---|---|
| ምሳሌ | የአበባዎቹን | የ- አበባ- ዎች-ኡ-ን |
| ሀ | ከቤታችን | |
| ለ | እንደመጣሽ | |
| ሐ | በዕውቀትህ | |
| መ | አስተማሪው | |
| ሠ | ለጓደኞቼ | |
| ረ | ስለጎረቤቶቻችን | |

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

# የሕይወት ታሪክ መጻፍ

**ማስታወሻ**

የሕይወት ታሪክ ስለአንድ ሰው ሕይወት በአጭሩ የሚተርክ እና በተራኪ የድርሰት አይነት ውስጥ በምሳሌነት የሚጠቀስ ነው፡፡ የአንድን ሰው የሕይወት ታሪክ ራሱ ባለታሪኩ ወይም ሌላ ሰው ሊጽፈው ይችላል፡፡ በሕይወት ታሪክ ውስጥ የሚከተሉት ዋና ዋና ጉዳዮች በአጭር በአጭሩ ይተረካሉ፡፡



## የሕይወት ታሪክ አጻጻፍ ናሙና ቅርጽ

አቶ----------ከአባቱ ከ------------- እና ከእናቱ ከ--------- በ--------ዓ.ም. --------- በተባለ ቦታ ተወለደ፡፡

በልጅነቱ ----------------፣ -----------------፣ ---------------፣ ---------------- እና --------------- እያደረገ አደገ፡፡

እድሜው ለትምህርት ሲደርስ --------------- በተባለ ትምህርት ቤት ትምህርት ጀመረ፡፡ የጀመረውን ትምህርት እስከ ---------- ድረስ በመማር በ---------- ዓ.ም. አጠናቀቀ፡፡

በ----------- ዓ.ም ወደ ስራ ዓለም ተቀላቀለ፡፡ በ-------- ዓ.ም ትዳር መስርቶ ከባለቤቱ -------- ሴትና ------- ወንድ ልጆችን አፈራ፡፡

አቶ----------- በስራ ዘመኑ ----------------------------፣ ---------------------------፣ ------------------------------ እና --------------------- የመሳሰሉ ተግባራትን ለሀገሩና ለወገኑ አከናውኗል፡፡

አቶ------------- በሕይወት ዘመኑ ካጋጠሙት ገጠመኞች -------------------------------- በአሳዛኝነቱ የሚጠቀስ ሲሆን -------------------------------------ደግሞ በአስደሳችነቱ ይጠቀሳል፡፡

አቶ---------------- በአሁኑ ጊዜ ------------ በሚባል ቦታ ይኖራል

ወይም

አቶ--------------- በ------- ዓ.ም. ባደረበት ህመም / ባጋጠመው ድንገተኛ አደጋ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል፡፡

## ተግባር

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከላይ የቀረበውን ማስታወሻና ምሳሌ በመመርኮዝ እንዲሁም መምህራችሁ የሚሰጧችሁን መመሪያ በመከተል በጽሑፍ መልስ ስጡ።**

ሀ. የራሳችሁን የሕይወት ታሪክ ከአንድ ገጽ ባልበለጠ በደብተራችሁ ላይ ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።

ለ. ከቤተሰቦቻችሁ መካከል የአንዱን የሕይወት ታሪክ በመጻፍ ለመምህራችሁ አሳዩ።

## ክፍል አምስት፡- ሰዋስው

### ተሳቢ

#### ርቱዕ እና ኢ-ርቱዕ ተሳቢን መለየት

አንድ ዓረፍተ ነገር ሁለት ዋና ዋና ተዋቃሪዎች አሉት። እነሱም ባለቤትና ማሰሪያ አንቀጽ ናቸው። ከእነዚህ በተጨማሪ እንደማሰሪያ አንቀጹ ባህሪ፣ ተሳቢና ሌሎች ተዋቃሪዎችን ሊያካትት ይችላል።

ባለቤት፡- በአንድ ዓረፍተ ነገር ውስጥ ድርጊት የፈጸመው አካል ነው።

ተሳቢ፡- በአንድ ዓረፍተነገር ውስጥ ድርጊት ተቀባዩ አካል ነው።

አንድ ዓረፍተነገር ሁለት ተሳቢዎች ሊኖሩት ይችላል። እነሱም ርቱዕ (ቀጥተኛ) ተሳቢ እና ኢ-ርቱዕ (ኢ-ቀጥተኛ ተሳቢ) ናቸው።

**ርቱዕ ተሳቢ፡-** በዓረፍተነገሩ የተከናወነው ድርጊት በቀጥታ የሚያርፍበት አካል ነው። ቀጥተኛ ተሳቢን ለማወቅ ‹‹ማንን/ ምንን?›› ብለን እንጠይቃለን።

ምሳሌ፡-

አልማዝ መጽሐፍ ገዛች።( ምን ገዛች?)

በዚህ ዓረፍተ ነገር ውስጥ ‹‹መጽሐፍ›› የሚለው ቃል ቀጥተኛ ተሳቢ ነው።

**ኢ-ርቱዕ ተሳቢ፡-** በዓረፍነገሩ የተከናወነው ድርጊት በተዘዋዋሪ ድርጊቱ የሚያርፍበት አካል ነው። ኢ-ቀጥተኛ ተሳቢን ለማወቅ ‹‹ለማን?›› ብለን እንጠይቃለን።

ምሳሌ፡- አልማዝ ለወንድሟ መጽሐፍ ገዛች። (ለማን ገዛች?)

በዚህ ዓረፍተነገር ‹‹ወንድሟ›› የሚለው ቃል ኢ-ቀጥተኛ ተሳቢ ነው።

## ተግባር 1

**ከዚህ ቀጥሎ በቀረቡት ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ የሚገኙትን ተሳቢዎች ርቱዕ ተሳቢ እና ኢ-ርቱዕ ተሳቢ በማለት ለዩ።**

| ተ.ቁ | የተሰጠ ዐረፍተ ነገር | ርቱዕ ተሳቢ | ኢ-ርቱዕ ተሳቢ |
|---|---|---|---|
| ምሳሌ | መምህሩ ለተማሪው መጽሐፍ ሸለመው። | መጽሐፍ | ተማሪው |
| ሀ | ጀማል ለጓደኛው ሠላምታ አቀረበ። | | |
| ለ | ወፏ ለጫጩቶቿ ምግብ አመጣች። | | |
| ሐ | ዓይናለም ለሰሚራ ስጦታ አበረከተች። | | |
| መ | የአካባቢው ኗሪ ለልማት ገንዘብ አዋጣ። | | |
| ሠ | ራሔል ኳሷን ለፊይሰል አቀበለች። | | |

## ተግባር 2

**ከዚህ በታች የቀረቡትን ግሶች በመጠቀም በምሳሌው መሠረት ቀጥተኛና ኢ-ቀጥተኛ ተሳቢ ያላቸው ዐረፍተ ነገሮች መስርቱ።**

ምሳሌ፡-

1. ሰለሞን ባረጋ በ10000 ሜ. ሩጫ ለኢትዮጵያ ወርቅ አመጣ።

   ቀጥተኛ ተሳቢ፡ ወርቅ ኢ-ቀጥተኛ ተሳቢ፡ ለኢትዮጵያ

ሀ. ገዛ

ለ. ቆረጠ

ሐ. አጨደች

መ. ጋገረ

ሠ. አፈላ

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ የተለያዩ የትምህርት ይዘቶችን ተምራችኋል:: ይዘቶቹም ማዳመጥና መናገር፣ ንባብ፣ ቃላት፣ ጽሕፈትና ሰዋስው ናቸው::

- ስነ ቃል በርካታ ጠቀሜታዎች ሲኖሩት አንዱ የስነ ቃል አይነት የሆነው እንቆቅልሽ የልጆችን አዕምሮ ለማስላትና አካባቢያቸውን እንዲያውቁ ያደርጋል::
- ተረት ለልጆች በመዝናኛነት ከማገልገሉም በተጨማሪ ልጆች በመልካም ስነ ምግባር ታንጸው እንዲያድጉ ጉልህ ሚና አለው::
- ቃላትን ነጣጥሎና አጣምሮ የማንበበ ልምምድ ማድረግ የንባብ ፍጥነትን ከመጨመሩም በተጨማሪ አንብቦ ለመረዳት አስተዋጽኦ አለው::
- የሕይወት ታሪክ አንድ ግለሰብ በሕይወት ዘመኑ ያሳለፋቸውን ነገሮች ከውልደቱ ጀምሮ አሁን እስካለበት ድረስ ታሪኮችን የሚተርክ ፅሁፍ ነው::
- በዓረፍተነገር ድርጊቱ የሚያርፍበት አካል ተሳቢ ይባላል:: ድርጊቱ በቀጥታ የሚያርፍበት አካል ቀጥተኛ ተሳቢ ሲባል ድርጊቱ በቀጥታ የማይርፍበት ድርጊት ተቀባይ ደግሞ ኢ-ቀጥተኛ ተሳቢ ይባላል::

## የክለሳ ጥያቄዎች

**ለሚከተሉት የክለሳ ጥያቄዎች መልስ ስጡ::**

1. ስነ ቃል ምንድን ነው?
2. ስነቃል ተብለው የሚታወቁት ምን ምን ናቸው?
3. ተረት ከዕንቆቅልሽ በምን ይለያል?
4. የልቦለድ አላባውያን የሚባሉትን ዘርዝሩ::
5. መሰብሰባችንን የሚለውን ቃል ነጣጥላችሁ በመጻፍ አንብቡ::
6. መኮንን ለወንድሙ ብርቱካን አካፈለ:: በዚህ ዐረፍተ ነገር ውስጥ ያሉት ርቱዕ ተሳቢና ኢ-ርቱዕ ተሳቢ ለዩ::
7. የአንድን ታዋቂ ኢትዮጵያዊ የሕይወት ታሪክ በአጭሩ ጽፉችሁ፣ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡ::

## ሙዳዬ ቃላት

| ቃላት | ፍቺ |
|---|---|
| መስህብ | ሳቢ፣ ማራኪ |
| መታከት | መድከም፣ መዛል፣ መስነፍ፣ መሰልቸት |
| መክሳት | ክብደት መቀነስ፣ መቅጠን፣ መመንመን፣ መሞገግ |
| ማሳ | ተደጋግሞ የታረሰ መሬት |
| ማብረጃ | ማቀዝቀዣ፣ ማስታገሻ፣ እንደ ጠላ የመሳሰሉ መጠጦችን ቀንሶ ማቅረቢያ |
| ማገገሚያ | ከአንድ ህመም ለመዳን የተለያዩ እንክብካቤዎችና ክትትሎች የሚሰጡበት የህክምና ማዕከል |
| ምጣኔ ሀብት | የአንድ ሀገር ጠቅላላ ሀብትና እንቅስቃሴው |
| ረግረግ | ውሃ አካባቢ |
| ቅጫም | ንጽሕናን ካለመጠበቅ በጸጉር ወይም በልብስ ላይ የሚፈጠር ተባይ |
| ባልጩት | ስለት ያለው ድንጋይ |
| ብዝኃ ሕይወት | በየትኛውም ስርዓተ ምኅዳር በሚገኙ ሕይወት ባላቸው ነገሮች መካከል መለያየት |
| ታደገ | አዳነ፣ አተረፈ፣ ከችግር አወጣ |
| ንጥረ ነገር | ከአንድ አይነት አቶም የተሰራና ወደ አነስተኛ ንዑስ ክፍሎች ሊከፋፈል የማይችል ቁስ |
| አማተረ | ተመለከተ፣ አካባቢውን ቃኘ |

| | |
|---|---|
| አርአያ | ምሳሌ፣ አምሳል፣ አብነት |
| አንቀልባ | ከተለፋ ቆዳ የሚሰራ፣ ለሕጻናት ማዘያ የሚሆን ስስና ለስላሳ ቆዳ |
| አጀብ | አንድን ሰው የማጀብ ስነ ስርዓት፣ መደነቅ፣ ግሩም ማለት፣ አየ ጉድ ማለት |
| አጸፋ | ለአንድ ተግባር የሚሰጥ ምላሽ |
| እልህ | ሞገድ፣ ድፍረት፣ ጭከና |
| እልፍኝ | ከዋናው ቤት ጀርባ የሚሰራ አነስ ያለ ቤት |
| ከተሜ | ከተማ አካባቢ የሚኖር ሰው |
| ክዋኔ | አንድን ድርጊት በአካል እንቅስቃሴ በመታገዝ መተግበር ወይም ማከናወን |
| ውዥምብር | ግራ መጋባት፣ ትርምስምስ፣ ግልጽ ያልሆነ ሁኔታ |
| ዛጎል | በባህር ውስጥ እና በምድር ላይ የሚኖሩ እንደ ኤሊ ያሉ ፍጥረታት ልብስ፣ ደረቅ፣ ጠንካራ |
| የብስ | በውሃ ያልተሸፈነ ወይም ደረቅ መሬት |
| ጀምበር | ጸሐይ |
| ጅረት | ወራጅ ውሃ |
| ግብረ ገብ | ምግባረ መልካም፣ እውነተኛ፣ ደግ |
| ግዳይ | ታድኖ የተገደለ የዱር እንስሳ በድን |

# ዋቢዎች


ማኅተመ ስላሴ ወልደ መስቀል፡፡(2007)፡፡የብላቴን ጌታ ማኅተመ ስላሴ ወልደ መስቀል ስብስብ ስራዎች፡፡ (ማተሚያ ቤት ያልተገለጸ)፡፡

ሰለሞን ሀለፎም ፡፡(1997)፡፡ የድርሰት አጻጻፍ፡፡ አዲስ አበባ፣ብራና ማተሚያ ቤት፡፡

በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ባህልና ቱሪዝም ቢሮ፡፡(2006)፡፡ የአፋር ባህላዊ እሴቶች፡፡ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

በጋሻው፡፡(2012)፡፡ ውፍረት (ያልታተመ)፡፡

ባዩ ይማም፡፡(2002)፡፡ አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው፡፡ አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች፡፡

ታሪኩ ፋንታዬ፡፡(2008)፡፡ አማርኛ ሁሉ ለሁሉ፡፡ አዲስ አበባ፣ ፋር ኢስት ማተሚያ ቤት፡፡

አለማየሁ ዋሴ፡፡(2008)፡፡ እመጓ፡፡ አዲስ አበባ፣ ያሬድ ማተሚያ ቤት፡፡

.......................(2012)፡፡ ሰበዝ፡፡ አዲስ አበባ ፋር ኢስት ማተሚያ ቤት፡፡

አሌክስ አብርሃም፡፡(2011)፡፡ ዙቤይዳ (11ኛ ዕትም)፡፡ አዲስ አበባ፣ ማንኩሳ ማተሚያ ቤት

አማረ ማሞ፡፡(1976)፡፡ የቀለም ጠብታ፡፡ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ መጻሕፍት ድርጅት፡፡

ዘሪሁን አስፋው፡፡(2004)፡፡ የስነ ጽሑፍ መሰረታዊያን፡፡ አዲስ አበባ ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን፡፡(2013)፡፡ አዲስ ፖሊስ መጽሔት፣ ቁጥር 10፡፡ አዲስ አበባ (ማተሚያ ቤት ያልተገለጸ)፡፡

የኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ሀብት ገጽታ፡፡(2010)፡፡ (ያልታተመ)፡፡

የዳውሮ ዞን ባህል፣ ቱሪዝምና የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች መምሪያ፡፡ (2008)፡፡ ዎንታ መጽሔት፣ ቁጥር 11፡፡ አዲስ አበባ፣ ብራና ማተሚያ ድርጅት፡፡

ያሬድ እንግዳ፡፡(2013)፡፡ ቴክ ሳይንስ መጽሔት፣ 7ኛ ዓመት፣ 19ኛ እትም፡፡ አዲስ አበባ፣ የኢፌዴሪ ቴክኖሎጅና ኢኖቬሽን ኢንስቲትዩት፡፡

ደረጀ ገብሬ፡፡(2007)፡፡ ተግባራዊ የጽሕፈት መማሪያ (3ኛ እትም)፡፡ አዲስ አበባ፣ አቢጌት ማተሚያ ቤት፡፡

ደበበ ኃይለ ጊዮርጊስ፡፡(2002)፡፡ የአማርኛ መርጃ መጽሐፍ፡፡ አዲስ አበባ፣ አስቴር ነጋ አሳታሚ ድርጅት፡፡

ዳንኤል ክብረት፡፡(2008)፡፡ የሚከራዩ አማት፡፡ አዲስ አበባ፣ አግዮስ ማተሚያ ቤት፡

ዳኛቸው ወርቁ፡፡(1977)፡፡ የጽሑፍ ጥበብ መምሪያ፡፡ አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፡፡

ጆርዳና፡፡(2007)፡፡ የምግብ አዘገጃጀት ቁጥር አንድ፡፡ አዲስ አበባ፣ ሰሊሆም ማተሚያ ቤት፡፡

ጌታሁን አማረ፡፡(2007)፡፡ የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ (13ኛ እትም)፡፡ አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች፡፡

## የአማርኛ የፊደል ገበታ

| ግዕዝ | ካዕብ | ሣልስ | ራብዕ | ኃምስ | ሳድስ | ሳብዕ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ | ሁ | ሂ | ሃ | ሄ | ህ | ሆ |
| ለ | ሉ | ሊ | ላ | ሌ | ል | ሎ |
| ሐ | ሑ | ሒ | ሓ | ሔ | ሕ | ሖ |
| መ | ሙ | ሚ | ማ | ሜ | ም | ሞ |
| ሠ | ሡ | ሢ | ሣ | ሤ | ሥ | ሦ |
| ረ | ሩ | ሪ | ራ | ሬ | ር | ሮ |
| ሰ | ሱ | ሲ | ሳ | ሴ | ስ | ሶ |
| ሸ | ሹ | ሺ | ሻ | ሼ | ሽ | ሾ |
| ቀ | ቁ | ቂ | ቃ | ቄ | ቅ | ቆ |
| በ | ቡ | ቢ | ባ | ቤ | ብ | ቦ |
| ተ | ቱ | ቲ | ታ | ቴ | ት | ቶ |
| ቸ | ቹ | ቺ | ቻ | ቼ | ች | ቾ |
| ኀ | ኁ | ኂ | ኃ | ኄ | ኅ | ኆ |
| ነ | ኑ | ኒ | ና | ኔ | ን | ኖ |
| ኘ | ኙ | ኚ | ኛ | ኜ | ኝ | ኞ |
| አ | ኡ | ኢ | ኣ | ኤ | እ | ኦ |
| ከ | ኩ | ኪ | ካ | ኬ | ክ | ኮ |
| ኸ | ኹ | ኺ | ኻ | ኼ | ኽ | ኾ |
| ወ | ዉ | ዊ | ዋ | ዌ | ው | ዎ |
| ዐ | ዑ | ዒ | ዓ | ዔ | ዕ | ዖ |
| ዘ | ዙ | ዚ | ዛ | ዜ | ዝ | ዞ |
| ዠ | ዡ | ዢ | ዣ | ዤ | ዥ | ዦ |
| የ | ዩ | ዪ | ያ | ዬ | ይ | ዮ |
| ደ | ዱ | ዲ | ዳ | ዴ | ድ | ዶ |
| ጀ | ጁ | ጂ | ጃ | ጄ | ጅ | ጆ |
| ገ | ጉ | ጊ | ጋ | ጌ | ግ | ጎ |
| ጠ | ጡ | ጢ | ጣ | ጤ | ጥ | ጦ |
| ጨ | ጩ | ጪ | ጫ | ጬ | ጭ | ጮ |
| ጰ | ጱ | ጲ | ጳ | ጴ | ጵ | ጶ |
| ጸ | ጹ | ጺ | ጻ | ጼ | ጽ | ጾ |
| ፀ | ፁ | ፂ | ፃ | ፄ | ፅ | ፆ |
| ፈ | ፉ | ፊ | ፋ | ፌ | ፍ | ፎ |
| ፐ | ፑ | ፒ | ፓ | ፔ | ፕ | ፖ |
| ቨ | ቩ | ቪ | ቫ | ቬ | ቭ | ቮ |

## የፊደል ቅደም ተከተል

ሀ. የመጀመሪያ ፊደል = ግዕዝ

ሁ. ሁለተኛ ፊደል = ካዕብ

ሂ. ሶስተኛ ፊደል = ሳልስ

ሃ. አራተኛ ፊደል = ራብዕ

ሄ. አምስተኛ ፊደል = ሀምስ

ህ. ስድስተኛ ፊደል = ሳድስ

ሆ. ሰባተኛ ፊደል = ሳብዕ

## የኢትዮጵያ ቁጥሮች

| | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ፩ 1 | ፪ 2 | ፫ 3 | ፬ 4 | ፭ 5 | ፮ 6 | ፯ 7 | ፰ 8 | ፱ 9 | ፲ | 10 |
| ፲፩ | ፲፪ | ፲፫ | ፲፬ | ፲፭ | ፲፮ | ፲፯ | ፲፰ | ፲፱ | ፳ | 20 |
| ፳፩ | ፳፪ | ፳፫ | ፳፬ | ፳፭ | ፳፮ | ፳፯ | ፳፰ | ፳፱ | ፴ | 30 |
| ፴፩ | ፴፪ | ፴፫ | ፴፬ | ፴፭ | ፴፮ | ፴፯ | ፴፰ | ፴፱ | ፵ | 40 |
| ፵፩ | ፵፪ | ፵፫ | ፵፬ | ፵፭ | ፵፮ | ፵፯ | ፵፰ | ፵፱ | ፶ | 50 |
| ፶፩ | ፶፪ | ፶፫ | ፶፬ | ፶፭ | ፶፮ | ፶፯ | ፶፰ | ፶፱ | ፷ | 60 |
| ፷፩ | ፷፪ | ፷፫ | ፷፬ | ፷፭ | ፷፮ | ፷፯ | ፷፰ | ፷፱ | ፸ | 70 |
| ፸፩ | ፸፪ | ፸፫ | ፸፬ | ፸፭ | ፸፮ | ፸፯ | ፸፰ | ፸፱ | ፹ | 80 |
| ፹፩ | ፹፪ | ፹፫ | ፹፬ | ፹፭ | ፹፮ | ፹፯ | ፹፰ | ፹፱ | ፺ | 90 |
| ፺፩ | ፺፪ | ፺፫ | ፺፬ | ፺፭ | ፺፮ | ፺፯ | ፺፰ | ፺፱ | ፻ | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፻ | 100 | ፼ | 10000 |
| ፪፻ | 200 | ፪፼ | 20000 |
| ፫፻ | 300 | ፫፼ | 30000 |
| ፬፻ | 400 | ፬፼ | 40000 |
| ፭፻ | 500 | ፭፼ | 50000 |
| ፮፻ | 600 | ፮፼ | 60000 |
| ፯፻ | 700 | ፯፼ | 70000 |
| ፰፻ | 800 | ፰፼ | 80000 |
| ፱፻ | 900 | ፱፼ | 90000 |
| ፲፻ | 1000 | ፲፼ | 100000 |

# አማርኛ

## እንደ መጀመሪያ ቋንቋ

## የተማሪ መጽሐፍ

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ
BIIROO BARNOOTA BULCHINSA MAGAALAA FINFINNEE
ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION EDUCATION BUREAU

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ